Watchman Nee

# የተሸነፈ ዓለም

ትርጉም

ጳውሎስ ፈቃዱ ተሰማ

" Love Not The World"
ከተባለው የዋችማን ኒ  መጽሐፍ የተተረጐመ።

የመጀመሪያ እትም፡  ጥር 1994ዓ.ም

ተርጓሚና አሳታሚ፡  ጳውሎስ ፈቃዱ

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዓይነት መንገድ
ለማባዛት በቅድሚያ ከተርጓሚው የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2002 by Paulos Fekadu

በዚህ መጽሐፍ ከሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች
አ.መ.ት የሚለው  በ1993 ዓ.ም. ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም
አዲስ ትርጉም የሚለው  በ1980 ዓ.ም. ቀለል ባለ አማርኛ ከታተመው
አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዲሁም
ሕያው ቃል የሚለው  በ1988 እ.ኤ.አ ከታተመው ሲሆን የቀሩት በሙሉ
ከድሮው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

የሽፋን ሥዕል ፡ ልዑል ገብርኤል

Translator's Address : Paulos Fekadu
P.O. Box 1614
Addis Ababa
Ethiopia
Tel. Res. 79 19 69
Off. 77 11 24

የኮምፒዩተር ጽሑፍ፦ አስታራ የጽሕፈት አገልግሎት ስ.ቁ 15 29 71

## ማስታወሻነቱ፦

ለሁለቱ የጥበብ ሰዎች፦

- ለደረጀ በላይነህ (ገጣሚና ደራሲ)

እና

- ለልዑል ገብርኤል (ሠዐሊ)

ይሁን።

"ጥበብም በልጆችዋ ጸደቀች"

## የተርጓሚው ቀደምት ሥራዎች

**የዘላለም ኪዳን:-**
(The Better Covenant)




ዕምቅ የሆነውን የቃል ኪዳን ምስጢር መዝዞ፣ የላላ ወገብ የሚያጠብቅ እውነት የጨበጠና በሕይወታችን ከሚያልፈው ሰልፍ የተነሣ የፈዘዘብንን የተስፋ ቃል ዳግም የሚያድስ ነው:: የአዲሱን ኪዳን መርሖዎችንም ፍንትው አድርጎ በማጉላት የተለወጠ የሕይወት አቅጣጫን የሚጠቁም ኮምፓስ በውስጡ የያዘ መጽሐፍ!

**ደራሲ:- ዋችማን ኒ**
**የገጽ ብዛት: 140**
**ዋጋ: 12.00**

**የጋብቻ ኪዳን:-**
(The Marriage Covenant)




ትዳርን ክሩቅ ሆነን እንደ እንከን-የለሽ ገነት ለምናይ አሊያም ደግሞ ውስጡ ገብተን ከሲኦል የባሰ ቃጠሎ ለሆነብን፣ ዴሪክ ፕሪንስ ካለፉበት የሕይወት ልምድ ጋር አጋምደው የተሳካ ትዳርን ምስጢር ያቀረቡበት መጽሐፍ!

**ደራሲ:- ዴሪክ ፕሪንስ**
**የገጽ ብዛት: 64**
**ዋጋ: 6.50**

## ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | 7 |
| 1. | ከአሠራሩ ጀርባ ያለው አእምሮ | 9 |
| 2. | ከእግዚአብሔር የመራቅ ዝንባሌ | 17 |
| 3. | ከውሃ በታች ያለ ዓለም | 25 |
| 4. | ለእኔ የተሰቀለበት | 34 |
| 5. | ልዩ መሆን | 41 |
| 6. | የዓለም ብርሃን | 47 |
| 7. | መላቀቅ | 53 |
| 8. | የእርስ በርስ መነቃቃት | 59 |
| 9. | ሕጎቼን በልባቸው ውስጥ | 67 |
| 10. | ሊመጣ ያለው ዘመን ኀይሎች | 74 |
| 11. | ያለ አግባብ ዙፋኑን የያዘውን መዝረፍ | 81 |

# መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል የተገኘው፣ ዋችማን ኒ (ኒ ቱ-ሼንግ) በሻንጋይ ከተማ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ቻይናና ጃፓን ጦርነት ጀምረው በነበረበት ወቅት በተከታታይ ካደረገው ገለጻ ነው:: ስለዚህ በጥቂቱም ቢሆን በእነዚህ ቀናት ኢኮኖሚያዊ ውጥረት የቀለመ ሊሆን ይችላል:: በእነዚህ ገለጻዎችም ላይ ከ1938-41 በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜዎች በተመሳሳይ ርዕስ ላይ የተደረጉ ንግግሮች ተጨምሮባቸዋል:: ለምሳሌ ሦስተኛው ምዕራፍ በግንቦት 1939 እ.ኤ.አ በተካሄደ የጥምቀት ፕሮግራም በተሰበከ ስብከት ላይ የተመሠረተ ነው:: ለመጽሐፉ መዋቅር በምንጭነት የሚያገለግሉ የጽሑፍ ማስታወሻዎችን የሰጡኝ በርካታ ጓደኞቼም ባለውለታዎቼ ናቸው::

ደራሲው፣ *ከሰምሰን* ከሚታዩ ነገሮች ጀርባ እንደሚገኝ መንፈሳዊ አካል እና ላለመበለጥ ሁልጊዜም በንቃት ልንጠብቀው እንደሚገባ ኀይል ነው የሚመለከተው:: ይህ በክርስቲያኑ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖና ክርስቲያኑም በእርሱ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ፣ ከሙያዊ መዋጮ በመገለል (በመታቀብ) እና በመሳተፍ ጉዳይ ላይ የሚያጋጥመውን ፍጭት፣ እንዲሁም በክርስቶስ ላለ ሰው ፍጻሜ የሆነውን "ገዢነት" ጭምር ትንታኔ ሰጥቶበታል:: እንደ ሁልጊዜውም የዋችማን ኒ ነጥቦች መሠረታዊ እሳቤን የሚያሳዩ ሲሆን፣ ሰዎችን የሚያስቆጣ ቢሆንም አያስፈራውም:: ስለዚህ መጽሐፉ ልብንና አእምሮን ለምላሽ የሚያነሣሣ ሆኖአል:: ትምህርቱም፣ የእግዚአብሔር ሰው በዓለም ውስጥ ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ ሥዕል የሚሰጥ እንዲሆንልን፣ በተጨማሪም የጌታን ስም የምንጠራ ሁሉ ተወዳጁን ልጁን ከሚመለከተው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ጋር በተያያዘ የሚኖረንን ሚና እያሰብን፣ በድፍረት በዚህ ምድራዊ ስፍራ አምንታዊ እርምጃ እንድንራመድ የሚቀሰቅሰን እንዲሆን ጸሎቴ ነው::

አንገስ ኪነር

ለንደን
1968 እ.ኤ.አ.

# ምዕራፍ አንድ

## ከአሠራሩ ጀርባ ያለው አእምሮ

"አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፣ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" (ዮሐ. 12፥31-32)።

ጌታችን ኢየሱስ እነዚህን ቃላት የተናገረው በአገልግሎቱ ቁልፍ ነጥብ ላይ ነው። ወደ ኢየሩሳሌም በጋለ ስሜት በተዋጡ ሰዎች ታጅቦ ቢገባም፣ ወዲያውኑ ሕይወቱን አሳልፎ ስለ መስጠቱ በዘይቤ መናገር ጀመረ፣ ሰማይም በዚህ ለመስማማቷ በሕዝብ ፊት ግልጽ ማረጋገጫ ሰጥታለች። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከላይ በአየነው ጥቅስ ውስጥ ያለው አሳብ ብቅ አለ። "በእልልታ ለተቀበሉት፣ ሊገናኙት ለወጡትና በጉዞውም ላጀቡት ሰዎች ይህ ምንን ያሳያቸዋል?" ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ እንችላለን። የቃላቱ ትርጉም ከገባቸው የእብዛኞቹን ተስፋ ሙሉ በሙሉ የሚያጨልም ምልክት ነው። በእርግጥም እንደ ወንጀለኛ የሚሞትበትን ትክክለኛ ሁኔታ የሚተነብይ መሆኑን ቃላቱን በጥንቃቄ የመረመረ ሰው አይስተውም።

ንግግሩም የነበራቸውን የተሳሳተ እምነት አፍርሶ በምትኩ ድንቅ፣ ጠንካራና አስተማማኝ ተስፋ ይሰጣል። ምክንያቱም የአይሁድ አርበኞች ከጠበቁት እጅግ የሚበልጥ፣ ሥር ነቀል የሆነ የሥልጣን ዝውውርን ያሳያልና ነው። "እኔም ... " በሚለው ቃል የሚጀምረው አገላለጽ ከፊተኛው ዐረፍተ ነገር ጋር ልዩነት እንዳለው ሁሉ፣ በቃሉ የተወከለው ጌታም፣ ከባላንጣው የዚህ ዓለም ገዥ ጋር በተቃራኒነት መቆሙን ይገልጣል። በእርሱም (በክርስቶስ) እስከ መስቀል ሞት መታዘዝ፣ የዚህ ዓለም የጭቆናና የፍርሃት አገዛዝ ከትዕቢተኛ ገዥው መውደቅ ጋር አብሮ አከተመ። በትንሣኤው ደግሞ ሰዎች በፈቃዳቸው እግዚአብሔርን የሚከተሉበት የጽድቅ ዘመነ መንግሥት ተመሠረተ። ልባቸውም ከፍርድ በታች ካለው ዓለም እየራቀ፣ ለመሞት ከፍ ከፍ ባለበት ድርጊት ለመንገሥም ከፍ ከፍ ወዳለው ወደ ኢየሱስ በፍቅር ገመድ ይሳባል።

"ምድር" የዚህ ሁከትና አስደናቂ ውጤቱ የሚፈጸምበት ስፍራ ሲሆን፣ "ይህ ዓለም" ደግሞ የግጭቱ ነጥብ ነው ማለት እንችላለን። ይህንንም ነጥብ የጥናታችን ዋና አሳብ እናደርገዋለን። ለዚህም ከሚጠቅመን የግሪክ ቃል - *ኮስሞስ (kosmos)* ጋር የሚያያዙ የአዲስ

ላል (ያዕ. 4÷4)። ከዚህ የተነሣም ኢየሱስ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም" (ዮሐ. 18÷36) ብሎ ተናግሮአል። ዓለምንም አሸንፎአል (16÷33)። "ዓለምንም የሚያሸንፈው"፣ በእርሱ ላይ ያለን "እምነታችን" ነው (1ዮሐ. 5÷4)። ምክንያቱም ይህንን ትምህርት የጀመርንበት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ያለው ቃል፣ ዓለም ከፍርድ በታች መሆኑን ያረጋግጥልናል። በዚህ ጕዳይ ላይ ደግሞ እግዚአብሔር የማይወላውል አቋም አለው።

ምክንያቱም በሁለተኛ ደረጃ ይኸው ቊጥር ከዚህ አሠራር ጀርባ አንድ አለምር እንዳለ ግልጽ አድርጓልና ነው። ዮሐንስ በተደጋጋሚ ስለ "የዚህ ዓለም ገዥ" ይጽፋል (12÷31፣ 14÷30፣ 16÷11)። በመልእክቱም ውስጥ፣ "በዓለም ያለው" በሚል ያስቀምጠውና (1ዮሐ. 4÷4) በአማኞች ውስጥ ካደረው ከእውነት መንፈስ ጋር ያለውን ተቃራኒነት ይናገራል። "ዓለምም በሞላው" አለ ዮሐንስ፣ "በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን" (5÷19)። እርሱ ዐመፀኛ ኮስሞክራተር (*kosmokrator*) - የዓለም ገዥ ነው። ይህንንም ቃል በብዙ ቊጥር "የጨለማ ዓለም ገዦች" ተብሎ በኤፌሶን 6÷12 ከተጠቀሰው ውጭ በሌላ በየትኛውም ስፍራ አናገኘውም።

ስለዚህ የራሱ የሆነ ሥርዐት ያለው አሠራር - ሰይጣን ከመጋረጃ ጀርባ የሚገዛው "ዓለም" መኖሩ ግልጽ ነው። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 12÷31 ላይ በዚህ ዓለም ላይ ፍርድ መተላለፉን ሲናገር በግዑዙ ዓለም ወይም በነዋሪዎቹ ተፈርዶባቸዋል ለማለት አይደለም። የእነርሱ ፍርድ ገና ወደ ፊት የሚመጣ ነው። በዚያ ስፍራ የተፈረደው ራሱ ሰይጣን ጀማሪና ራስ በሆነበት የዓለም አሠራር ላይ ነው። በመጨረሻም ከዙፋኑ የሚወርደውና ለዘላለም የሚጣለው "የዚህ ዓለም ገዥ" እንደ ሆነ የኢየሱስ ቃል ግልጽ ያደርገዋል (16÷11)።

በዙሪያችን ስላለው ዓለም ከቃለ እግዚአብሔር ጥልቅ መረዳት ማግኘት እንችላለን። ስለዚህ ከግዑዝ ነገሮች ጀርባ ስውር ኀይላት መኖራቸውን መገንዘብ ካልቻልን በእርግጥም ለመታለል የተዘጋጀን ነን ማለት ነው።

በ1 ጴጥሮስ 3÷3-4 ላይ ያለው ምንባብ ይህን ከላይ የተወላውን ነገር እንድናስተውል ይረዳናል። በዚያ ስፍራ ሐዋርያው "ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል፣ ወይም ልብስን በመጐናጸፍ" የሚገኘውን "በውጭ የሆነ ሽልማት (ኮስሞስ)"፣ "በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ" ከሆነው የማይጠፋ ልብስ ጋር ያለውን ጕልህ ልዩነት ሆን ብሎ በማወዳደር ያስቀም



ምጠዋል። እንደዚህ አባባል ከሆነ የመጀመሪያዎቹ ጠፊና ለእግዚአብሔርም ምንም ዋጋ የሌላቸው ናቸው። የጴጥሮስን ዋጋ አሰጣጥ ለመቀበልና ላለመቀበል መፍቀዳችን የቃላቱን እውነተኛ አሳብ እንደ መረዳታችን ይወሰናል። እርሱ ለማለት የፈለገው ልብስን ከመጐናጸፍ፣ ከጌጣጌጦችና ከመኳኳል ጀርባ ለራሱ ግብ የሚንቀሳቀስ አንድ ኀይል መኖሩን ነው። እናም ይህ ኀይል እንዲይዛችሁ አትፍቀዱለት።

ራሳችንን መጠየቅ ያለብን እነዚህን ነገሮች ለማድረግ የሚያነሣሣን ምንድን ነው? ብለን ነው። ምናልባት በየዋህነት፣ ኅብረ ቀለማቱና ሌሎቹ ጌጣጌጦች የሚፈጥሩትን ውበት በማግኘት ለመደሰት በማሰብ ብቻ እንጂ ሥጋዊ ስሜትን በመቀስቀስ ለፍትወት ለማነሣሣት ላይሆን ይችላል። ይህንን ማድረግ ጕዳት አይኖረው ይሆናል፣ ግን እዚህ ጋ ምን እየነካን እንደ ሆነ ዐውቀናል? ከእነዚህ ከሚታዩት ነገሮች ጀርባ ያለውን የተቀናጀ አሠራር፣ የእግዚአብሔር ጠላት የሚቈጣጠረውን አሠራር እየነካን ነውና እንጠንቀቅ!

መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን እንደ ፈጠረ በመግለጽ ነው። ዓለምን አሁን በምንወያይበት መልኩ እርሱ እንደ ፈጠረ ግን አይናገርም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ "ዓለም" ትርጕም እያደገ ሄዶ ወደ ሙሉ መንፈሳዊ ቁምነገር የደረሰው (በተወሰነ ደረጃ ከመዝሙረ ዳዊትና ከነቢያት መጻሕፍት ውጭ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ነው። የዚህን የዕድገት ምክንያት ደግሞ አሁን እናያለን። ከሰው ውድቀት በፊት የዓለም ሕልውና ምድርን፣ የምድርን ነዋሪዎችና የምድርን ነገሮች በሚወክል መልኩ ብቻ ነበር። የተቀናጀውን አሠራር በሚመለከት ምንም ኮስሞስ፣ ምንም "ዓለም" አልነበረም። በውድቀት ጊዜ ግን ሰይጣን ራሱ የነደፈውን ሥርዐት ወደ ምድር ይዞ መጣ፤ በዚህም አሁን የምንነጋገርበት የዓለም ሥርዐት ተጀመረ። አስቀድሞ ይህች ግዑዝ ምድርም ሆነች ሰው፣ በዚህ የሰይጣንን ሥርዐት በሚወክለው መልኩ ከ "ዓለም" ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም። ሰይጣን ግን የሰውን ኀጢአት ተጠቅሞ፣ ራሱ የመሠረተውን መዋቅር ወደ ምድር ለማስገባት በሩ ወለል ብሎ ተከፈተለት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምድር በ "ዓለም" ውስጥ ናት፣ ሰውም በ"ዓለም" ውስጥ ነው። ከውድቀት በፊት የነበረችው ምድር (መሬት) ስትሆን፣ ከውድቀት በኋላ "ዓለም" ነበረች በጌታ ዳግመኛ መምጣት ደግሞ ንጉሣዊ መንግሥት ይመሠረታል ማለት እንችላለን። ልክ ዓለም የሰይጣን እንደ ሆነ ሁሉ፣ መንግሥትም ለጌታችን ለኢየሱስ የተገባ ነው። በተጨማሪም ዓለምን የሚያስወግደውና የሚተካውም ይኸው መንግሥት ነው። ድንጋይም "እጅ ሳይነ

ነው” ተወርውሮ በመምጣት የሰውን የትዕቢት ምስል ሲያንኮታኩተው የዚህ ዓለም መንግሥት “የጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ” ይሆናል (ዳን. 2÷44-45፣ ራእይ 11÷15)።

ፖለቲካ፣ ትምህርት፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ሳይንስ፣ ኪነ-ጥበብ፣ ንግድ፣ ሙዚቃ - ኮስሞስ የተዋቀረባቸውና በየዕለቱ የምናገኛቸው ነገሮች ናቸው። እነርሱን ከቀነሳችሁ አሁን እንደምንለው እንደ ተሳካ አሠራርነቱ የዓለም ሕልውና ያበቃል። የሰውን ዘር ታሪክ ስናጠና በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ጉዳዮች ላይ ተጨባጭ የሆነ ዕድገት እንደ ታየ እንገነዘባለን። ይሁን እንጂ ጥያቄው የዚህ “ዕድገት” አቅጣጫ ወዴት እያዘነበለ ነው? የዚህ ዕድገት የመጨረሻ ግብ ምንድን ነው? የሚል ይሆናል። በመጨረሻ የክርስቶስ ተቃዋሚ እንደሚነሣና የራሱን መንግሥት በዚህ ዓለም እንደሚመሠርት ዮሐንስ ይነግረናል (1ዮሐ. 2÷18፣ 22፣ 4÷3፣ 2ዮሐ. 7፣ ራእይ 13)። ዓለም እየተጓዘበት ያለው አቅጣጫ ይህ ነው። ሰይጣን እያደር ሁሉም ነገር ወደ ክርስቶስ ተቃዋሚው መንግሥት እንዲያመራ ግዑዙን ዓለም፣ የዓለምን ሰዎችና በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች እየተጠቀመ ነው። በዚያ ሰዓት ደግሞ የዓለም አሠራር ቁንጮው ላይ ይደርሳል፣ እናም በዚያ ሰዓት እያንዳንዱ ነገር የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ ይገለጻል።

በዔድን ገነት ምንም ዐይነት የቴክኖሎጂም ሆነ የሜካኒካል መሣሪዎች ፍንጭ እንደ ነበር የዘፍጥረት መጽሐፍ አይነግረንም። ከውድቀት በኋላ ግን ከቃየን ልጆች መካከል ከናስና ከብረት የሚቀጠቀጥ ዕቃና የመቁረጫ መሣሪያዎችን የሚሠራ ሰው ነበር። ለረጅም ዘመናት ሰይፍ ከማረሻ ጋር ሲወዳደር የኖረ ቢሆንም፣ ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በፊት የክርስቶስን ተቃዋሚ መንፈስ ከብረት መሣሪያዎች ጋር አያይዞ መናገር ከሕልም የሚቈጠር ነበር። ዛሬ ግን ብረት በሰው እጅ ለአደገኛ፣ አሥጊና ሕዝብ ጨራሽ ዐላማ እየዋለ ሲሆን፣ ፍጻሜው በተቃረበ መጠን ቴክኖሎጂንና ምህንድስናን አላግባብ መጠቀም እየተስፋፋና ግልጽ እየሆነ ነው።

ለሙዚቃና ለኪነ-ጥበብም እውነታው ተመሳሳይ ነው። በቃየን ቤተሰብ የተጀመሩት በገናና መለከት ዛሬ ባልተቀደሱ እጆች ውለው እግዚአብሔርን የመቃወም (ፀረ-እግዚአብሔር) ባሕርያቸው እየጨመረ ይታያል። በዓለም ላይ በብዙ ስፍራዎች በሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽ፣ በሙዚቃ እና በጣዖት አምላኪነት መካከል ያለውን ትስስር መረዳት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ቀላል ሆኖአል። በእርግጥም የክርስቶስ ተቃዋሚው ባሕርይ በሙዚቃ፣ በጭፈራ፣ በተለያዩ ትዕይንቶችና በድራማ በኩል ከፊት ይልቅ የሚገለጽበት ቀን እየመጣ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።



ንግድማ እንዲያውም ግንኙነቱ የበለጠ ይጠረጠራል። ሰይጣን ከሔዋን ጋር ለራሱ ጥቅም የሚውሉ አሳቦችን ሲለዋወጥ የነበረ የመጀመሪያ ነጋዴ ሲሆን፣ በሕዝቅኤል 28 ላይ የመጀመሪያ ባሕርይውን የሚገልጥ የሚመስለውን “በንግድህ ብልጥግናህን አብዝተሃል፣ በብልጥግናህም ልብህ ኰርቶአል” የሚል ቃል እናነባለን (ቊጥር 5)። ብዙዎቻችን የንግድን ሰይጣናዊ መነሻና ባሕርይ ከልምድ ልናውቅ ስለምንችል ምናልባት ይህ አያከራክረን ይሆናል። ለማንኛውም በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ፊት የምንጨምረው ይኖረናል።

ስለ ትምህርትስ? “እረ ትምህርት ምንም ጉዳት የለውም” ብለን እንደምንቃወም አያጠራጥርም። ለነገሩ ልጆቻችን መማር አለባቸው። ቢሆንም ትምህርት ከንግድ ወይም ከቴክኖሎጂ የማያንስ ከዓለም ነገሮች አንዱ ሲሆን፣ ምንጩም መልካምና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ ነው። እንደ ክርስቲያን፣ በቅንነት ልጆቻችንን በጣም ግልጽ ከሆነው የዓለም ወጥመድ መጠበቅ እንፈልጋለን። ትምህርት እንዲማሩ ማድረግም አለብን። ታዲያ በዋነኛነት የዓለም የሆነውን ነገር እንዲነኩ እየፈቀድን፣ በዚያኑ ጊዜ ከትልቁ የዓለም አሠራርና አደጋ ልንጠብቃቸው መፈለጋችን የሚፈጥረውን ችግር እንደ ምን መፍትሔ ልናገኝለት እንችላለን?

ሳይንስስ? ይህም ኮስሞስን ካዋቀሩት ክፍሎች አንዱ ነው። ደግሞም ዕውቀት ነው። ሳይንስ ወደ ፊት የሚደርስበትን ነገር ስንገምት፣ የግዑዙን ዓለምና የሰውን ባሕርይ ስናመዛዝን፣ ሳይንሳዊ ምርምርና ግኝት ሕጋዊና ተገቢ የሚሆነው እስከ ምን ድረስ ነው? ከዕውቀት ውስጥ ጠቃሚ በሆነውና ጐጂ በሆነው መካከል መለያ መስመሩ የት ላይ ነው? ዕውቀትን እየፈለግን በሰይጣን መረብ ከመያዝ ራሳችንን የምንከላከለውስ እንዴት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች መነሣታቸው አይቀርም።

በእርግጥ እነዚህ ልንመለከታቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ለአንዳንዶች ነገሮችን የማጋነን መስዬ እንደምታያቸው ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን ነጥቤን ለማምጣት ይህ ያስፈልገኛል። ምክንያቱም “ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም” (1ዮሐ. 2÷15)። በመጨረሻም የዓለምን ነገር ስንነካ “ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?” ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን።

ለእኛ ከዓለም ጋር ለመገናኘት ወደ ዓለም የምንሄድበት ጊዜ አልፎአል። ዛሬ ዓለም ራሱ ፈልጐን ወደ እኛ እየመጣ ነው። ሰዎችን ምርኮኛ የሚያደርግ ኀይል በውጭ አለ። ለመሆኑ እስከ ዛሬ የዓለም ኀይል ተሰምቷችሁ ያውቃል? ስለ ምግብና ስለ ልብስ እንዳሁኑ ጊዜ

አስባችሁ ታውቃላችሁ? የትም ሂዱ የት፣ የዓለም ነገሮች በክርስቲያኖች መካከል እንኳ የመወያያ ርዕሶች ናቸው። ዓለም፣ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ድረስ ተንሰራፍቶ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን እንኳ ለመያዝ የሚጥር ሆኖአል። በነገሮች ሁሉ ነጻ የምንወጣበትን የክርስቶስን የመስቀል ኀይል እንደ አሁኑ ማወቅ የሚያስፈልግበት ጊዜ ከዚህ በፊት ኖሮ አያውቅም።

ከዚህ በፊት ስለ ኀጢአትና ስለ ተፈጥሯዊ ሕይወት ብዙ አውርተናል። በዚያም ብዙ መንፈሳዊ ጉዳዮችን አይተናል፤ ነገር ግን ዓለምን በተመለከተ ትልልቅ መንፈሳዊ ጉዳዮች እዚህም እንዳሉ የገባን በጥቂቱ ነው። "በዓለም ባሉት ነገሮች" ሰዎችን ወደ ራሱ አሠራር ለማጥመድ የሚፈልግ መንፈሳዊ ኀይል ከዚህ ዓለም ጀርባ አለ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ራሳቸውን በንቃት መጠበቅ ያለባቸው ከኀጢአት ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም ገዥም ጭምር ነው። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን ለክርስቶስ አጽናፍ-አቀፍ አገዛዝ ለማዘጋጀት እየገነባት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀናቃኙም ለክርስቶስ ተቃዋሚው ከንቱ ንግሥ መግነኛና ማክተሚያ የዚህን ዓለም አሠራር እያነጸ ይገኛል። በማንኛውም ጊዜ የሰይጣንን ዘላቂነት የሌለው የመንግሥት ግንባታ ሳናውቅ ስናግዝ እንዳንገኝ በጣም ጠንቃቃ መሆን አለብን። በዛ ያሉ አማራጮችና መንታ መንገዶች ሲያጋጥሙን ጥያቄያችን "ይህ መልካም ነው ወይስ ክፉ?"፣ "ጠቃሚ ነው ወይስ ጐጂ?" የሚል መሆን የለበትም። ራሳችንን መጠየቅ ያለብን *ይህ የዓለም ነው፣ ወይስ የእግዚአብሔር?* ብለን ነው። በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ያለው ግጭት አንድ ብቻ ስለሆነ፣ ሁለት የሚጋጩ ጉዳዮች በፊታችን ሲያጋጥሙን የሚኖረን ምርጫ "እግዚአብሔር … ወይስ ሰይጣን?" ከሚለው አያንስም።



## ምዕራፍ ሁለት

## ከእግዚአብሔር የመራቅ ዝንባሌ

እያንዳንዳችን ከኀጢአት በታች ተገዝተን ስለ ኖርን፣ ኀጢአት የሆኑ ነገሮች በሙሉ ሰይጣናዊ እንደ ሆኑ እናምናለን። የዚህ ዓለም ነገሮችም የዚያኑ ያህል ሰይጣናዊ መሆናቸውንስ ምን ያህል እናውቃለን? በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙዎቻችን እንደምናመነታ አስባለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን "ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ" በግልጽ ይናገራል (1ዮሐ. 5÷19)። ጠቅለል አድርጎ ለመናገር፣ ሰይጣን ኀጢአትነታቸው ግልጽ በሆኑ ነገሮች እውነተኛ ክርስቲያኖችን ለማጥመድ መሞከር ከንቱና ፍሬቢስ እንደ ሆነ በደንብ ያውቃል። እነርሱም እነዚህ ነገሮች የሚያመጡት አደጋ ስለሚገባቸው ያመልጡታል። ስለዚህ እርሱም በዚህ ፋንታ በጣም የዋህ የሆኑትን ሰዎች ሳይቀር እንዲያጠምዱ ሆነው የተጠላለፉ የማባበያ መረቦችን ፈጠረ። በኀጢአት የተሞሉ ምኞቶችን ለመሸሽ በቂ ምክንያት ቢኖረንም፤ ሳይንስ፣ ኪነ-ጥበብና ትምህርትን ወደ መሳሰሉ የማያስከፉ ነገሮች ስንመጣ ግን በቀላሉ በማባበያው እንማረካለን።

ነገር ግን ጌታችን ስለ ፍርድ የተናገረው ዐረፍተ ነገር "ዓለምን" ያዋቀሩት ነገሮች በሙሉ ከእግዚአብሔር ዕቅድ ውጭ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል። "አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል" የሚለው ቃሉም ለኮስሞስ ግንባታ በሚውሉ ሁሉ ላይ የሚመጣውን ኩነኔ ያመለክታል። የሆነ መሠረታዊ ብልሽት ባይኖር ኖሮ ይህ ቃል ባልተነገረም ነበር። በተጨማሪም ኢየሱስ "አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል" በማለት ንግግሩን ሲቀጥል በሰይጣንና በዓለም ሥርዐት መካከል ያለውን የቅርብ ትስስር ብቻ ሳይሆን፣ ፍርዳቸውም የተያያዘ እንደ ሆነ እያስረገጠ ነው። ዛሬ ሰይጣን የትምህርት፣ የሳይንስ፣ የባህል፣ እንዲሁም የኪነ-ጥበብ ገዥ እንደ ሆነና እነርሱም ከእርሱ ጋር እንደ ተፈረደባቸው ገብቶን ይሆን? የዓለምን ሥርዐት የሚገነቡት የእነዚህ ነገሮች መሪ ሰይጣን መሆኑንስ እናውቃለን?

የጭፈራ አዳራሽ ወይም የምሽት ክለብ ሲጠቀስ እንደ ክርስቲያንነታችን የተቃውሞ ምላሽ እንሰጣለን። ምክንያቱም ይህ ለእኛ ከፍተኛው "ዓለም" ነው። በሌላ በኩል የሕክምና ሳይንስ ወይም ሌላ ማኅበራዊ አገልግሎት ለውይይት ቢቀርብ ግን ከቶውንም እንዲህ ዐይነት ምላሽ አይኖረንም። ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንዳንዶቹን በዝምታ ስንቀበላቸው፣ የቀሩትን ደግሞ በጋለ ስሜት እንደግፋቸዋለን።

ከእነዚህ ጽንፎች መካከል ደግሞ ትክክለኛውን መለያ መስመር የትማስመር እንዳለብን የማንስማማባቸው፣ ለመልካም ወይም ለክፉ በሚያሳድሩት ተጽዕኖ በስፋት የሚለያዩ ሌሎች በርካታ ነገሮች አሉ። የዚህ ዓለም በሆኑ ነገሮች በሙሉ - በከፊል ሳይሆን በሁሉም ላይ ፍርድ በእግዚአብሔር እንደ ተበየነባቸው እውነታውን መቀበል ግን አለብን።

እስቲ ራሳችሁን ፈትኑ። ወደ እነዚህ ተፈላጊ መስኮች መሰማራት ብትሞክሩና የሆነ ሰው መጥቶ "ዓለምን እኮ እየነካችሁ ነው" ብሎ በመደነቅ ቢጠይቃችሁ ከስፍራችሁ ትነቃነቃላችሁ? በፍጹም! እንድትጠራጠሩ ለማድረግ እንኳ አንድ በትክክል የምታከብሩት ሰው መጥቶ በቀጥታና በቅንነት "እዚህ ጋ ከሰይጣን ጋር እየተባበራችሁ እኮ ነው!" እንዲላችሁ ያሻል። አይደል? ማንም መጥቶ "እዚህ ጋ ትምህርትን ነክታችኋል" ወይም "የሕክምና ሳይንስን ነክታችኋል" ወይም "ንግድን ነክታችኋል" ቢላችሁ ምን ይሰማችኋል? "እዚህ ጋ ዲያብሎስን ነክታችኋል" ቢላችሁስ የምትወስዱት የጥንቃቄ መጠን ተመሳሳይ ነውን? ዓለምን ካዋቀሩት ከእነዚህ ነገሮች ማንኛውንም ስንነካ የዚህን ዓለም አምላክ እንደምንነካ በትክክል ከገባን፣ በማንኛውም መንገድ ከዓለማዊ ነገሮች ጋር ላለመተባበር ጥንቃቄ መውሰድ እንዳለብን ኅሊናችን ጠቆም ሳያደርገን አይቀርም። "ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን" - በከፊል ሳይሆን በሞላው። ሰይጣን እግዚአብሔርን የሚቃወመው በሰዎች ልብ በሚኖረው ኀጢአትና ሥጋዊነት ብቻ እንደ ሆነ ለቅጽበት እንኳ ማሰብ የለብንም፤ እርሱ እግዚአብሔርን የሚቃወመው በእያንዳንዱ ዓለማዊ ነገር ሁሉ ነው። የዓለም ነገሮች በሙሉ ግዑዝ፣ ሕይወት አልባና እናንተን ለመጉዳት ምንም ኀይል እንደሌላቸው ከእናንተ ጋር እስማማለሁ። ቢሆንም መለኮታዊ ሕይወት እንደሌለበት እንደ ማንኛውም ነገር ሁሉ፣ እነርሱም የእግዚአብሔር ዕቅድ ተቃዋሚ ለመሆናቸው ያ ራሱ በቂ ምስክር ነው።

በዘፍጥረት 1 ላይ የምናገኘው "እንደ ወገኑ" የሚለው ተደጋጋሚ ሐረግ ጠቅላላውን የሥነ ሕይወት ሂደት የሚገዛ የመባዛት ሕግ ነው። የመንፈስን ክልል ግን አይገዛም። ለብዙ ትውልዶች ዘመን ወላጆች እንደ ወገናቸው ልጆችን ሲወልዱ ኖረዋል፤ አንድ ነገር ግን እርግጠኞች ነን፤ ክርስቲያኖች ክርስቲያኖችን አይወልዱም! ሁለቱም ወላጆች ክርስቲያን ቢሆኑ እንኳ የሚወልዷቸው ልጆች ወዲያውኑ ክርስቲያን አይሆኑም። በመጀመሪያው ትውልድም ይህ አልሆነም። ይህ ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን አዲስ ሥራ ይፈልጋል።

ይህ መርሕ ደግሞ ይበልጥ የሰው ዘር ጉዳዮችን በስፋት ይመለከታል። የሰብአዊ ፍጥረት የሆኑ ነገሮች በሙሉ በዚህ መልክ ይቀጥ



ላሉ፤ የእግዚአብሔር የሆኑት በሙሉ ግን የሚቀጥሉት የእግዚአብሔር ሥራ እስከ ቀጠለ ድረስ ብቻ ነው። ዓለም ደግሞ ሁሉንም የሚያጠቃልልና የእግዚአብሔርን ርዳታና መለኮታዊ እገዛ ሳይፈልግ በራሱ መቀጠል የሚችል ነው። ይህም የዓለም እና የዓለም ነገር ሁሉ ባሕርይ ሲሆን፣ በዚህም ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒው ይጓዛል። ይህንን ዐረፍተ ነገር ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከክርስቲያናዊ ልምምድ አኳያ በምሳሌ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው።

አስቀድመን የፖለቲካ ሳይንስን እንውሰድ። የእስራኤል የብሉይ ኪዳን ታሪክ፣ በጣም ከፍተኛ መብቶች የተሰጣትን አገርና አስተዳደሯን በምሳሌነት ይሰጠናል። እንደ ተጻፈልን የእስራኤል ሕዝብ በዙሪያቸው እንደሚገኙ አሕዛብ መሆን ፈለጉና ልባቸው ንጉሥን በማንገሥ ፍላጐት ተሞላ። ሳኦልን መምረጣቸውን ለጊዜው እንተወውና በመጨረሻ፣ እግዚአብሔር መንግሥቱን በእርሱ ምሪት የሚመሠርትና እንደ ልቡ የሚሆንለትን ንጉሥ በራሱ ጊዜ ለሕዝቡ ወደ መስጠቱ እንለፍ።

ይህ በግልጽ የእግዚአብሔር ሥራ ቢሆንም፣ ንጉሣዊ አገዛዙ በባሕርይው "እንደ አሕዛብ" ከእግዚአብሔር ርቆ የሚጓዝ መሆኑ ተረጋግጦአል። ምክንያቱም በመጀመሪያ ደረጃ ገና ከመነሻው ዓለማዊ (ከዓለም የተኮረጀ) ነገር ስለ ነበር፣ ከዓለማዊ ነገሮች ጋር ሁሉ እንደሚሆነው፣ ከመለኮታዊ ዕቅድ ጋር ግጭት የሚፈጥር ነው። በዓለም ውስጥ የአንድ አገር መንግሥት ለራሱ ከተተወ፣ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ ይበልጥ ከእግዚአብሔር ይርቃል። በሌሎች የአሕዛብ መንግሥታት ፖለቲካ እውነት የሆነው ነገር ሁሉ፣ በእግዚአብሔር በተመረጠችው በእስራኤልም በእኩል ሁኔታ ሠርቶአል። ልክ እግዚአብሔር በእነርሱ ምትክ የሚፈጽማቸውን የተወሰኑ ተግባሮች ሲያቆም፣ የእስራኤል መንግሥትም ወደ ጣዖታዊ የፖለቲካ ሥርዐት የሚዋልል ይሆናል። በእርግጥ በተደጋጋሚ ወደ እግዚአብሔር መመለሳቸው እውነት ቢሆንም እንኳ ተሐድሶው የሚመጣው በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ብቻ ነው። ያለዚህ ጣልቃ ገብነት ደግሞ ሁልጊዜም ቁልቁል ማምራታቸው አይቀርም።

በንግድም በኩል የዚሁ ዐይነት ሁኔታ እውነት መሆኑ ብዙም አያስደንቀንም። በተጨማሪም እንደ ንግድ፣ ታማኝነትን ማጉደል የሚፈታተንበትና ብልሹ ድርድር የሞላበት ሌላ ጉዳይ ያለ አይመስለኝም። ስለዚህ ጉዳይ ደግሞ ሁላችንም የምናውቀው ነገር ይኖራል። ውድድር በሞላበት የንግድ ዓለም፣ ቀጥተኛ መሆንና ጉዳዮችን በታማኝነት መወጣት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደ ሆነ ሁላችንም ይገባናል። ብዙዎችም ይህ የማይቻል - ለማድረግ ቢፈለግም እንኳ በልዩ መልኩ በእግዚአብሔር ላይ የተጣለ ሕይወትን የሚጠይቅ ነው ይላሉ።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ሁለት የተለያዩ ሰዎች - ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ነፍሱን ስላጐደለ ሰውና አንዲት ዋጋዋ እጅግ የበዛ ዕንቍ ለመግዛት ያለውን በሙሉ ስለ ሸጠ ነጋዴ መናገሩን እናስታውሳለን። ጌታ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማይን ያያያዘው ከዚህ ከኋለኛው ነጋዴ ጋር ነው (ማቴ. 16፥26፣ 13፥45-46)። ሌሎችም ሰዎች በንግዳቸው ውስጥ ተመሳሳይ ባሕርይ እንዲኖራቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ያን ቀሰቀሳቸዋል። ለነገሩ ትርፋቸውን ለወንጌል ሥርጭትና ለተለያዩ መለኮታዊ ሥራዎች የሚሰጡ የንግድ ድርጅቶች ጥቂት አይደሉም።

ከእነዚህ የንግድ ድርጅቶች መካከል አብዛኞቹ መጀመሪያ የተመሠረቱት እግዚአብሔርን በሚፈራ ሰው ነው። ዛሬ እግዚአብሔርን መፍራት ከሰማይ ሲሰጥ ብቻ የሚገኝ ባሕርይ ቢሆንም፣ ጉበዝ ነጋዴ በመሆን የሚፈጠረውን ትርፋማ ድርጅት ጠብቆ ለማቆየት ግን የሚያስፈልገው የራስ ጥረት ብቻ ነው። በዚህ ኩባንያ የመጀመሪያ ትውልድ ታሪክ፣ ያኔ ዓለማዊ ሥራ የሆኑትን ነገሮች ሳይቀር በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር በጥንቃቄ ለመያዝ የሚያስችል መለኮታዊ ሕይወት በመሥራቾቹ በኩል ይተላለፍ ነበር። በሁለተኛው ትውልድ ግን ያ ቍጥጥር ተወገደና ማንም እንደሚጠብቀው ወዲያውኑ ንግዱ ወደ ዓለም-አሠራር ዘቀጠ። እግዚአብሔርን መፍራት ጠፍቶአል፤ ኩባንያው ግን እስካሁን እያደገና እየተስፋፋ ነው።

ዕርሻን ደግሞ ከዚህ ነጻ እንደ ሆነ መገመታችን አይቀርም። ባልሠለጠነው የእንስሳትና የግብሬ ዓለም ዘመን የተጻፈው የዘፍጥረት መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ የሚነግረን ነገር አለው። በአዳም ውድቀት ጊዜ እግዚአብሔር አዳምን "ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደ ወጣህ በት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ" ለማለት ተገድዶ ነበር። ቢሆንም የሕይወት ዛፍ ለምልሞ በሚገኝበት በዔድን፣ ማንም ግብርና ወይም አትክልተኝነት ስሕተት ነው ማለት አይችልም። እንዲያውም ዕርሻን የጀመረው እግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሔር እጅ በታች መሆኑ ሲቀር ግን ተበላሸ። ሰው ፍጻሜ ለሌለው ተደጋጋሚ እንግልትና ተስፋ መቁረጥ ስለ ተኮነነ የልፋቱ ፍሬ የተዛባ ነበር። በዚህ መካከል የኖኅ ነጻ መውጣት፣ ምድር አዲስ ጅማሬ ያገኘችበት የእግዚአብሔር ከፍተኛ የተሐድሶ እርምጃ ሆኖ ነበር። እጅግ የሚያሳዝነው ግን ወደ ተቃራኒው ለመቀልበስ ሰው መፍጠኑ ነው! "ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፥ ወይንም ተከለ። ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ፤ በድንኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ"። በእርግጥ ዕርሻ በራሱ ኀጢአት አይደለም፣ የሚጓዝበት አቅጣጫ ግን ከእግዚአ



ብሔር እየራቀ እንደ ሆነ ይህ በቂ ምስክር ነው። ስለዚህ የራሱን የተፈጥሮ ሂደት እንዲከተል ብትተዉት እንደ ምንም ብሎ እግዚአብሔርን የሚቃረን እርምጃ ይከተላል።

የእግዚአብሔር ዕርሻ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ግን የተለየች ናት! በእግዚአብሔር ጸጋና በውስጧ ባለው መንፈስ የተነሣ የሕይወት ኀይል ስላላት፣ ለዚህ ኀይል ምላሽ በመስጠት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር አቅጣጫ ትጓዛለች፤ መንገዱን ከሳተች ግን ከእግዚአብሔር ትርቃለች።

ወደ ትምህርት ጉዳይ ስንመለስ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ልምድ የሚነግሩን ይኖራቸዋል። በምሳሌ ለመናገር፣ እግዚአብሔር ሳኦልን ንቆ ዳዊትን ሲመርጥ፣ በጭንቅላቱ ከተመረጠው ሰው (በዙሪያው ከነበሩት ሰዎች ያን ያህል ይልቅ ስለ ነበር)፣ እንደ ልቡ ወደሚሆንለት ሰው መሻገሩ ነው! ይበልጥ ጥበባቸውን ለሕዝቡ ጥቅም ያዋሉት ዮሴፍ፣ ሙሴና ዳንኤልም እያንዳንዳቸው የሚያስፈልጋቸውን ማስተዋል የተቀበሉት በቀጥታ ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው። በነበራቸው ምድራዊ (መንፈሳዊ ያልሆነ) ትምህርት ላይ ብዙም ልባቸውን አልጣሉብትም። ሐዋርያው ጳውሎስማ ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት ሲል እንደ ጉዳት ከቈጠራቸው ነገሮች መካከል ይህንን ጨምሮታል (ፊልጵ. 3፥8)። በዓለም ጥበብና ከእግዚአብሔር በሚገኘው ጥበብ መካከል ያለውንም ልዩነት በግልጽ አስቀምጦአል (1ቆሮ. 1፥21፣ 30)።

የትምህርትን መሠረታዊ ዓለማዊነት በግልጽ የምንረዳው ግን ከልምድ ነው። በምዕራቡ የዓለም ክፍል የሚገኙ በርካታ ታሪካዊ ዩኒቨርስቲ ኮሌጆች፣ ዜጎቻቸው በክርስትና ተጽዕኖ ሥር ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ በክርስቲያኖች የተመሠረቱ ናቸው። መሥራቾቹ ከነበራቸው መንፈሳዊ ፍሬነገር የተነሣም፣ በመሥራቾቹ የሕይወት ዘመን ሁሉ እነዚህ ተቋሞች የተመሠረቱባቸው መሠረቶች በጉልህ የሚታዩና ተሰሚ ድምፅ ያላቸው ነበሩ። ሰዎቹ ሲያልፉ ግን መንፈሳዊ ቍጥጥሩም ቀረና ትምህርትም ከእግዚአብሔር ርቆ ወደ ቁሳዊው ዓለም አይቀሬውን ጉዳና ተከተለ። ሃይማኖታዊ ልማድ ግን ቶሎ ስለማይሞት፣ በአንዳንድ ስፍራዎች ይህ ረጅም ጊዜ ወስዶ ይሆናል። አካሄዱ ግን ግልጽ ነው። በብዙ ጉዳዮችም ወደ ፍጻሜው ተደርሶአል። ቁሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊ ቍጥጥር ሥር ሲሆኑ ተገቢውን የበታችነት ሚና ይጫወታሉ። ከዚህ ጥብቅ ቍጥጥር ሲላቀቁ ግን ወዲያውኑ ከጀርባቸው ያለውን ኀይል ይገልጻሉ። የተፈጥሮ ሕጋቸው ራሱን ይገልጽና በአካሄዳቸው ዓለማዊ ባሕርያቸው ይገለጣል።

በዚህ ዘመን የሚሲዮናውያን ሥራዎች መስፋፋት፣ ይህንን መርሕ በዘመናችንና በምድራችን ሃይማኖታዊ ተቋሞች እንድንፈትን

ዕድል ይሰጠናል። ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ቤተ ክርስቲያን በቻይና ውስጥ ግልጽ መንፈሳዊ ቃናና ወንጌላዊ ዓላማ ያላቸው ትምህርት ቤቶችንና ሆስፒታሎችን ለማቋቋም ወሰነች። በዚያ ዘመን ለተቋሙ ወንጌልን የማወጅ ሚና ጠንካራ አጽንኦት ሲሰጠው፣ ለሕንጻ ግንባታው እምብዛም ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። ከዐሥር ወይም ከዐሥራ አምስት ዓመት በፊት ወደ እነዚህ ስፍራዎች ሄዳችሁ ቢሆን ግን የበፊቶቹ ትንንሽ ሕንጻዎች ከበፊቱ በጣም የሚልቁና የሚያምሩ ሆነው ታዩ ነበር። ከበፊቱ ጋር ሲነጻጸር ወደ ጌታ ያመጧቸው ሰዎች ብዛት እጅግ አናሳ ነው። ጭራሽ ዛሬ ደግሞ እነዚያ በርካታ ድንቅ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ሙሉ በሙሉ እውነተኛ የወንጌል አሳብ የጐደላቸው፣ ንጹሕ የትምህርት ማዕከላት ብቻ ሲሆኑ፣ በዚያው መጠን አብዛኞቹ ሆስፒታሎችም ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ፈውስ የማይገኝባቸው የአካላዊ ፈውስ ቦታ ብቻ ሆነዋል። የጀመሩ አቸው ሰዎች አካሄዳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ነበር፣ እነዚህን ተቋማት በታማኝነት ለእግዚአብሔር ዕቅድ አቁይተዋቸው ነበር፤ እነርሱ ሲያልፉ ግን ተቋሞቹ ራሳቸው በፍጥነት ወደ ዓለማዊ ደረጃና ግብ ተሳቡ፤ ይህን በማድረጋቸውም ራሳቸውን ከ"ዓለም ነገሮች" ጋር መደቡ። እንደዚህ በመሆኑም ልንደነቅ አይገባም።

በመጀመሪያዎቹ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፎች፣ ቤተ ክርስቲያን ለድኾች ቅዱሳን ርዳታ እንድታደርግ ስላስገደዳት ድንገተኛ ችግር እናነባለን። ያ የአስቸኳይ ጊዜ ድርጊት እግዚአብሔር የባረከው ማኅበራዊ አገልግሎት ቢሆንም፣ በአደረጃጀቱ ጊዜያዊ ነበር። "ቢቀጥል ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር!" ትሉ ይሆናል። እነዚያ የእርዳታ እንቅስቃሴዎች ጊዜአቸው ቢራዘም ኖሮ፣ ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረው መንፈሳዊ ተጽዕኖ ተወግዶ፣ ጕዞው ያለ ጥርጥር በዓለም አቅጣጫ በሆነ ነበር። ይህ የማይቀር ነው።

ይህ የሚሆነው፣ የእግዚአብሔር ሕንጻ በሆነችው ቤተ ክርስቲያንና በአባሎቿ እምነትና ራእይ በምታካሂዳቸው ጠቃሚ ማኅበራዊና የልግስና እንቅስቃሴዎች መካከል፣ ግልጽ ልዩነት ስላለ ነው። ኋለኞቹ በተመሠረቱበት መንፈሳዊ ራእይ ምክንያት፣ በውስጣቸው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንኳ የሌላት በነጻነት የመቆም ኀይል አለ። የሚጀመሩት በእግዚአብሔር ልጆች እምነትና ተነሣሽነት ቢሆንም፣ አንዴ መንገዱና ሙያዊ መዋቅሩ ከተመቻቸ በጌታ ባል ሆኑ የዓለም ሰዎችም ለመተዳደር የሚችሉ ይመስላል።

እንድደግመው ፍቀዱልኝና - የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ግን ጸንታ ለመቆም በእግዚአብሔር ሕይወት ላይ ተደግፋ መኖሯ ግድ ነው። እስቲ በአንድ ከተማ ውስጥ ያለች ሕያው ቤተ ክርስቲያን



ምን ዐይነት የጸሎት ኅብረትና የወንጌል ሥርጭት እንዲሁም በቤት ለቤት ፕሮግራሞች ውስጥ ምን ዐይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንደ ሚኖራት ገምቱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላስ ምን ታገኛላችሁ? የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ከተከተሉት ያ ስፍራ ከመቼውም ይበልጥ በእግዚአብሔር ሕይወት፣ ብርሃንና በቃሉ ኀይል የተሞላ ይሆናል፤ የነበራቸውን የክርስቶስ ራእይ ባለ መታዘዝ ክተዉ ግን በዚያው መጠን ስፍራው ሰዎች ክሂዶተ-እግዚአብሔር የሚሰበኩበት ይሆናል። ከዚያም ቤተ ክርስቲያንነቱ ያበቃል። ምክንያቱም ለቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከእግዚአብሔር ዘንድ አዲስ ሕይወትን ያለ ማቋረጥ መሞላት ያስፈልጋልና ነው። ያለዚያ ደግሞ አንድ ቀን እንኳ መቆም አትችልም።

ነገር ግን ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ በዚህችው ቤተ ክርስቲያን አባላት እምነት የተጀመረ ትምህርት ቤት ወይም ሆስፒታል ወይም ማተሚያ ቤት ወይም ሌሎች ሃይማኖታዊ መሠረት ያላቸው ድርጅቶች አሉ እንበል። ከዐሥር ዓመት በኋላም የእነዚህ ድርጅቶች አስፈላጊነት ቢቀጥልና ሌላ የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት በአማራጭነት ባይኖር፣ ድርጅቱ ውጤታማነቱና የሚመሰገነው የአገልግሎት ደረጃው ሳይቀንስ ሥራውን እንደሚቀጥል እንገምታለን። አንድ ጊዜ እንዴት እንደምናስተዳድረው ካወቅን፣ የተመሠረተው ኮሌጅም ሆነ ሆስፒታል ምንም መለኮታዊ ሕይወት ሳያስፈልገው ሙሉ በሙሉ በውጤታማነቱ ሊቀጥል ይችላል። ራእዩ ይጠፋ ይሆናል፤ እንቅስቃሴው ግን ይቀጥላል። ዓለማዊነቱም፣ ከእግዚአብሔር ሕይወት ውጭ በራሱ ከሚቆም ከማንኛውም ነገር ያነሰ አይሆንም። እንደዚህ ዐይነት ነገሮች ደግሞ "አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል" በሚለው የጌታ አባባል ውስጥ ይጠቃለላሉ።

"ሥራችሁ ምንድን ነው?" ብዬ ብጠይቃችሁ "ሕክምና" ብላችሁ ትመልሱልኝ ይሆናል። ይህንንም ስትመልሱ ሰብአዊነት የተሞላበት ሥራ በመሥራታችሁ ከሚሰማችሁ ኩራት በስተቀር ምንም ዐይነት የአደጋ ሥጋት ሊኖራችሁ ወይም ሌላ የተለየ ነገር ልታስቡ አትችሉም። እሺ፣ የሕክምና ሳይንስ ሰይጣን ከሚቆጣጠራቸው አሠራሮች አንዱ መሆኑን ብነግራችሁስ? ምን ትሆናላችሁ? እንደ ክርስቲያንነታችሁ የተናገርኩትን በቁምነገር ስለምትቀበሉኝ፣ ተደናግጣችሁ ሥራውን መተው የሚሻል መሆኑን ታስቡ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ግን በፍጹም ዶክተርነታችሁን እንዳታቆሙ! በእርግጥ የምትገኙት በጠላት ክልል ውስጥ በመሆኑ ካልተጠነቀቃችሁ ተጠልፋችሁ ልትወድቁ ትችላላችሁና በእርጋታና በማስተዋል መጓዝ አለባችሁ።

መሀንዲስ ወይም ገበሬ ወይም አታሚ ናችሁ እንበል። ነገር ግን የመዝናኛ ስፍራን ወይም መጥፎ ምግባር የሚታይባቸውን የን

ባቸው በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ። እርሱ እንደነገረኝ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የጸለየላቸው ሰዎች በሙሉ ተፈወሱ። ይህ ደግሞ እጅግ አስደ ሰተው። እምነቱ በዚህ መንገድ ተፈትኖ ከተረጋገጠ በኋላ እኔ እርሱን ባገኘሁት ቦታ ላይ ሆኖ ልብስ እየሰፋ ያለ ማቋረጥ ስለ ጌታ ይመሰክራል። ታዲያ እርሱ የጌታን ቃል በቀጥታ ከተቀበለ እኔስ መቀበል አይኖርብኝም?)

ስለዚህ እደግመዋለሁ፣ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል"። "በመጠመቅ በሚገኝ ዳግም ልደት ታምናለህ ማለት ነው? " ብላችሁ ትጠይቁኝ ይሆናል። በፍጹም! "ጌታ እመንና ተጠመቅ፣ ከዚያ ዳግመኛ ትወለዳለህ" አላለም፤ እርሱ ካላለ ደግሞ በዚህ ማመን አይኖርብኝም። የእርሱ ቃል፣ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል" የሚል ነው። ስለዚህ በጥምቀት ደኅንነት ነው የማምነው።

ስለዚህ አሁን የሚነሣው ጥያቄ፣ ይህ ዐረፍተ ነገር ምን ማለት ነው? የሚል ይሆናል። "ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ" ብሎ ጴጥሮስ ለሰጣቸው ልባዊ ምክር ምላሽ "ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ" ብሎ ሉቃስ ሲነግረን ምን ማለቱ ነው? (የሐ.ሥ. 2÷40-41)።

ይህን ለመመለስ አስቀድመን "መዳን" የሚለውን ቃል ትርጓሜ መፈለግ አለብን። ለደኅንነት ያለን በጣም የተሳሳተ አመለካከት ነው ብዬ እፈራለሁ። አብዛኞቻችን ስለ ደኅንነት የምናውቀው ከሲኦል ድኖ ወደ ሰማይ መግባትን፣ ወይም ከእንግዲህ አዲስ ሕይወት እንድንኖር ከኀጢአታችን መዳናችንን ነው። ግን ተሳስተናል። ደኅንነት ከዚህ የሚያልፍ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ብዙ ትኩረትንም ያደረገው በኀጢአትና በሲኦል፣ ወይም በቅድስናና በመንግሥተ ሰማይ ላይ ሳይሆን በሌላ ጉዳይ ላይ ነው።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን መልካም ስጦታ ሲሰጠን የዚያ ተቃራኒ የሆነውን ክፉ ነገር ለመቃወም እንደ ሆነ ሁላችንም እንደ ምናውቅ እገምታለሁ። መጽደቅን የሚሰጠን ኩነኔ ስላለ ነው። የዘላለም ሕይወት የሚሰጠን ሞት በመኖሩ ነው። ይቅርታን ያቀረበልን በኀጢአት ከመኖር የተነሣ ነው። እሺ፣ ደኅንነትንስ የሚሰጠን በምን ምክንያት ነው? ጽድቅ በኩነኔ ምክንያት፣ መንግሥተ ሰማይ በሲኦል ምክንያት፣ ይቅርታም በኀጢአት ምክንያት ከሆነ ደኅንነትስ የሚገኘው ምንን በሚመለከት ነው? ደኅንነት አሁን እንደምናየው ከ*ኮስሞስ* - ከዓለም ጋር የሚያያዝ ነው።

የክርስቶስ የግል ጠላት የሆነው ሰይጣን፣ በዚህች ምድር ላይ የእነዚህን ነገሮች ምሳሌ ለማምጣት የሚጠቀመው በሰው ሥጋ በኩል ነው። አንዳችንም ከዚህ ውጭ አይደለንም። የጠቅላላው ዓለማዊ ዕቅድ



ልዩ ጠባዩ ደግሞ የእግዚአብሔር አብ ተቃራኒ መሆኑ ነው። ሦስቱ የጨለማ ኀይላት - ሥጋ፣ ዓለምና ዲያብሎስ ለሦስት መለኮታዊ አካላት በተቃራኒነት እንደ ቆሙ እናውቃለን ብዬ እገምታለሁ። ሥጋ፣ ጰራቅሊጦስ ለሆነው መንፈስ ቅዱስ በተቃራኒነት የተመደበ ጠላት፣ ሰይጣን ራሱ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ላይ እና ዓለምም አብ ፈጣሪ በመሆኑ ላይ በተቃርኖ ነው የቀረቡት።

አሁን የምንነጋገርበት *ኮስሞስ* በእግዚአብሔር አብ የነገር ሁሉ ምንጭነት ላይ ሁልጊዜም ተቃዋሚ ነው። "መልካም እንደ ሆነ" የሚሉት ቃላት በፍጥረት ጊዜ ስለ ነበረውና አሁንም ስላልተቋረጠው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ የሚሰጡት ፍንጭ አለ። እግዚአብሔር የሰው ልጆች ገዥ የሚሆኑበትና የልጁን መልክ በግልጽ የሚያሳዩበት ሥርዐት በምድር ላይ እንዲኖረው በልቡ ያሰበው ከዓለም ምሥረታ በፊት ነው። ሰይጣን ግን ጣልቃ ገባ። መሬትን እንደ መወጣጫና ሰውን እንደ መሣሪያ ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ንብረት ያለ አግባብ በመንጠቅ በራሱ ዙሪያ የተማከለና የእርሱን ምስል የሚያንጸባርቅ እንዲሆንለት ፈለገ። ስለዚህ ይህ እንግዳ አሠራር ለመለኮታዊው ዕቅድ በቀጥታ የቀረበ ተግዳሮት ነው።

እናም ዛሬ በጠቅላላው የተለያዩና የሚጋጩ ባሕርያት ካላቸው ሁለት ዓለማት - ሁለት የሥልጣን ክፍሎች ጋር ተፋጥጠናል። ዛሬ ጉዳዩ የመንግሥተ ሰማይና የሲኦል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የሁለት ዓለማት ጥያቄ - ክርስቶስ ጌታና የበላይ በሆነበት የነገሮች ሥርዐት እና በተቃራኒው፣ ሰይጣን ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት ሥርዐት መካከል እኔ ወደ የትኛው የመሆኔ ጥያቄ ነው።

ስለዚህ ደኅንነት ኀጢአታችን ይቅር የመባሉ ወይም ሲኦል የመወገዱ ጥያቄ አይደለም። ይልቁን እኛ ከየትኛው ሥርዐት የመሆናችን ሁኔታ ተደርጎ መታየት አለበት። እኔ ስድን ከአንደኛው ግዙፍ ዓለም ወጥቼ ወደ ሌላኛው በመግባት የራሴን እርነት ማካሄዴ ነው። እናም አሁን ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅድ በእምቢታ ለመቋቋም ካደራጀው የተቀናጀ ክልል ድኛለሁ።

ክልሉ - ሁሉን የሚያቅፈው *ኮስሞስ* ብዙ እንግዳ ገጽታዎች አሉት። በእርግጥ ኀጢአትና ምድራዊ ምኞት በዚህ ዓለም ከፍተኛ ስፍራ ቢኖራቸውም፣ ሰዋዊው አእምሮ ከነባህሉና ከነፍልስፍናው፣ ከምርጡ ሰብአዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዘይቤ ጭምር ሁሉም ተጠቃልለው በውስጡ ተካትተዋል። የዓለምን ሃይማኖቶች - በተለይ ዝንጉርጉሮቹ ዓለማዊ ክርስቲያንና "የዓለም ቤተ ክርስቲያን" ከእነዚህ ጋር መመደብ አለባቸው። ተፈጥሯዊው የሰው ኀይል የበላይ በሆነበት

በዚያም ይቈያል። በአዲሱ ሁኔታችሁ አቋም ላይ ስትሆኑ፣ ውሃው የነበራችሁበትን ዓለም ሁልጊዜ እንደሚሸፍነው ትረዳላችሁ። ኖኅና ቤተሰቡን ያዳነው ያው ውሃ፣ ከዚህ በፊት ይኖሩበት የነበረውን ዓለማቸውን አሰጠመው። ስለዚህ ይኸው ውሃ እናንተንና እኔን በክርስቶስ ውስጥ በደኅንነት ስፍራ ሲያስቀምጠን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰይጣንን ጠቅላላ የነገሮች አሠራር ይቀብረዋል። የአዳም ልጅ የመሆናችሁ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ ዓለማችሁም በጥምቀታችሁ ያበቃል። በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ምንም ትንሣኤ የሌለበት ሞትና ቀብር ይካሄዳል። ይህም የሁሉ ነገር ፍጻሜ ነው።

ስለዚህ ከሌላኛው ዓለም ወደ አዲሱ ተሸክማችሁ የምታሻግሩት ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው። በአዳም ውስጥ የነበረው በሙሉ ላይመለስ በዚያው ቀርቶአል። አስቀድማችሁ በአንድ ሱቅ ወይም በቤት ውስጥ ተቀጥራችሁ የምትሠሩ ሠራተኞች የነበራችሁ ትሆኑ ይሆናል። ወይም ምናልባት የንግድ ድርጅቱ ባለቤት፣ ወይም ሥራ አስኪያጅ አሊያም ዳይሬክተር የነበራችሁ ልትሆኑም ትችላላችሁ። ለነገሩ ዛሬም አሠሪ ወይም ሠራተኛ ሆናችሁ ልትቀጥሉ ትችላላችሁ። ወደ መለኮታዊ ነገሮች፣ ወደ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብሔር አገልግሎት ስንመጣ ግን ባሪያም ሆነ ጨዋ፣ ሠራተኛ ወይም አሠሪ የሚባል ልዩነት የለም። እንዲሁም በአዳም ውስጥ ሳላችሁ አይሁድ ወይም አሕዛብ፣ ዝነኛ ወይም በሰው ዐይን ፊት የቀለለ ብዙ ነገር የነበራችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ። በዚህ ውሃ ውስጥ ስታልፉ ግን ጠቅላላው አሠራር ላይመለስ ይሄዳል። በምትኩም አንድ አዲስ ሰው እንጂ አይሁዳዊም ሆነ ግሪካዊ፣ ባሪያም ሆነ ስኩቴስ ወይም ሌላ በሌለበት፣ በክርስቶስ ውስጥ ራሳችሁን ታያላችሁ። መለኮታዊ ምስጢር ባላቸው የወይራ ዛፎችና የወይራ ቅጠሎች ወደ ሚወከለው የነገሮች ሥርዐት ገብታችኋል። ጠቅላላው ወደፊታችሁ "በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ" ይሸፈናል (1ጴጥ. 3÷21)። ይህም እግዚአብሔር ወደ ፈጠረው አዲስ ነገር ሙሉ በሙሉ መሻገራችሁን ያመለክታል። ሮበርት ያንግ ያዘጋጀው (Analytical Concordance of the Holy Bible) እንደሚናገረው አራራት ማለት "ቅዱስ ስፍራ" ማለት ነው። ብቻ ምንም ይሁን ምን፣ በታደሰችው መሬት ላይ ያረፈው መርከብ አዲሱን ፍጥረት በሚወክሉ ፍጥረታት ተሞልቶ ስለ ነበር እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። በክርስቶስ ሞት፣ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አዲስ የሆነ ፍጥረት ወደ መኖር ሲያመጣ፣ ሰውንም በክርስቶስ ትንሣኤ ወደዚህ እያስገባው ነው። በክርስቶስ፣ እናንተና እኔም እዚያ ነው ያለነው።

ባንጠመቅ አለመጠመቃችን የሚያመጣውን ለውጥ ብትጠይቁ፣ ጌታ ራሱ ያዘዘው መሆኑን በመናገር መልስ እሰጣችኋለሁ



(ማቴ. 28÷19)። በዚህም ላይ እርሱ ራሱ እንዳያደርግ ሲጠየቅ እምቢ ብሎ የፈጸመው እርምጃ ነው (ማቴ. 3÷13-15)። ጴጥሮስም ጥምቀት ለእግዚአብሔር የበጎ ኅሊና ልመና፣ ወይም መማጸኛ፣ ወይም ምስክርነት እንደ ሆነ ያብራራል (1ጴጥ. 3÷21)። ምስክርነት እወጃ ነው። ስለዚህ ይህን በመፈጸም የምታስተላልፉት ነገር ይኖራል፤ ምናልባት ቃላት ባትጠቀሙም፣ የቆማችሁት የት እንደ ሆነ በድርጊታችሁ ብቻ ታውጃላችሁ። በውሃው ውስጥ በማለፍ፣ ዓለማችሁን ወደ ኋላ ትታችሁ አዲስነቱ ወደሚነገርለት ወደ ሌላ ነገር መግባታችሁን ለመላው አጽናፈ-ዓለም ይፋ ታደርጋላችሁ። ይህ ደኅንነት ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ባስቀመጣችሁ ስፍራ በሕዝብ ፊት አቋም ትወስዳላችሁ።

ይህም ደኅንነትን ከሲኦልና ከኀጢአት ጋር ካያያዝን ልንተረጉማቸው የሚያስቸግሩንን፣ በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የምናገኛቸውን ደኅንነትን የሚመለከቱ ምንባቦች ለመተንተን ይረዳናል። ለምሳሌ ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ለነበረው የወኅኒ ጠባቂ የተናገሩትን አስቸጋሪ ቃላት ያበራልናል። ጠባቂው፣ "እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" ብሎ ጠየቀ። እናንተ ብትሆኑ ምን ብላችሁ ትመልሱለታላችሁ? የዚህ ዘመን ጥሩ የወንጌል ሰባኪ ከሆናችሁ፣ በእርግጠኝነት "በጌታ ኢየሱስ እመን ትድናለህ" ትሉታላችሁ። ጳውሎስ ግን "አንተና ቤተ ሰዎችህም" የሚል ቃል ጨመረበት። እንዴ ምን ማለትህ ነው? እኔ በጌታ ኢየሱስ ካመንኩ እኔና ቤተሰቤ እንዴት እንድናለን? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። አሁንም እንደገና መጠንቀቅ አለብን። ጳውሎስ በጌታ ኢየሱስ እመን፣ አንተና ቤተሰቦችህ የዘላለም ሕይወት ታገኛላችሁ አላለም። እርሱ "በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ" ነው ያለው (የሐሥ. 16÷31)። የእርሱ ትኩረት በነገሮች ሥርዐት ላይ እና የወኅኒው አለቃ ከዚህ አሠራር እንዲወጣ ከመፈለጉ ላይ መሆኑን አስታውሱ። ያ ሰው የቤተሰቡ ራስ እንደ መሆኑ ከዚያን ቀን ጀምሮ እርሱና ቤተሰቡ ጌታን እንደሚከተሉ ይፋ ሲያደርግና ይህም በሕዝብ ሲታወቅ፣ በመንገድ የሚያልፉ እንኳ ወደ ቤቱ እየጠቆሙ "ክርስቲያን ቤተሰብ" ናቸው ይላሉ።

መዳን ማለት ይህ ነው። የእናንተ ስፍራ በሌላ የነገሮች አሠራር መሆኑን ታውጃላችሁ። ሰዎችም ወደ እናንተ እያመለከቱ፣ "አዎን የክርስቲያን ቤተሰብ ነው፣ የጌታ ናቸው!" ይላሉ። ጌታ ለእናንተ የሚመኘው ደኅንነት፣ "የእኔ ዓለም ተወግዶአል፣ እኔም ወደ ሌላ ገብቻለሁ" በማለት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የምትፈጽሙትን ምስክርነት ነው። ከአሮጌውና ከተፈረደበት ሥርዐት ሙሉ በሙሉ ተነቅለን በምትኩ በአዲሱና በመለኮታዊው በጥልቀት ተተክለን ራሳችንን እንድናገኝ፣ ጌታ እንዲህ ዐይነቱን ደኅንነት ይስጠን!

ይህ ሁሉ የከበረና እምንታዊ ጐን ስላለው እግዚአብሔር ይመስገን! ጴጥሮስ፣ የዳንነው "በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው" ይልና ንግግሩን በመቀጠል፣ "እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኀይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ አለ" ይለናል (1ጴጥ. 3፥22)። እግዚአብሔር ለልጁ በሁሉ ነገር ላይ ልዕልና በመስጠት ሥልጣናትን በሙሉ የበታቹ አድርጎለታል። ይህን ማድረግ የቻለው እግዚአብሔር፣ እኔን - ሥጋዬንና ነፍሴን ወደ ሌላ ክልል ለማስገባት በደንብ የሚችል ነው።

እንደገና መግለጽ ቢያስፈልግ፣ ያሉት ሁለት ዓለሞች ናቸው። በአንድ በኩል፣ ከሰይጣን ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ዓለም በአዳም ውስጥ ሲኖር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ አዲስ ፍጥረት የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚንቀሳቀስበት ክልል አለ። እናንተና እኔ ከአንደኛው ክልል፣ ከአዳም ወጥተን ወደ ሌላኛው ክበብ፣ ወደ ክርስቶስ የምንገባው እንዴት ነው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ እርግጠኛ ካልሆናችሁ አንድ ሌላ ልጠይቃችሁ። ቀድሞ ነገር ወደ አዳም የገባችሁት እንዴት ነው? የገባችሁበት መንገድ አወጣጣችሁን ይጠቁማል። ወደ አዳም ውስጥ የገባችሁት በአዳም ዝርያ ውስጥ በመወለዳችሁ ነው። ታዲያ ወደ ክርስቶስስ እንዴት ትገባላችሁ? መልሱ ተመሳሳይ ነው - በመወለድ። ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የመግቢያው መንገድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሣት፣ ለሕያው ተስፋ ዳግመኛ በመወለድ ነው (1ጴጥ. 1፥3) ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ስለ ተባበራችሁ ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ከእርሱ ጋር ተባብራችኋል (ሮሜ 6፥5)። ሞት ከአሮጌው ዓለም ጋር የነበራችሁ ግንኙነት መደምደሚያ ሲሆን፣ ትንሣኤ ደግሞ ወደ አዲሱ ዓለም - ወደ ሕያው ኅብረት ያመጣናችኋል።

በመጨረሻ፣ ክፍተቱን የሚሸፍነው ምንድን ነው? በሁለቱ ዓለማት መካከል ያለው መወጣጫ ምንድን ነው? መቀበር አይደለ ምን? "ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" (ሮሜ 6፥4)። "ከእርሱ ጋር ተቀብረናል" የሚሉት ቃላት ያለ መወላወል ስለ ፍጻሜ ያሳዩናል። በአዳም ውስጥ የነበረን ታሪክ በክርስቶስ ሞት አብቅቶአል። ስለዚህ ከመቃብሩ ስፍራ ስሄድ፣ "ያበቃልኝ" ሰው ነኝ ማለት እችላለሁ። ነገር ግን ይህ እውነት ሌላ ጐን አለው። እግዚአብሔር ይመስገን! "ክርስቶስ ... ከሙታን እንደ ተነሣ"፣ እኔም ከውሃው ወጥቼ ስንዝ፣ "በአዲስ ሕይወት" እመላለሳለሁ (6፥4)።

የመስቀሉን ሁለት ውጤቶች ከዚህ ቀደም በሚለው ቍጥር - ሮሜ 6፥3 ላይ ማየት ይቻላል። "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ



እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?" ይህ ነጠላ ዐረፍተ ነገር ሁለቱን የጥምቀት ገጽታዎች እንደገና ያሳያል። ይህም ወደ ሁለት ነገሮች ውስጥ መጠመቅ ነው። ያመንን በመጀመሪያ "ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ *(በሞቱ ውስጥ)*" ተጠምቀናል። ይህ አስደናቂ እውነት ነው። ግን እዚህ ላይ አላበቃም። በሁለተኛ ደረጃ፣ "ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ *(በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ)*" ተጠምቀናል ብሎ ያው ቍጥር ይናገራል። በክርስቶስ ሞት ውስጥ በመጠመቄ ከዚህ ዓለም ጋር የነበረኝ ግንኙነት ሲደመደም፣ እንደ ሕያው ሰውነቱና የአዲስ ዘር ራስነቱ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ መጠመቄ ሙሉ በሙሉ አዲስ የሆነ የነገሮች ዓለም ከፍቶልኛል። "ከፍ ከፍ" ያለው የሰው ልጅ ወደ ራሱ ከሳበኝ ቀን ጀምሮ ወደ ውሃው በመግባት "የዚህ ዓለም ፍርድ" እውነት እንደ ሆነልኝ በቀላሉ በሕዝብ ፊት እያጸናሁ፣ ሁሉን ነገር አሳያለሁ።

ለፍጥረት ሁሉ መስበክ ያለበት ድንቅ ወንጌል!

# ምዕራፍ አራት

## ለእኔ የተሰቀለበት

ለእግዚአብሔር መለየት - ከዓለም መለየት የክርስትና ሕይወት ተቀዳሚ መርሕ ነው። ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ባየው ራእዩ፣ ሁለት የማይታረቁ ጽንፎችን፣ ሁለት በሞራል የተራራቁ ዓለማትን ተመልክቶአል። በቅድሚያ የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት የሆነችውን ባቢሎንን ያይ ዘንድ በመንፈስ ወደ በረሃ ተወሰደ (17÷3)። ቀጥሎ ደግሞ ኢየሩሳሌምን፣ ሙሽራይቱን፣ የበጉን ሚስት ወደሚመለከትበት ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ በዚያው መንፈስ ተወሰደ (21÷10)። ንጽጽሩ ፍንትው ብሎ የሚታይ ስለ ሆነ ከዚህ በላይ መግለጽ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

እኛ ሙሴንም ሆነ በለአምን ብንሆን፣ ነገሮችን በእግዚአብሔር ዕይታ ለመመልከት እንደ ዮሐንስ ወደ ተራራ ጫፍ መውጣት አለብን። ብዙዎች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ ለማየት አልቻሉም፣ ቢያዩም እንኳ በከፍታ ላይ በመቆየታቸው ብቻ ስለሚረኩ የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደ ደረቅ አስተምህሮ ብቻ ተረድተውት ያልፋሉ። ደግሞም መገለጥ ብቻ እንጂ፣ መረዳት ወደ የትም አያደርሰንምና በበረሃ ስለ ባቢሎን የሆነ ነገር ልናይ እንችል ይሆናል፣ አዲስትዋን የእግዚአብሔር ኢየሩሳሌም ለማየት ግን መንፈሳዊ መገለጥ ያስፈልገናል። አንድ ጊዜ ካየን ደግሞ ሳንለወጥ አንቀርም። እንደ ክርስቲያንነታችን ሁሉ ነገር በዐይኖቻችን መከፈት ላይ የተወሰነ ቢሆንም፣ ይህንን በሕይወታችን ለመለማመድ፣ የተለመደውን ደረጃ ለመተውና ወደ ከፍታ ለመውጣት መዘጋጀት አለብን።

ጋለሞታይቱ ባቢሎን ሁልጊዜም "ታላቂቱ ከተማ" (16÷19፣ ወዘተ) ናት፣ ታላቅነቷም የተመሠረተው በራሷ ሥራ ላይ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ኢየሩሳሌም "ቅድስቲቱ ከተማ" (21÷2፣ 10) ስትሆን፣ በዚህም ለእግዚአብሔር መለየቷ ነው ጕልቶ የሚታየው። እርሷም "ከእግዚአብሔር ዘንድ" ወጥታ "ለባልዋ" የተዘጋጀች ናት። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር ተሞልታለች። ይህ ለሁላችንም የልምምድ ጕዳይ ነው። በውስጣችን ያለው ቅድስና፣ የእግዚአብሔር የሆነና ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ የተለየ ማለት ነው። ከዚህ ሌላ ምንም ነገር ቅዱስ ስላልሆነ ከሰማይ የተጀመረ ነገር ብቻ ወደዚያው የመመለስን ሕግ ይከተላል። ይህ የቅድስና መርሕ ከተተወ፣ እኛ ራሳችን ወዲያውኑ በባቢሎን ውስጥ እንገኛለን።



ዮሐንስ ስለ ከተማዋ ሲዘረዝር መጀመሪያ የገለጸው ስለ ቅጥርዋ ነው። በእርግጥ ለእግዚአብሔር እንቅስቃሴ የተመቻቹ ደጆች ነበሩአት፤ ቅጥርዋ ግን ይቀድማል። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር መለየት ለክርስትና ሕይወት የመጀመሪያ መርሕ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር በዚያን ቀን ከተማዪቱን የሚፈልጋት ከነመጠኗና ከነክብሯ ከሆነ፣ በሰው ልብ ውስጥ ያንን ቅጥር አሁኑኑ መገንባት አለብን። ይህም በተግባር ሲገለጽ የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ እንደ ክቡርና ውድ ነገር ተንከባክበን እየጠበቅን፣ የባቢሎን የሆነውን ሁሉ መጥላትና መናቅ ማለት ነው። ይህን ስል በክርስቲያኖች መካከል መለያየት ይኑር ማለቴ አይደለም። በሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ባንተባበርም እንኳ ራሳቸውን ወንድሞቻችንን ለማግለል መድፈር አይኖርብንም። እንዲያውም ክርስቲያን ወገኖችን መውደድና መቀበል ይጠበቅብናል። ከዓለም በመለየታችን መርሕ ላይ ግን ማመቻመች የለብንም።

ነሕምያ በዘመኑ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ተሳክቶለት በድጋሚ ቢገነባም ብዙ ተቃውሞ ነበረበት። ምክንያቱም ሰይጣን ልዩ መሆንን ይጠላልና የሰዎችን ለእግዚአብሔር መለየት መታገሥ አይችልም። ለዚህም ነው፣ ነሕምያና ባልደረቦቹ ድንጋይን በድንጋይ ላይ ለመገንባት የጦር መሣሪያ በመታጠቅ ለጦርነት መዘጋጀት የነበረባቸው። ይህ ልንዘጋጅበት የሚገባ ለቅድስና የሚከፈል ዋጋ ነው።

እርግጥ ነው ቅጥር መገንባት አለብን። ዔድን ጠላት ወደ ውስጥ እንዳይገባ የሚከላከል ሰው ሠራሽ ቅጥር አልነበራትም። ስለ ዚህ ሰይጣን መግቢያ አገኘ። የእግዚአብሔር አሳብ ግን አዳምና ሔዋን ሰይጣን የሚሾልክበት የሞራል ክፍተት እንዳይኖር ማገጃ በማበጀት "እንዲጠብቋት" ነበር (ዘፍ. 2÷15)። ዛሬ እግዚአብሔር በተዋጁት ሕዝቦቹ ልብ ውስጥ፣ ሰይጣን የሞራል ክፍተት የማያገኝበት ዔድንን በክርስቶስ አቅዶአል። "ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር÷ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም"።

ለሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ልዩ መገለጥ እንደ ተሰጠው አብዛኞቻችን እንስማማለን። በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ለዮሐንስ ስለ ዓለም ባሕርይ ልዩ መረዳት እንደሰጠውም ይሰማናል። በእርግጥም *ኮስሞስ* በተለይ የዮሐንስ ቃል ነው። ሌሎቹ ወንጌሎች የተጠቀሙበት *ዐሥራ* አምስት ጊዜ (ማቴዎስ ዘጠኝ፣ ማርቆስ እና ሉቃስ እያንዳንዳቸው ሦስት ጊዜ) ብቻ ሲሆን ጳውሎስ ደግሞ በስምንት መልእክቶች ውስጥ አርባ ሰባት ጊዜ ጠቅሶታል። ዮሐንስ ግን በወንጌሉ ውስጥ ሰባ ዘጠኝ ጊዜ፣ በመልእክቶቹ

ውስጥ ሃያ አራቴና በተጨማሪም፣ በራእይ ውስጥ ሦስቴ - በአጠቃላይ 105 ጊዜ ተጠቅሞበታል።

ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ፣ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም "የሥጋ ምኞት፥ የዐይን አምሮት፥ የኑሮ ትምክሕት ከዓለም ነው እንጂ ከእግዚአብሔር አብ አይደለም" ብሎ ጽፎአል (2፥16 - የ1980 ትርጒም)። የሔዋንን ፈተና (ዘፍ. 3፥6) በግልጽ የሚያንጸባርቁትን እነዚህን ቃላት በመጠቀም የዓለምን ነገሮች ተንትኖልናል። በምኞት ወይም ባልተገራ ፍላጐት ሥር የሚመደቡ ነገሮች በሙሉ፣ ስግብግብ ምኞትን የሚያነሣሡ ነገሮች በሙሉ፣ በውስጣችን የሕይወትን ብርቅርቅነት ወይም ኩራት የሚያነሣሡ ነገሮች በሙሉ የሰይጣናዊ አሠራር ክፍሎች ናቸው። ምናልባት የመጀመሪያዎቹ ሁለቱን በጥልቀት ለመመልከት እዚህ መቆየት እምብዛም ባያስፈልገንም፣ እስቲ ሦስተኛውን ለትንሽ ጊዜ እንመልከት። በውስጣችን ኩራት የሚያነሣሣ ነገር በሙሉ የዓለም ነው። ለታዋቂነት፣ ለሀብትና ለስኬት ዓለም ያጨበጭባል። ሰዎችም በስኬት የሚመኩ ናቸው። ዮሐንስ ግን እንደዚህ ዐይነቱን የስኬት ስሜት የሚያመጡ ነገሮችን በሙሉ "የዓለም" ከሆኑ ነገሮች ጋር መድቦአቸዋል።

ስኬትን በተገናኘን ጊዜ ሁሉ የዓለምን አሠራር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ስለምንነካ፣ ከምንለማመደው ከእያንዳንዱ ስኬት በኋላ በፍጥነት ራሳችንን ዝቅ አድርገን በትሕትና የመናዘዝ ጥያቄ በውስጣችን ይመጣል። በአንዳንድ ስኬቶቻችን ምክንያት በራሳችን የመርካትና የሙሉነት ባሕርይ ሊሰማን ሲጀምር፣ ዓለምን እንደ ነካን በጥቂቱ ይታወቀን ይሆናል። ራሳችንን ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ማኖራችንንስ እናውቅ ይሆን? ምክንያቱም ዓለም በሙሉ ከፍርድ በታች እንደ ሆነ ተስማምተን የለ? ስለዚህ (ይህንን እውነታ ለመጨበጥ እንሞክር) ይህንን የተረዱና ጉድለታቸውን የሚናዘዙ ዋስትና አላቸው።

ችግሩ ግን፣ ስንቶቻችን ይህንን ዐውቀናል? በራሳችን የግል ቤት ተገልለን የምንኖር ሰዎችም እንኳ እንደ ስመጥርና ዝነኛ ሰዎች በኑሮ ትምክሕት ተጠልፈን ለመውደቅ የተጋለጥን ነን። በትንሽ ማዕድቤት ውስጥ ያለች ሴት፣ የዕለት ምግብ እያዘጋጀች ወይም እንግዶችን እያስተናገደች ሳለ ዓለምንና ዓለም የሚያመጣውን በራስ የመርካትና በራሴ ሙሉ ነኝ የማለት ስሜት ልትነካ ትችላለች። ለእግዚአብሔር ክብር የማይሆን ክብር ሁሉ ከንቱ ክብር ነው፣ አስገራሚው ደግሞ ዋጋ ቢስ ስኬት ከንቱ ክብር ሊያመጣ መቻሉ ነው። ትምክሕትን በምናገኝበት ስፍራ ዓለምን እናገኛለን። ስለዚህ ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ኅብረት ላይ ክፍተት ይፈጠራል። ስለዚህ የዓለምን ምንነት በግልጽ እንድናይ እግዚአብሔር ዐይናችንን ይክፈት



ልን! ክፉ ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ጥሩ መስለው ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር የሚያርቁን ነገሮችም የዚያ የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው አሠራር ክፍሎች ናቸው። ጥቂት ሥራ አከናውነን የምናገኘው እርካታ በእኛና በራሱ በእግዚአብሔር መካከል እስከ መግባት ድረስ ኀይል ያለው ነው። ምክንያቱም ውስጣችን የተሞላው በኑሮ አጉል ትምክሕት እንጂ በእግዚአብሔር ምስጋና ካልሆነ፣ ዓለምን እንደ ነካን በእርግጠኝነት እናውቃለንና ነው። ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የአምልኮ ሕይወት እንዳይደበዝዝብን ከፈለግን በቋሚነት ልንነቃና ልንጸልይ ያስፈልገናል።

ታዲያ ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥመድ ካዘጋጀው ከዚህ መንገድ ማምለጫው ምንድን ነው? በመጀመሪያ ማምለጫው ርቆ በመሮጥ እንዳልሆነ በአጽንኦት እንድነግራችሁ ፍቀዱልኝ። ብዙዎች ከዓለም ነገሮች በመታቀብ ዓለምን ማምለጥ እንደሚቻል ያስባሉ። ይህ ስሕተት ነው። ለመሆኑ ከራሱ ከዓለማዊ ዘዴዎች ትንሽ ብቻ የሚልቅ መንገድ ተጠቅመን ከዓለም አሠራር እንዴት ማምለጥ እንችላለን? እስቲ በማቴዎስ 11፥18-19 ያለውን ቃል ላስታውሳችሁ። "ዮሐንስ ሳይበላና ሳይጠጣ መጣ፥ እነርሱም፦ ጋኔን አለበት አሉት። የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፥ እነርሱም፦ እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኀጢአተኞች ወዳጅ ይሉታል"! አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ እዚህ ላይ ከዓለም የማምለጫውን ቀመር እንዳቀረበ ያስባሉ፣ ነገር ግን "አለመብላትና አለመጠጣት" ክርስትና አይደለም። ክርስቶስ እየበላና እየጠጣ መጣ፣ ይህም ክርስትና ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ "ዓለማዊ ትምህርት" ሲናገር፣ ይህንን "አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ" የሚል እንደ ሆነ ያስረዳል (ቈላ. 2፥20-21)። ስለዚህ መታቀብ ዓለማዊ ትምህርት ብቻ ስለ ሆነ፣ ይህንን ዓለማዊ ትምህርት በመጠቀም ከዓለም አሠራር ለማምለጥ ምን ተስፋ ይኖራል? ነገር ግን ከዓለም ነጻ ለመውጣት በማሰብ ሁሉንም ዐይነት ዓለማዊ ደስታዎችን የተዉ ቅን ክርስቲያኖች ስንትና ስንት ናቸው! አሁን ያላችሁበትን ስፍራ ትታችሁ ብትመንኑና እንደ ባህታዊ በዋሻ በመኖር ከዓለም ለማምለጥ ብታስቡ እንኳ፣ ዓለም እስካላችሁበት ድረስ ይከተላችኋል። የትም ብትደበቁ፣ ዱካችሁን በጥብቅ ተከታትሎ ያገኛችኋል።

ከዓለም ነጻ መውጣታችን የሚጀምረው ይህንን ወይም ያንን በመተው ሳይሆን፣ ይህን ምዕራፍ ስንጀምር "ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች!" (ራእይ 18፥2) ተብሎ በምሳሌነት የተጠቀሰውን የዓለምን ከሞት ፍርድ በታች መሆን እንደ እግዚአብሔር ዐይኖች በማየት ነው። አሁን የሞት ፍርድ በሞቱት ላይ ሳይሆን፣ በሕይወት

ባሉት ላይ ለሁልጊዜም ተላልፎአል። ዛሬ ዓለም የሚገብሩለትን ለማግኘት ያለ ማቋረጥ ፍለጋ የሚያካሂድና የሚከታተል ጠንካራ ኀይል ነው። በእርግጥ የሞት ፍርድ ሲፈረድ ፍርዱ የሚፈጸመው ገና ወደ ፊት ቢሆንም፣ ተፈጻሚነቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ሞት የተፈረደበትም ሰው ከታሰረበት ጠባብ የእስር ክፍል ባሻገር የሚታየው ተስፋ አይኖርም። ዓለምም ከፍርድ በታች በመሆኑ ተስፋ የለውም። የዓለም አሠራር እስካሁን ፍርድ ባይፈጸምበትና እግዚአብሔር ባያስወግደውም፣ የፍርዱ መፈጸም ያለቀለት ጉዳይ ነው። ይህንን መረዳታችን ለእኛ ልዩነት ያመጣል። አንዳንዶች በምናኔና እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ባለመብላትና ባለመጠጣት ከዓለም ነጻ መውጣትን ይፈልጋሉ። ይህ ቡዲዝም እንጂ ክርስትና አይደለም። እኛም እንደ ክርስቲያን እንበላለን እንጠጣለን፣ ይህን ስናደርግም መብላትና መጠጣት የዓለም መሆናቸውን አብረውም ከፍርድ በታች እንደ ሆኑ ተገንዝበን በመሆኑ፣ በተጽዕኗቸው ሥር ሊያውሉን አይችሉም።

እስቲ ለምሳሌ የከተማችሁ ማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣናት እናንተ የተቀጠራችሁበት ትምህርት ቤት እንዲዘጋ አዘዙ እንበል። ልክ ይህንን ዜና ስትሰሙ በዚያ ትምህርት ቤት የወደፊት ዕድል ፈንታ እንደሌላችሁ ታውቃላችሁ። ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ሥራችሁን ብትቀጥሉም፤ ለወደፊት የሚሆን ነገር በዚያ አታቅዱም። ልክ ትምህርት ቤቱ መዘጋት እንዳለበት በሰማችሁበት ቅጽበት ለትምህርት ቤቱ ያላችሁ አመለካከት ይለወጣል። ወይም ሌላ ምሳሌ ለመጠቀም፣ መንግሥት አንድ የሆነ ባንክን ለመዝጋት ወሰነ እንበል። ታዲያ እናንተ ባንኩን ከወደቀበት ለማዳን ብዙ ገንዘብ ወደ ባንኩ ለማስገባት ትጣደፋላችሁ? በፍጹም፣ ባንኩ ወደ ፊት እንደማይቀጥል ከሰማችሁ ጀምሮ አንዲትም ሳንቲም ወደ ባንኩ ይዛችሁ አትሄዱም። ከእርሱ ምንም ስለማትጠብቁ፣ ምንም አታስቀምጡም።

ዓለምም እንዲዘጋ ታውጆበታል ልንል እንችላለን። ባቢሎን፣ ታጋዮቿ ከበጉ ጋር ጦርነት ሲገጥሙና የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ የሆነው እርሱ በሞቱና በትንሣኤው ድል ሲነሣቸው ወድቃለች (ራእይ 17፥14)። ስለዚህ ምንም ተስፋ የላትም።

የክርስቶስ መስቀል መገለጥ፣ የዓለም የሆነው ነገር ሁሉ በመስቀሉ ኀይል ከሞት ብይን በታች የመሆኑን እውነታ ወደ መረዳት ያመጣናል። አሁንም በዓለም ውስጥ መኖራችንና የዓለምን ነገሮች መጠቀማችን ቢቀጥልም፣ በእነርሱ ውስጥ ያለንን ተስፋ መስቀሉ ሰባብሮልናልና ተስፋ አንጥልባቸውም። እውነቱን ለመናገር፣ የጌታ ኢየሱስ መስቀል በዓለም ውስጥ ያለንን ዕድልና ተስፋ አፈራርሶታል። ስለዚህ በዚያ ልንኖርለት የሚገባ ነገር የለም።



ከእንደዚህ ዐይነት መገለጥ የማይጀምር ከዚህ ዓለም የመዳኛ እውነተኛ መንገድ የለም። ከዓለም ርቀን በመሮጥ ከዓለም ለማምለጥ መሞከር የሚያስፈልገን፣ ዓለምን ምን ያህል እንደምንወድና ዓለምም ምን ያህል እንደሚወደን ለመረዳት ብቻ ነው። ምናልባት ለመራቅ ወደምንችልበት ቦታ እንሮጥ ይሆናል፤ ዓለም ግን በእርግጥ እነፍንፎ ይደርስብናል። ዓለም እንደ ተፈረደበት ሲገባን ግን ለዓለም የነበረን ጉጉት ስለሚከስም ዓለምም በእኛ ላይ ያለውን ይዞታ ያጣል። ይህንን መረዳት ማለት በጠቅላላው ከሰይጣን ኢኮኖሚ ጋር የነበረንን ትስስር በፍጥነት ማቋረጥ ማለት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ ማጠቃለያ ላይ ይህንን በግልጽ አስቀምጦታል። “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ” (6፥14)። ስለዚህ ክፍል ምን አስገራሚ ነገር ተረዳችሁ? ይህ ክፍል የሚናገረው ባለፈው ምዕራፋችን ዓለምን በሚመለከት አስቀድመን የጠቆምነውን የመስቀሉ ሥራ ሁለት ገጽታዎች ነው። “እኔ ለዓለም ተሰቅያለሁ” የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ ሮሜ ምዕራፍ 6 ን በመሳሰሉ ምንባቦች ላይ የተነገረውን ከክርስቶስ ጋር የመሰቀላችንን እውነታ ከመረዳታችን ጋር በትክክል የሚገጥም ሆኖ እናገኘዋለን። እዚህ ላይ ግን በተለይ “ዓለም ለእኔ ተሰቅሎአል” ይላል። እግዚአብሔር በክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ መገለጥ ወደ እኔና ወደ እናንተ ሲመጣ፣ የእኛን በዚያ በመስቀሉ ላይ መሆን ብቻ አይደለም ያሳየን። ዓለማችንም በዚያ በመስቀሉ ላይ መሆኑን ጭምር አሳይቶናል። እኔና እናንተ የመስቀሉን ፍርድ ካላመለጥን ዓለምም የመስቀሉን ፍርድ ማምለጥ አይችልም። ጥያቄው ይህ ነው። ይህ ከገባኝ የምወደውን ዓለም በራሴ ለመካድ አልሞክርም፣ መስቀሉ እንደ ካደው አያለሁ። የተጣበቀብኝን ዓለም ለማምለጥም አልሞክርም፤ በመስቀሉ እንዳመለጥኩት አያለሁ።

ልክ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ እንደሚያጋጥመን ሌሎች ነገሮች ሁሉ ከዓለም ነጻ የምንወጣበትም መንገድ ከሰው ተፈጥሯዊ አመለካከት እንግዳ መሆኑ ለብዙዎቻችን አስደናቂ ነው። ሰው አደጋ እንዳለበት ከሚገምተው አካባቢ በመራቅ የዓለምን ችግር ለመፍታት ይፈልጋል። ነገር ግን አካላዊ መራራቅ መንፈሳዊ መራራቅን እንደማያመጣ ሁሉ፣ ተቃራኒውም እውነት ነው፤ ከዓለም ጋር አካላዊ ንክኪ መፍጠር የግድ ለዓለም መንፈሳዊ ምርኮኛነት አያበቃም። የዓለም መንፈሳዊ ምርኮኛ መሆን የመንፈሳዊ ዕውርነት ፍሬ ሲሆን፣ ነጻ መውጣቱ ደግሞ የዐይኖቻችን መከፈት ውጤት ነው። ከዓለም ጋር ምንም ያህል የጠበቀ ውጫዊ ንክኪ ቢኖረን፣ ስለ ዓለም ባሕርይ

ትክክለኛ መረዳት ስናገኝ ዓለም በእኛ ላይ ከነበረው ኀይል እንላቀቃለን። የዓለም መሠረታዊ ባሕርይ ሰይጣናዊ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላትነት ነው። ይህን በመረዳትም ነጻ መውጣት ይገኛል።

አንድ ነገር ልጠይቃችሁ? ሥራችሁ ምንድን ነው? ነጋዴ? ሐኪም? ከእነዚህ ጥሪዎች አትሽሹ። ይልቅ ንግድ ከሞት ፍርድ በታች መሆኑን ጸፉ። ሕክምናንም እንዲሁ። ያንን በእውነት ካደረጋችሁ ከዚህ በኋላ የተለወጠ ሕይወት ይሆንላችኋል። በዚህም፣ በእግዚአብሔር ጠላትነቱ ከፍርድ በታች በሆነው ዓለም መካከል እግዚአብሔርን እንደሚወድና እንደሚፈራ ሰው መኖር ማለት ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ።



# ምዕራፍ አምስት

## ልዩ መሆን

አሁን ትኩረታችሁን ኢየሱስ በዮሐንስ 8፥23 ላይ ለአይሁዳውያን ወደ ተናገረው ቃል እንድታደርጉ እጋብዛችኋለሁ። "እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም"። እዚህ ላይ "ከ ..." በማለት የሚጀምሩትን ቃላት አጠቃቀም ልብ እንድትሉ እመኛለሁ። ይህ የግሪኩ ቃል ኤክ *(ek)* በተለይ "መውጣት" የሚል ትርጉም ሲኖረው፣ መነሻን - መሠረትን (ምንጭን) ያመለክታል። ኤክ ቶ ኮስሞስ *(ek tou kosmos)* የሚለው አገላለጽ "ከዚህ ዓለም መውጣት" ን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ የዚህ ምንባብ አሳብ "እናንተ የተገኛችሁት ከታች ነው፣ እኔ የተገኘሁበት ምንጭ ከላይ ነው። እናንተ የወጣችሁት ከዚህ ዓለም ነው፣ የእኔ መሠረት (መገኛ) ግን ከዚህ ዓለም አይደለም" የሚል ነው። ጥያቄው፣ እናንተ ጥሩ ወይስ መጥፎ ሰዎች ናችሁ? የሚል ሳይሆን፣ መሠረታችሁ ከየት ነው? የሚል ይሆናል። ስለዚህም ያ ነገር ከየት ነው የተገኘው? ብለን እንጂ፣ ያ ነገር ጥሩ ነውን? ወይም፣ ያ ነገር ስሕተት ይሆን? ብለን እንጠይቅም። ሁሉም ነገር የተገኘበት ምንጭ ይወስነዋል። "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው" (ዮሐ. 3፥6)።

ስለዚህ ኢየሱስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ ያንኑ የግሪክ መስተዋድድ በመጠቀም፣ "ከዓለምስ ብትሆኑ (*ኤክ ቶው ኮስሞስ*) ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ፥ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል" ሊላቸው ይችላል (ዮሐ. 15፥19)። እዚህም "ከዓለም ስለ አይደላችሁ" የሚል ተመሳሳይ አገላለጽ ከማግኘታችን በተጨማሪ "እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ" የሚል ሌላ ጠንከር ያለ አገላለጽም እናገኛለን። ይህ የኋለኛው አባባል በጥንድ አጽንኦት የሚሰጠው ጉዳይ አለ። በውስጡ እንደ በፊቱ ኤክ *(ek)* "መውጣት" ሲኖር፣ ከዚህ በተጨማሪም "መምረጥ" የሚለው ግስ - ኤክ ሌጎ *(ek lego)* ራሱ ሌላ ኤክ ይዟል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን "ከዓለም እንድትወጡ፣ ተጠርታችሁ የወጣችሁ" ናችሁ ነው የሚላቸው።

በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ድርብ ኤክ አለ። *ኮስሞስ* ተብሎ ከሚጠራው ትልቅ ሥርዐት ውጭ፣ የእርሱም ከሆኑት፣ በውስ

ጡም ከሚሳተፉት በጣም በርካታ ግለሰቦች ውጭ፣ ከእነዚህ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ነጻ ተን፣ ተለይተን እንድንወጣ እግዚአብሔር ጠርቶናል። ከዚህም "ቤተ ክርስቲያን" - *ኤክሌሽያ* (ekklesia)፣ በእግዚአብሔር "ተጠርተው የወጡ" የሚለው ማዕረግ ይገኛል። እግዚአብሔር ከትልቁ *ኮስሞስ* መካከል አንዱን ከዚህና አንዱን ከዚያ ይጠራል፣ የጠራቸውንም በሙሉ ደግሞ ጠርቶ ያወጣቸዋል። ከዚህ ዓለም ጠርቶ "የማያወጣ" የእግዚአብሔር ጥሪ ብሎ ነገር የለም። ቤተ ክርስቲያን *ኤክሌሽያ* ናት። በመለኮታዊ አሳብ መሠረት፣ *ኤክ* (ek) የጐደለው *ክሌሽያ* (klesia) ሊኖር አይችልም።

የተጠራችሁ ከሆናችሁ ተጠርታችሁ የወጣችሁ ናችሁ ማለት ነው። እግዚአብሔር ጠርቷችሁ ከሆነ፣ የጠራችሁ ከዓለም ሥርዐት ውጭ በመንፈስ እንድትኖሩ ነው። አስቀድመን ምንም ማምለጫ ባል ነበረው ሰይጣናዊ ሥርዐት ውስጥ ነበርን፣ ነገር ግን ተጠራን፣ ያ ጥሪ ደግሞ አወጣን። በእርግጥ ይህ አሉታዊ ጐኑ ቢሆንም ለመዋቅራችን አዎንታዊ ጐንም አለው። ምክንያቱም እኛ ለራሳችን ካለን ዕይታ አንጻር ትርጉም የሚሰጡ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን ሁለት ማዕረጐች አሉን። ያለፈው ታሪካችንን የኋሊት ስንመለከት *ኤክሌሽያ* - ቤተ ክርስቲያን ነን፣ አሁን በእግዚአብሔር ውስጥ ያለንን ሕይወት ስንመለከት ግን የክርስቶስ አካል፣ በምድር የምንገኝ በሰማይ ያለው የእርሱ ነጸብራቆች ነን። እግዚአብሔር እኛን ከመረጠበት ማዕዘን ስናየው፣ ከዓለም "የወጣን" ነን፣ ከአዲሱ ሕይወታችን አኳያ ሲታይ ግን በፍጹም ከዓለም አልነበርንም፤ ከላይ እንጂ። በአንድ በኩል፣ የተመረጥን፣ የተጠራንና ከዓለም ሥርዐት ነጻ የወጣን ሕዝብ ነን። በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈስ ከላይ በመወለዳችን ከዚያ ሥርዐት ጋር ግንኙነት የሌለን፣ ዳግመኛ የተወለድን ሕዝብ ነን። ስለዚህም ዮሐንስ ያየው፣ ቅድስቲቱ ከተማ "ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ" ነው (ራእይ 21፥10)። እንደ እግዚአብሔር ሕዝብነታችን ሰማይ መሄጃችን (ዕጣችን) ብቻ ሳትሆን፣ *መሠረታችን (ምንጫችን)* ናት።

በመሠረቱ ከሌላ-ዓለም የሆነ ነገር በእኔና በእናንተ ውስጥ መገኘቱ ራሱ ያስደንቃል። ይህኛው ዓለም የፈለገውንም ያህል ቢያድግ እንኳ ያኛውን ለመምሰል አንድ እርምጃ እንኳ መራመድ እስከ ማይችል ድረስ፣ በውስጣችን ያለው በእርግጥም ከሌላ-ዓለም የሆነ ነገር ነው። በእግዚአብሔር ስጦታ ያገኘነው ሕይወት፣ ከሰማይ የመጣና ፈጽሞ በዓለም ያልነበረ ነው። ከዚህም ዓለም ጋር ምንም መጣጣም የለውም፤ ከሰማይ ጋር ግን ፍጹም ይስማማል። ስለሆነም በየዕለቱ ከዚህ ዓለም ጋር መዳበል ቢኖርብንም እንኳ ልክ በቤታችን ያለን ይመስል እንድንደላደል አይፈቅድልንም።



እስቲ ይህን መለኮታዊ ስጦታ - ዳግም በተወለደ ሰው ልብ ውስጥ የሚኖረውን የክርስቶስ ሕይወት ለአፍታ እናስበው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ብዙ የሚናገረው አለው። በልዩ መገለጥ በተሞላው የ1 ቆሮንቶስ መጽሐፍ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት የሚያስደንቁ ዐረፍተ ነገሮችን ጽፎአል። (ሀ) ራሱ እግዚአብሔር በክርስቶስ (ውስጥ) እንዳደረገን፣ እና (ለ) "እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ጥበባችን፥ ጽድቃችን፣ ቅድስናችን፥ ቤዛችን እንዲሆን" እንዳደረገው (1፥30 - የ1980 ትርጉም)። እነዚህ እግዚአብሔር በልጁ የፈጸማቸው ጠቅላላውን የሰውን ልጅ ጉድለቶች ስፋት የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው። እግዚአብሔር እነዚህን የጽድቅ፣ የቅድስናና ሌሎች ብቃቶች "እንደ ፍላጐታችን" እንደማያድለን ቀደም ሲል በሌላ ስፍራ[1] አይተናል። እርሱ የሚያደርገው ክርስቶስን ለሁሉም ጉድለቶቻችን ምላሽ አድርጎ መስጠት ነው። እርሱ እኔን በተሰቀለውና በተነሣው ክርስቶስ ውስጥ አስቀድሞ ስላኖረኝ፣ ልጁን ጽድቄ፣ ቅድስናዬና ሌላ የሚጐድለኝን ነገር ሁሉ እንዲሆን ያደርገዋል።

አሁን ትኩረታችሁን "ቤዛችን" ወደሚለው የመጨረሻ ቃል እንድታደርጉ እጠይቃለሁ። ምክንያቱም ቤዛነት ከዓለም ጋር ብዙ የሚያያዝ ነገር አለው። እስራኤላውያን፣ በዚያን ጊዜ የሚያውቁት ጠቅላላ ዓለም ከነበረችውና ለእኛ ደግሞ በሰይጣናዊ አመራር ሥር ላለው ዓለም ምሳሌ ከምትሆነን፣ ከግብፅ "የተቤዡ" ናቸው። "እኔ እግዚአብሔር ነኝ" አለ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን፣ "በተዘረጋች ክንድ ... እቤዣችኋለሁ" (ዘፀ. 6፥6 - አ.መ.ት)። ስለዚህ በእነርሱና በሚያሳድዳቸው የፈርኦን ሰራዊት መካከል ማገጃ በማድረግና ፍርድን በመፈጸም አወጣቸው። በዚህም ሙሴ "የተቤዠሃቸውን ሕዝብህን" ብሎ ስለ እስራኤላውያን መዘመር ቻለ (15፥13)።

በዚህ ብርሃን እስቲ የጳውሎስን ጥምር ዐረፍተ ነገር እንመልከት። (ሀ) *እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ አድርጎናል*፣ ስለዚህ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም አይደለምና እኛም ከዚህ ዓለም አይደለንም። እርሱ የእኛ ከባቢ ሲሆን፣ በእርሱ ውስጥ በመሆናችንም በዙሪያችን ካለው ከሌላኛው ከበባ ውጭ ነን ማለት ነው። እግዚአብሔር አብ "ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ *ቤዛነቱንም እርሱንም የኀጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት* ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን" (ቈላ.1፥13-14)። ይህንንም ፍልሰት ባለፉት ምዕራፎች ተመልክተነዋል።

በተጨማሪም (ለ) *ክርስቶስ "ቤዛችን" ከተደረገልን* - ቤዛ እንዲሆነን ከተሰጠን፣ እግዚአብሔር ራሱን ክርስቶስን *በውስጣችን ዓለ*

1 - ክርስትና እንዲህ ነው! ገጽ 99

ምን የምንቋቋምበት ማገኛ እንዲሆነን አድርጎታል ማለት ነው። ዓለ
ማዊ ያልሆነ ኑሮን በመኖር፣ በአንድና በሌላ መንገድ ዓለምን ለመቋ
ቋም የሚሞክሩ ብዙ ወጣት ክርስቲያኖች አጋጥመውኛል። ይህም
ከባድ ሆኖባቸዋል፤ ደግሞም እንዲህ ዐይነቱ ጥረት አስፈላጊ አይደ
ለም። ምክንያቱም ክርስቶስ በራሱ መሠረታዊ "ሌላነት" ከዓለም
የምንከለልበት በመሆኑ፣ ከዚህ በላይ ምንም አያስፈልገንም። እስራኤ
ላውያን መቤዠታቸውን በሚመለከት ያደረጉት ነገር እንዳልነበር፣
እኛም ከመቤዠታችን ጋር በተገናኘ ምንም የምናደርገው ነገር አይኖ
ርም። እነርሱ የምትቤዣቸውንና ስለ እነርሱ የተዘረጋችውን የእግዚአብ
ሔር ክንድ ታምነዋል። ለእኛ ደግሞ ክርስቶስ ቤዛችን ሆኖአል። ስለ
ዚህ በእኔና በዓለም መካከል እግዚአብሔር በልቤ ያስቀመጠው ማገኛ
- የራሱ የጌታ የሆነ ሌላ ዐይነት ሕይወት አለ። እናም በክርስቶስ
ምክንያት ዓለም ሊደርስብኝ አይችልም።

ታዲያ የነገሮችን አሠራር ለመቋቋም ወይም ለማምለጥ
መሞከር ለምን ያስፈልገኛል? ዓለምን የማሸንፍበትን ነገር ለማግኘት
ወደ ውስጤ ብመለከት፣ ወዲያውኑ በውስጤ ያለው እያንዳንዱ ነገር
ለዚያ ዓለም ሲጮኽ አገኘዋለሁ፣ ራሴን ከዓለም ለማላቀቅ ስታገል
ደግሞ በቀላሉ ይበልጥ ገብቼበት ዐርፋለሁ። ነገር ግን ክርስቶስ
በውስጤ መቤዠቴ መሆኑን፣ በጠቅላላም "የወጣሁት" በእርሱ መሆ
ኑን የምገነዘብበት ያ ቀን ይምጣ። ያ ቀን የትግል መጨረሻ የሚታይ
በት ነው። ይህንን የ "ዓለም" ጉዳይ በሚመለከት ምንም ማድረግ
እንደማልችል በቀላሉ እነግረዋለሁ፣ ነገር ግን መቤዠት ስለ ሆነኝ
በሙሉ ልቤ አመሰግነዋለሁ።

ብትሰለቹኝም አንድ ጊዜ ልድገመው። የዓለም ባሕርይ ከእግዚ
አብሔር ከተቀበልነው በመንፈስ-የተሞላ ሕይወት ጋር ሞራላዊ ልዩ
ነት አለው። በመሠረቱ ዓለም የሚጠላን ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ
የሆነው አዲስ ሕይወት ስላለን ነው እንጂ፣ የራሱ የሆኑትን አይጠላ
ቸውም። ይህ መሠረታዊ ልዩነት በእርግጥም ዓለም እኛን እንዲወደን
የምናደርግበት ምንም መንገድ አልተወልንም። "ከዓለምስ ብትሆኑ
ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋ
ችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል"(ዮሐ.
15፥19)።

ዓለም ተፈጥሯዊውን የሰው ታማኝነትና ጨዋነት በውስጣችን
ሲያገኝ፣ ሊያደንቀንና አክብሮት ሰጥቶ በአስተማማኝ ስፍራ ሊያኖረን
የተዘጋጀ ነው። ከራሳችን ያልሆነ ነገር - ተከፋዮች የሆንበትን መለኮ
ታዊ ሕይወት በውስጣችን ሲያገኝ ግን ጥላቻው ይቀሰቀሳል። የክርስ
ትናን ፍሬ ለዓለም አሳዩት፣ ያጨበጭባል፤ ክርስትናን ስታሳዩት ግን



በብርቱ ይቃወማል። ምክንያቱም ዓለም የሚፈልገውን ያህል እንዲያ
ድግ ብትፈቅዱለት እንኳ አንድ ክርስቲያን እንኳ ማፍራት አይች
ልም። ክርስቲያናዊ ታማኝነትን፣ ክርስቲያናዊ ትሕትናን፣ ክርስቲያናዊ
ልግስናን አም፣ ሊያስመስል ይችላል፤ አንድን ክርስቲያን ለማስገኘት
ግን ፈጽሞ አይመኝም። ክርስቲያናዊ ሥልጣኔ የሚባለው ግን ከዓለም
ተቀባይነትንና አክብሮትን አግኝቶአል። ዓለም ይህንን ሊታገሥ፣
እንዲያውም ከራሱ ጋር ቀላቅሉ ሊጠቀምበት ይችላል። የክርስትና
ሕይወትን - በክርስቲያኑ አማኝ ውስጥ ያለውን የክርስቶስ ሕይወት
ግን ይጠላዋል፣ በሚያገኘው ስፍራም ሁሉ እስከ ሞት ድረስ በጽናት
ይቃወመዋል።

ክርስቲያናዊ ሥልጣኔ ዓለምንና ክርስቶስን የማስታረቅ
ሙከራ ውጤት ነው። ይህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሉጥ በሰዶም የነበ
ረው ተሳትፎና ማመቻመች ውጤት በሆኑት ሞአብና አሞን ይመ
ስላል። ሞአብም ሆነ አሞን ለእስራኤል የነበራቸው ጠላትነት ከሌሎች
የአሕዛብ መንግሥታት ያነሰ እንዳልነበረ ታይቶአል። ክርስቲያናዊ
ሥልጣኔም ከዓለም ጋር ሊቀላቀል እንደሚችል፣ እንዲያውም በችግር
ጊዜ ከዓለም ጐን ሲሆን እንደሚገኝ ተረጋግጦአል። ለዘለዓለም ከዓ
ለም የራቀ እና ሊቀላቀል የማይችል አንድ ነገር አለ፣ እርሱም
የክርስቶስ ሕይወት ነው። በባሕርያቸውም አንዱ ለአንዱ ባላንጣና
ሊታረቁ የማይችሉ ናቸው። ዓለም ሊያፈራው በሚችለው የመጨረሻ
ምርጥ ውጤትና እዚህ ግባ በማይባል ክርስቲያን መካከል ምንም
የጋራ ነገር ስለሌለ ማነጻጸሪያ መሠረት አይኖረንም። ምክንያቱም
ተፈጥሯዊ ደግነት፣ ስንወለድ በተፈጥሮ ያገኘነውና በራሳችን ምንጮች
በተፈጥሮ የሚጐለብት ሲሆን፣ መንፈሳዊ ደግነት (መልካምነት) ግን
ዮሐንስ እንደሚለው "ከእግዚአብሔር የተወለደ" ነው (1ዮሐ. 5፥4)።

እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ሁሉን አቀፍ ቤተ ክርስቲያን
መሥርቶአል፣ በተለያዩ ስፍራዎች ደግሞ በርካታ አጥቢያ አብያተ
ክርስቲያናትን ተክሎአል። እግዚአብሔር ይህን አድርጓልና እርሱ
ያዘጋጀው ከዓለም ነጻ የመውጫ መንገድ ከዓለም ጋር አካላዊ ንክኪ
እንዳይኖር መራቅ ነው ብሎ መጠበቅ ተገቢ አይደለም። በውጤቱ
ግን ብዙ ልባዊ ክርስቲያኖች በመገለል ችግር እጅግ ተደናግረዋል።
እግዚአብሔር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን እዚህ ከመሠረተ፣ የተመ
ሠረተው አንድ ቀን ምናልባት እንደገና በዓለም ይዋጥ ይሆን? ብለው
ይጠይቃሉ።

በእርግጥ ያ ለሕያው እግዚአብሔር የሚያመጣው ችግር
የለም። መሠረቱ ከዓለም እንዳልሆነ ሁሉ፣ በዓለም በኩል ምንም
ይሁን ምን፣ ከዓለም ጋር የመመሳሰል ፍላጐት በእግዚአብሔር ቤት

አስቀድመን እንዳየነው፣ መታቀብ - “አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ” (ቈላ. 2፥21) የዓለም የአሠራር አንድ ክፍል በመሆኑ፣ እርሱ ራሱ የሚጠረጠር ነው። እናም ከዚህ አለፍ ማለት አለብን፣ በዚያ ጉዳይ ላይ ደግሞ አሁንም ሐዋርያው ጳውሎስ የሚረዳን ነገር ይናራል። የክርስትና ሕይወት አድርጉና አታድርጉ ከሚለው ክርክር የራቀ መሆኑን በሮሜ 14፥17 ላይ ያሳየናል። “የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም” - ማለትም ሙሉ በሙሉ ከተለየ ክልል ውስጥ ስለ ሆነች በእነዚህ ጉዳዮች ልትገመት - ልትታሰብ አይገባም። የክርስቲያን ሕይወት መመራት ያለበት፣ ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ በሚሰጠው ውስጣዊ ችሎታ እንጂ ከሰዎች ጋር መቀላቀል የሚኖርበት እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ በሚገልጹ ሕጎች መሆን የለበትም።

“ጽድቅና ሰላም፣ በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ” - ትኩረታችንን ለጊዜው ከእነዚህ መካከል በሁለተኛው ላይ ብናደርግ መልካም ይሆናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ እኛን ከክፉ ይጠብቀን ዘንድ ልጁ ለጸለየው ጸሎት (ዮሐ. 17፥15) በሚሰጠው ምላሽ ውስጥ ሰላም ጉልህ ስፍራ እንዳለው እንረዳለንና ነው።

ሊነገር በማይቻል ፍልሚያና ተቃርኖ መካከል ሳይረበሽና ሳይናወጥ የሚጠብቀው ሰላም - ፍጹም ጥብቅ የሆነ የመንፈስ መረጋጋት በራሱ በእግዚአብሔር ውስጥ አለ። “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ” ያለው ኢየሱስ፣ ነገር ግን “በእኔ ሳላችሁ ሰላም” አላችሁ ብሎ በዚያው ቍጥር መጀመሪያ ላይ ተናግሮአል (ዮሐ. 16፥33)። እኛ አንድ የሆነ ነገር ሲበላሽብን እንዴት ነው ፈጥነን የምንናወጠው! ነገር ግን እግዚአብሔር ልቡን ባኖረበት ትልቅ ዕቅዱ ላይ ያጋጠመውን ብልሽት ለመረዳት ቆም ብለን እናውቃለን? ብርሃን የሆነው እግዚአብሔር ዘላለማዊ ንድፍ ነበረው። በጨለማ ውስጥ ብርሃን እንዲያንጸባርቅ በማድረግ ይህ ዓለም የዕቅዱ መተግበሪያ ስፍራ እንዲሆን መደበ። ነገር ግን ሁላችንም እንደምናውቀው፣ እግዚአብሔርን ለማሰናከል ሰይጣን ጥልቅ አለ፣ ስለዚህ ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የሚወዱ ሆኑ። በዚህ እንቅፋት መካከል ግን፣ እግዚአብሔር አንድ ምታውን ብዙም የማናደንቀውን ፍጹም የመረጋጋት ሰላም በውስጡ ጠብቆአል። ይህንን የእግዚአብሔር ሰላም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ልባችንንና አሳባችንን በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚጠብቅ የሚነግረን (ፊልጵ. 4፥7)።

“መጠበቅ” ሲል ምን ማለት ነው? መጠበቅ ማለት ጠላቴ ወደ እኔ ለመድረስ አስቀድሞ በደጅ ላይ ካሉት የታጠቁ ጠባቂዎች ጋር መዋጋት አለበት ማለት ነው። እኔ ከመነካቴ በፊት፣ ጠባቂዎቹ



ራሳቸው መሸነፍ አለባቸው። ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚጠብቀው ሰላም እኔንም ስለሚጠብቀኝ እንደ እግዚአብሔር በሰላም የተሞላሁ ለመሆን እደፍራለሁ። ይህ ዓለም የማያውቀው ነገር ነው። “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፣ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም” (ዮሐ. 14፥27)።

ሰዎች ግን ኢየሱስን ከመረዳት ወድቀዋል! በውስጣቸው የነበረው ብርሃን ጨለማ ስለ ነበር፣ እርሱ የሚያደርገው ሁሉ በዐይኖቻቸው ፊት ስሕተት ሆነባቸው። እንዲያውም በውስጡ ያለውን መንፈስ፣ የአጋንንት አለቃ የሆነው ብዔል ዜቡልን እርገው እስከ መቍጠር ደፍረዋል። እርሱ ግን በበላተኝነትና በጠጪነት ሲከሱት በምላሹ “አባት ሆይ ... አመሰግንሃለሁ!” (ማቴ. 11፥19፣ 25) አለ እንጂ አልተናወጠም። ምክንያቱም በመንፈስ በእግዚአብሔር ሰላም ውስጥ ይኖር ነበር።

ወይም ከፋሲካው በፊት የነበረውን የመጨረሻ ሌሊት አስታውሱ። በዚያ ምሽት ሁሉ ነገር እየተበላሸ ያለ ይመስል ነበር - አንድ ወዳጁ አሳልፎ ሊሰጠው ከድቶ በምሽት ወጣ፣ ሌላኛው በቍጣ ሰይፉን መዘዘ፣ የቀሩት ወደ መሸሸጊያቸው ሄዱ፣ ወይም ለማምለጥ በመጓጓት ራቁታቸውን ሳይቀር ሮጡ። በዚህ ሁሉ መካከል ግን ኢየሱስ፣ ሊወስዱት የመጡት ሰዎች ከእርሱ ይልቅ ተደናግጠው በማፈግፈግ ወደ ኋላቸው እስኪወድቁ ድረስ በመረጋጋት፣ “እኔ ነኝ” ሲላቸው፣ በሰላም ተሞልቶ ነበር። ይህም ልምምድ በእያንዳንዱ ዘመን በነበሩ ሰማዕታት ሲደጋገም ኖሮአል። ሲሠቃዩና ሲቃጠሉ እንኳ ውስጣቸው የእርሱን ሰላም የተሞላ ስለ ነበር፣ ተመልካቾቹ በክብራቸውና በእርጋታቸው እስከ መደነቅ ይደርሱ ነበር። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ ሰላም ከመታወቅ የሚያልፍ መሆኑን ቢናገር አያስደንቅም።

ኢየሱስ፣ “በዓለም” ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፣ “በእኔ” ውስጥ ደግሞ ሰላም ታገኛላችሁ እያለ፣ እንዴት ከባድ ንጽጽር ነው ያስቀመጠው! በግፊቱና በሙግቱ እንድንታፈግ እግዚአብሔር ከእነዚህ ከሁለቱ በአንደኛው ውስጥ ሲያስቀምጠን፣ በዚህ ሁሉ መካከል ደግሞ ያለ መናወጥ መቆም እንድንችል በሌላኛውም ውስጥ እኖርናል። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ራሱ “የዳሰሰኝ ማነው?” ብሎ እንደ ጠየቀ ሁላችንም እናስታውሳለን። በዚያ የቅፍርናሆም ግርግርና ግፊያ መካከል በእምነት የተነካውን መነካት ያስታውሳል። ይህ መነካት ከሩኅሩኅ ልቡ ጋር ተመጣጣኝ የነበረ ሲሆን፣ የሌሎቹ መተራመስ በእርሱ ላይ የሚፈጥረው ግፊት ግን የዚህ ዐይነት ውጤት አላመጣም። እርሱና እነርሱ የሚጋሩት ነገር ኢምንት ስለ ነበር፣ ትዕግሥት አልባ ግፊአቸው ትንሽ እንኳን አልተሰማውም። “እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ

አይደለም"። ሕይወታችን ተራ የሰው ሕይወት ከሆነ፣ በዓለም እንወዘወዛለን። የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ከሆነ ግን በዓለማዊ ግፊቶች አይናወጥም።

"ጽድቅ፣ ሰላምና ደስታ" - የእግዚአብሔር መንግሥት ከእነዚህ ነገሮች ጋር የሚያያዝ ነው። እኛንም የሚያሳስበን ሌላኛው ዓለም እንጂ እነዚህን ነገሮች የማድረግና ያለማድረግ፣ ፈቃድም ሆነ ክልከላው ስላልሆነ፣ ወደ እርጌው የ "መብልና የመጠጥ" ክልል ተስበን መግባት የለብንም። ስለዚህ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለነው መታቀብ አያስፈልገንም። ዓለምን ያሸነፍነው የዓለምን ነገሮች በመተው ሳይሆን፣ በአዎንታዊ መንገድ - በሌላኛው ዓለም ውስጥ በመሆን - ዓለም ሊሰጠው በማይችለውና ሰዎች በጣም በሚያስፈልጋቸው ፍቅር፣ ደስታ እና ሰላም በመሞላት ነው።

ዓለምን ለማስወገድ ከመፈለግ ይልቅ፣ እግዚአብሔር በዚያ ስላስቀመጠን ምን ያህል ዕድለኛ እንደ ሆንን ማየት ያስፈልገናል። "ወደ ዓለም እንደ ላከኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላከኋቸው" (ዮሐ. 17÷18)። ምን ዐይነት ዐረፍተ ነገር ነው! ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ወራሽ - በዚህ በሰይጣን ግዛት መካከል የተተከለች መለኮታዊ ስፍራ ናት። ሰይጣን ራሱን ኢየሱስን ሊታገሠው እንዳልቻለ ሁሉ፣ ይህንንም መታገሥ ባይችልም፣ በምንም መንገድ ሊሸሸው የማይችለው ጉዳይ ነው። ሊቃወመው ኀይል ያጣበት፣ በግዛቱ ውስጥ ያለ የሰማይ ቅኝ ግዛት - የባዕድ ጣልቃ ገብነት ሆኖበታል። ሐዋርያው ጳውሎስም "የእግዚአብሔር ልጆች" ብሎ ይጠራንና "ክፉ ሰዎች በሞሉበት በዚህ ዓለም÷ የሕይወትን ቃል እያበሠራችሁ እንደ ብርሃን ፋና አብሩ" ይለናል (ፊልጵ. 2÷15 - ሕያው ቃል)። ትክክለኛ ምንነቱን እናሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ሆን ብሎ እኛን *በኮስሞስ* ውስጥ አስቀምጦናል። በአንድ በኩል ለእግዚአብሔር የማይታዘዝ ዐመፀኛ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የውስጡን ባዶነት ሰዎች ሁሉ ያዩ ዘንድ ለመለኮታዊው ብርሃን ማጋለጥ አለብን።

ሥራችን እዚህ ላይ አያበቃም። ፊታቸውን ወደ እርሱ ከመለሱ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ብርሃን ከዓለም ከንቱ ባዶነት ነጻ አውጥቶ የእርሱ ወደ ሆነው ሙላት እንደሚያመጣቸው መልካሙን ዜና ለሰዎች ማወጅ አለብን። የሰይጣንን ጥላቻ የሚገልጠው ይህ የቤተ ክርስቲያን ጣምራ ተልእኮ ነው። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ የመገኘቷን ያህል የሚጉረብጠው ሌላ ነገር የለም። የምሥራች አብሣሪውና አጋላጩ ብርሃንዋ ተወግዶ ከማየት የበለጠም ምንም አያስደስተውም። ቤተ ክርስቲያን የዚህን የእግዚአብሔር ባላንጣ ጉን የምትወጋ እሾህ፣ እንዲሁም የቊጣውና የብስጭቱ



ቋሚ ምንጭ ናት። በዓለም ውስጥ *በመሆናችን* ብቻ በሰይጣን ላይ በቀላሉ የችግር ክምር እንሠራበታለን። ስለዚህ ዓለምን ለምን እንተዋለን?

"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ... ስበኩ" (ማር. 16÷15)። ይህ የክርስቲያን ልዩ መብት ነው። ሥራውም ነው። ከዓለም መውጣትን መርጠው የሚሞክሩ እስካሁን በተወሰነ ደረጃ ከዓለም የአስተሳሰብ ተጽዕኖ እንዳልተላቀቁ ብቻ ነው የሚያሳዩት። "ከዓለም ያልሆንን" እኛ፣ ለቀነው ለመውጣት የምንሞክርበት ምንም ምክንያት የለም። *ልንገኝበት የሚገባን ስፍራ ነውና።*

ስለዚህ ሥራዎቻችንን መተው አያስፈልገንም። እንዲያውም ለእኛ የተልእኮ ስፍራ ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አመለካከትና ግምት አይሠራም። ሕይወታችንን እንደ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ሥጋዊ ፍጥረት በተለያየ አኗኗር አንኖረውም። በሠለጠንበት ሙያ ወይም በተቀጠርንበት ሥራ ውስጥ ያለን ሚና፣ በእርሱ ልጅነታችን ከሚኖረን ሕይወት የተነጠለ እንዲሆን እግዚአብሔር ያሰበው አንዳች ነገር የለም። በመስክ ሥራም ሆነ በአውራ ጐዳና ላይ፣ በሱቅ ውስጥ፣ በፋብሪካ፣ በኩሽና፣ በሆስፒታል ወይም በትምህርት ቤት የምንሠራው ነገር ሁሉ ከክርስቶስ መንግሥት አኳያ መንፈሳዊ ዋጋ አለው። እያንዳንዱ ነገር ለእርሱ ሊሆን የተገባ ነው ብለን መሟገት አለብን። እነዚህ ስፍራዎች ለእርሱ መንገድ መመቻቸት የተወሰኑ በመሆናቸው፣ ሰይጣን በእነዚህ ስፍራዎች ምንም ክርስቲያኖች ባይኖሩ ይመርጣል። ስለዚህ ሰይጣን ከዚህ ዓለም እንድንወጣ ሊያስፈራራን፣ ይህ ካልሆነለት ደግሞ እንደ ዓለም አመለካከት እያሰብንና ባሕርያችንንም በዓለም ደረጃ እያስተካከልን በእርሱ የዓለም-አሠራር ውስጥ እንድንሳተፍ ሊያግባባን ይጥራል። ከሁለቱ የትኛውም ለእርሱ ድል ነው። ተስፋዎቻችን በሙሉ፣ ጠቅላላው ዝንባሌያችንና ዕድሎቻችን ሁሉ ከዓለም ውጭ ሆነው፣ እኛ በዓለም ውስጥ መሆናችን ግን ለሰይጣን ሽንፈት፣ ለእግዚአብሔር ደግሞ ክብር ነው።

የኢየሱስን በዓለም መገኘት በተመለከተ "ጨለማም አላሸነፈውም" ተብሎ ተጽፎአል (ዮሐ. 1÷5)። "ልናሸንፈው" ስለሚገባ ኀጢአት በቃለ-እግዚአብሔር ውስጥ በየትኛውም ስፍራ አልተነገረንም፣ ዓለምን ማሸነፍ እንዳለብን ግን በጉልህ ይነግረናል። ኀጢአትን በሚመለከት የእግዚአብሔር ቃል ነጻ ስለ መውጣት ብቻ ሲናገር፣ ስለ ማሸነፍ የሚናገረው ዓለምን በተመለከተ ነው።

በፍጹም ከኀጢአት ጋር ንክኪ ይኖረን ዘንድ የእግዚአብሔር አሳብ ስላይደለ፣ ከኀጢአት ነጻ መውጣት ያስፈልገናል፤ ከዓለም ነጻ

መውጣት ግን አያስፈልገንም፣ እኛም መፈለግ የለብንም፣ ከዓለም ጋር ግንኙነት ይኖረን ዘንድ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ከዓለም ነጻ አልወጣንም፣ ነገር ግን ከላይ በመወለዳችን አሸንፈነዋል። አሸናፊነታ ችንም ልክ ብርሃን ጨለማን የማሸነፉን ያህል የተረጋገጠና ተመሳ ሳይ ነው።

"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው። ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?" (1ዮሐ. 5፥4-5)። የድል መንግሥት ቁልፉ ከድል አድራጊው ጋር ያለን የእምነት ግንኙነት ነው። "አይዞአችሁ" አለ ጌታ፣ "እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16፥33)። እንደዚህ ማለት የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው፣ ይህን ንም ማለት የቻለው አስቀድሞ "የዚህ ዓለም ገዥ ... በእኔ ላይም አንዳች የለውም" በማለት ስላረጋገጠ ነው (ዮሐ. 14፥30)። በምድር ላይ ያለ ሰው እንዲህ ዐይነት ነገር ሲናገር ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። በእርሱም ድል መንግሥት የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ተጣለና ኢየሱስ ሰዎችን ወደ ራሱ መሳብ ጀመረ።

እርሱ እንዲህ ስላለ፣ አሁን እኛም ለማለት እንደፍራለን። "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና" እኔም ከአዲሱ ልደቴ የተነሣ፣ ጌታዬ በነበረበት ዓለም ውስጥ መሆን እችላለሁ፣ እንዲሁም እርሱ ከዓለም የተለየ እንደ ነበረ እኔም በተመሳሳይ ሁኔታ ከዓለም የተለየሁና በመቅረዝ ላይ ሆኖ ወደ ቤት ለሚገቡ ሁሉ ብርሃን እንደሚሰጥ መብራት እሆናለሁ። "እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና" (1ዮሐ. 4፥17)። ቤተ ክርስቲያን እግዚአ ብሔርን የምታስከብረው የእርሱን ብርሃን በዓለም ውስጥ በማንጸባረቅ እንጂ ከዓለም በመውጣት አይደለም። መንግሥተ ሰማይም እግዚአ ብሔርን የማምለኪያ ስፍራ እንጂ እግዚአብሔርን የማስከበሪያ ስፍራ አይደለም። እርሱን የምናስከብረው እዚህ ነው።



# ምዕራፍ ሰባት

## መላቀቅ

ቤተ ክርስቲያን ለሰይጣን ደንበኛ ውጋትና እንደ ልቡ የመንቀሳቀስ ነጻነቱን የምትገድብ የጐን እሾህ መሆንዋን አይተናል። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ ሆና የዓለምን ግንባታ ለማገዝ ባለመፍቀድ ብቻ ሳትወሰን፣ በበላዩ ፍርድ ማወጀንም ትቀጥላለች። ነገር ግን ይህ እውነት ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ለዓለም የብስጭት ምንጭ ከሆነች፣ ዓለምም በዚያው መጠን ለቤተ ክርስቲያን ቋሚ የሐዘን ምንጭ ነው። እናም ዓለም እያደገና የእግዚአ ብሔርን ሕዝብ የማስጨነቅ ኀይሉ እየተስፋፋ በመሆኑ፣ በእውነቱ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በዓለም ውስጥ ልትገናኝ ያለችው በቀደሙት ቀናት ተጋጥማው የማታውቀውን ኀይል ነው። ያኔ የእግዚአብሔር ልጆች በሰውነታቸው ላይ በአካላዊ ጥቃት መልክ ግልጽ ስደት ይደርስባቸው ነበር (የሐዋርያት ሥራ 12፣ 2 ቆሮንቶስ 11)። ከቁሳዊና ከተጨባጭ ነገሮች ጋር ሁልጊዜ ግጭት ያጋጥማቸው ነበር። አሁን በዓለም ውስጥ የሚያጋጥመው ዋነኛ ችግር፣ ይበልጥ ሙልጭልጭ የሆነ፣ ከቁሳዊ ነገሮች ጀርባ የሚገኝ፣ የማይታይ ክፉ መንፈሳዊ ኀይል ነው። ያ መንፈሳዊ ኀይል ዛሬ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ደግሞ ከዚያን ጊዜው በጣም ይበልጣል። መብለጥ ብቻ ሳይሆን፣ ቀድሞ በዚያን ጊዜ ያልነበረ ተጨማሪ አሠራር ዛሬ እናገኛለን።

በራእይ 9 ላይ ለሐዋርያው ዮሐንስ በርቀት ይታየው ስለ ነበረው እድገት እናነባለን። "አምስተኛውም መልአክ ነፋ፣ ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው። የጥልቁንም ጉድጓድ ከፈተው፣ ጢስም ከታላቅ እቶን እንደ ሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጉድጓዱ ወጣ ... ። ከጢሱም አንበጣዎች ወደ ምድር ወጡ፥ የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣ ቸው። የእግዚአብሔርም ማኅተም በግምባራቸው ከሌለባቸው ሰዎች በቀር፣ በምድር ያለውን ሣር ቢሆን ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር፣ ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው" (ቍጥር 1-4)። ይህ ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው፣ ነገር ግን ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀው ኮከብ የሚለው በግልጽ ሰይጣንን የሚጠቅስ ሲሆን፣ ጥልቁ ጉድጓድ ደግሞ ግዛቱ - መጋዘኑ እንደ ሆነ መናገር እንችላለን። እናም በፍጻሜው ቀን ልዩ ማከማቻዎቹን ስለሚከፍት፣ ሰዎች ከዚህ በፊት ተቋ ቁመውት ከማያውቁት መንፈሳዊ ኀይል በተቃራኒ ተሰልፈው ራሳቸ ውን ያገኛሉ።

ይህ ከጊዜአችን ሁኔታ ጋር በእርግጥ ይስማማል። ኀጢአትና ዐመፃ ከምንጊዜውም የበለጠ በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ የሚገኑ ቢሆንም፣ ያኔ ቤተ ክርስቲያን የምትተናነቀው በተለይ ከእነዚህ ጋር ሳይሆን፣ በየዕለቱ ከሚያጋጥሙን ጉዳዮች እጅግ ከመጠቀ መንፈሳዊ ፋይዳ ጋር እንደ ሆነ ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት አይከብድም። “በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ÷ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። ኖኅ ወደ መርከብ እስከ ገባበት ቀን ድረስ÷ ይበሉና ይጠጡ ያገቡና ይጋቡም ነበር÷ የጥፋት ውሃም መጣ ሁሉንም አጠፋ” (ሉቃ. 17÷26-29)። እነዚህ ነገሮች - ምግብ፣ ጋብቻ፣ ንግድ፣ እርሻና ምህንድስና ጉልተው የሚታዩ የሎጥና የኖኅ ዘመን ባሕርያት መሆናቸውን ሳይሆን በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ሊያስቀምጠው የፈለገው አሳብ፣ በልዩ መንገድ የመጨረሻውን ቀናት የሚገልጡ መሆናቸውን ነው። “የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል” (ቍጥር 30) - ነጥቡ ያ ነው። እነዚህ ነገሮች በባሕርያቸው ኀጢአት አይደሉም፤ የዓለም ነገሮች ብቻ ናቸው። በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ እንደ አሁኑ ለጥሩ ኑሮ ከፍተኛ ትኩረት የሰጣችሁበት ጊዜ አለ? ዛሬ ምግብና ልብስ የእግዚአብሔር ልጆች ልዩ ሸክም ሆነዋል። ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? የምንለብሰውን ከየት እናገኛለን? የሚሉት ከሞላ ጎደል ለብዙዎች ብቸኛ የውይይት አርእስት ናቸው። እነዚህን ነገሮች እንድታስላስሉ የሚገፋፋችሁ አንድ ኀይል አለ፤ መኖራችሁ ራሱ ለእነዚህ ነገሮች ትኩረት እንድትሰጡ ይጠይቃችኋል።

የእግዚአብሔር ቃል ግን፣ “የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ... እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም” በማለት ያስጠነቅቃል። ከሁሉ አስቀድመን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እንድንፈልግ፣ ይህን ካደረግን ደግሞ እነዚህ ነገሮች በሙሉ እንደሚጨመሩልን ያረጋግጥልናል። ምግብና ልብስን በሚመለከት እንዳንጨነቅ ያዝዘናል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሜዳ አበቦችና ለሰማይ ወፎች ከተጠነቀቀ፣ የእርሱ ለሆንነው ለእኛ ከዚህ ይልቅ እጅግ አይጠነቀቅልምን? ጭንቀታችን ሲታይ ግን ለእነርሱ እንጂ ለእኛ የሚጠነቀቅልን ያለ አይመስልም!

ልዩ ትኩረት የሚፈልገው ነጥብ ይህ ነው። ይህ የነገሮች አካሄድ ጤነኛ አይደለም። በእነዚህ ቀናት ብዙ ክርስቲያኖችን እንደ ንገምታቸው የሚያደርገን፣ ቀምሶ ለማደርም ይሁን ለቅንጦት ሲባል ለመብልና ለመጠጥ የሚሰጠው ከልክ ያለፈ ትኩረት፣ የተለመደ ጉዳይ ሳይሆን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ነው። ምክንያቱም እዚህ ጋ የምናገኘው የምግብና የመጠጥ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን፣ አጋንንቶችን ነው። የዓለምን ሥርዐት የመሠረተውና የሚቈጣጠረው ሰይጣን በዓለም ነገ



ሮች በኩል አጋንንታዊ ኀይል በመጠቀም አባብሉ ወደ ውስጥ ሊከተን ተዘጋጅቶአል። ነባራዊው ሁኔታም ከዚህ ተለይቶ የሚታይ ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔር ልጆች ለዚህ ገሃድ እውነታ ቢነቁ ምናለ! ባለፉት ቀናት የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉም ዐይነት ችግር ሲገጥማቸው በብዙ ጭንቅ መካከል ወደ እግዚአብሔር በማቅናት ሊታመኑት ችለዋል። በዛሬው ጫና መካከል ግን በጣም ግራ ስለ ተጋቡና ስለ ተደናገሩ እርሱን መታመን ያቃታቸው ይመስላል። እባካችሁ የእነዚህ ሁሉ ጫናዎችና ግራ መጋባቶች ምንጭ ሰይጣናዊ እንደ ሆነ እንረዳ!

ጋብቻንም በሚመለከት ይኸው ነው። እንደ ዛሬው ዐይነት በርካታ ችግር በዚህ ጉዳይ አጋጥሞን አያውቅም። ወጣቶች እሮጌውን ባህል ሲጥሱና በአዳዲስ ለመተካት ምሪት ሲያጡ የተፈጠረ ግራ መጋባት አለ። ይህ ጉዳይ እንደ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ነገር እንጂ እንደ ተራ ጉዳይ መወሰድ የለበትም። ማግባትና መጋባት በማንኛውም ዘመን ቢሆን ጤናማና የተለመዱ ነገሮች ናቸው። ዛሬ ግን አንድ እንግዳ ጉዳይ ወደ እነዚህ ነገሮች ውስጥ እየገባ ነው።

በመትከልና በመገንባት፣ በመግዛትና በመሸጥም እንዲሁ ነው። እነዚህ ነገሮች በትክክል ተገቢና ጠቃሚ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከጀርባቸው ያለው ኀይል፣ እስኪደናገሩና ሚዛናቸውን እስኪስቱ ድረስ ሰዎችን እየተጫነ ነው። የዓለም አሠራር አንቀሳቃሽ የሆነው ክፉ ኀይል ዛሬ ሁለት ጽንፎችን የምናይበት ሁኔታ አስከትሎአል፤ የመጀመሪያው ጽንፍ፣ ሰዎች ጉድለታቸውን እንኳ ለማሟላት አለመቻላቸው ሲሆን፣ ሌላኛው ጽንፍ ደግሞ ሀብትን የማከማቸት ያልተለመደ ዕድል መኖሩ ነው። በአንድ በኩል ብዙ ክርስቲያኖች ተደርጎ በማይታወቅ ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ተዘፍቀው ራሳቸውን ሲያገኙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎች ራሳቸውን የማበልጸግ ያልታሰበ ዕድል አጋጥሞአቸዋል። ሁለቱም ሁኔታዎች ትክክል አይደሉም።

በእነዚህ ቀናት ወደ የትኛውም ቤት ገባ ብላችሁ የሚካሄደውን ውይይት ለመስማት ጆሮአችሁን ጣል ብታደርጉ፣ እንደዚህ ዐይነት አስተያየቶችን ትሰማላችሁ። “ባለፈው ሳምንት የሆነ ዕቃ በርካሽ ዋጋ ስለ ገዛሁ፣ ብዙ ብር አተረፍኩ”። “ያንን ዕቃ ከዓመት በፊት በመግዛቴ ተደስቻለሁ፣ ያ ባይሆን ኖሮ እከስር ነበር”፣ “መሸጥ ከፈለግህ፣ አሁኑኑ ገበያው ጥሩ እያለ ሽጠው”። ሰዎች የንግድ ድርድሮችን በጥድፊያ ለመፈጸም ወደዚህና ወደዚያ የሚሮጡበትን መንገድ አስተዋላችሁ? ዶክተሮች ዱቄት እያከማቹ ነው፣ ጨርቅ አምራቾች ወረቀት እየሸጡ ነው፣ ከዚህ በፊት እነዚህን ነገሮች ነክተው የማያውቁ ወንዶችና ሴቶች ወደ ፊት ያተርፈኛል በሚል ሞገድ እግሮቻቸው እየ

ከነፉ ናቸው። እንደ እብድ በሚያሽከረክራቸው የገበያ አዙሪት ተይዘዋል። ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ጤናማ አለመሆኑን አትገነዘቡም? ሰዎችን ምርኮኛ የሚያደርግ ኀይል መኖሩስ አይታያችሁም? ሰዎች እየሠሩ ያሉት እንደ ባለ አእምሮ አይደለም፣ ከቍጥጥራቸው ውጭ ሆነዋል። ዛሬ የመግዛትና የመሸጥ ግርግር፣ ገንዘብ የማትረፍ ወይም የመክሰር ጥያቄ አይደለም። ሰይጣናዊ አሠራርን የመንካት ጥያቄ ነው። ዛሬ እየኖርን ያለነው፣ በፈቃዳቸውም ሆነ ያለፈቃዳቸው ሰዎችን ወደፈለገበት አቅጣጫ የሚነዳ ልዩ ኀይል በተለቀቀበት የፍጻሜ ጊዜ ነው።

ስለዚህ ዛሬ በአንድ ነገር ኀጢአትነት ላይ ያለው ጥያቄ፣ በአንድ ነገር ዓለማዊነት ላይ ያለውን ጥያቄ አያክልም። በመብላታችሁና በመጠጣታችሁ ስሕተት አድርጋችኋል ሊል የሚደፍር ማነው? ማግባትና መጋባትን ለማጣጣል ማን ይደፍራል? የመግዛትና የመሸጥ መብታችሁንስ ማን ይቃወማል? እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ስሕተት አይደሉም፤ ስሕተቱ ያለው ያለ ርኅራኄ በሚጫነን፣ ከበስተ ጀርባቸው ባለው መንፈሳዊ ኀይል ላይ ነው። እነዚህ ነገሮች ተራና ቀላል ቢሆኑም፣ ሰይጣን የእግዚአብሔር ልጆችን በዓለም ሥርዐቱ ለማጥመድ እንደ ትልቅ መረብ እየተጠቀመባቸው መሆኑን ለመረዳት መንቃት ይኖርብናል።

“በመብልና በመጠጥ ብዛት በስካርም በመባከንና ስለ ዓለማዊ ኑሮ (ሕይወት) በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝል ተጠንቀቁ። አለበለዚያ ያ ቀን እንደ ወጥመድ በድንገት ይመጣባችኋል” (ሉቃ. 21፥34 - የ1980 ትርጉም)። ከኢየሱስ ቃላት መካከል “ሕይወት” የሚለውን ቃል አጠቃቀም ልብ በሉ። በግሪኩ አዲስ ኪዳን ሕይወትን ለመግለጽ ሦስት ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል - *ዞይ (zóe)*፣ መንፈሳዊ ሕይወት፤ *ሱኬ (psuche)*፣ ሥነ-ልቦናዊ ሕይወት፣ እና *ባዮስ (bios)* ሥጋዊ ሕይወት። በዚህ ስፍራ *ባዮቲኮስ (biotikos)* በሚል ቅጽል የምናገኘው ሦስተኛውን የሕይወት ዐይነት ነው። ጌታ ኢየሱስ ለኑሮ ማሰብ ከልክ በላይ እንዳይጫነን - ለምድራዊ ሕይወታችን የሚያስፈልጉንን ምግብና ልብስን በሚመስሉ ነገሮች እንዳንጨነቅ ጥንቃቄ መውሰድ እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። አዳምና ሔዋን የወደቁት በዚህ ዐይነት ቀላል ነገር ሲሆን፣ ጥቂት ክርስቲያኖችም ሰማያዊውን የእግዚአብሔር ጥሪ ችላ የሚሉት በዚሁ ዐይነቱ ቀላል ጉዳይ ይሆናል። ሁልጊዜም፣ ይህ ልብ የሚገኝበትን ስፍራ የሚመለከት ነው። እኛም ልባችን ስለ እነዚህ ነገሮች በማሰብ “እንዳይከብድ” እና እንዳንከስር በጥብቅ ተነግሮናል። ማለትም፣ እነርሱን በሚመለከት ከልክ በላይ የሆነ የሚከብደንን ሸክም መሸከም የለብንም ማለት ነው። በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉን ንብረቶቻችን ጋር በመንፈስ መለያየት አለብን (ሉቃ. 17፥31)።



ማን እንደ ሆንን እንወቅ! ቤተ ክርስቲያን - በጨለማ መካከል የምናበራ የዓለም ብርሃን ነን። ስለዚህ እዚህ ታች ሳለን ልክ እንደዚህ እንኑር።

ቤተ ክርስቲያን የዓለምን መንገዶች የናቀችበት አንድ ወቅት ነበር። አሁን ግን ከመጠቀምም አልፋ አላግባብ እየተጠቀመችባቸው ናቸው። በእርግጥ ዓለም አስፈላጊያችን ስለ ሆነ እንጠቀምበታለን፤ ነገር ግን እኛ እንፈልገው፣ እንመኘው። ስለዚህ ኢየሱስ ንግግሩን በመቀጠል፣ “እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ” ይለናል (ሉቃ. 21፥36)። እግዚአብሔር ተግተን እንድንጸልይ የሚናገረን፣ በተቃራኒ የምንሰለፍበት ምንም መንፈሳዊ ኀይል በሌለበት ስፍራ ነውን? ከዚህ ዓለም ጉዳዮች በመንፈስ መለያየታችን እውነት እስኪሆን ድረስ ሁልጊዜ መንቃት አለብን እንጂ፣ የሕይወት ዕጣችንን እንደ ተራ ሂደት ለመውሰድ አንድፈር። ለሕልውናችን ወሳኝ የሆኑ የዓለም ነገሮች አሉ። ስለ እነርሱ ማሰብ ተገቢ ነው፣ ሲጫኑንና ሲከብዱብን ግን ትክክል ካለመሆኑም በላይ፣ እግዚአብሔር ያሰበውን የተሻለ ነገር ያሳጣናል።

የራእይ መጽሐፍ፣ ሰይጣን በፖለቲካው ዓለም ውስጥ (ምዕራፍ 13)፣ በሃይማኖታዊው ዓለም ውስጥ (ምዕራፍ 17) እና በንግዱ ዓለም ውስጥ (ምዕራፍ 18) የክርስቶስ ተቃዋሚውን መንግሥት እንደሚመሠርት ይነግረናል። የእርሱ አገዛዝ፣ በእነዚህ ሦስት - የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና የንግድ ዘርፎች ውስጥ የመጨረሻውን የዐመፃ መግለጫ ያገኛል። በኋለኞቹ ሁለት ምዕራፎች ይህ መንግሥት የሰይጣን ሙሉ መገለጫ በሆነችው በባቢሎን ምሳሌነት ተገልጦአል። ባቢሎን የተበላሸውን ክርስትና - ምናልባት ሮምን፣ ነገር ግን ከሮም በላይ የምታጠፋውን - ስትወክል፣ የተፈረደባትም ከንግዷ ጋር በተያያዘ ነው። ጠቅላላው የምዕራፍ 18 ዘገባም በነጋዴዎችና በንግዳቸው ዙሪያ ነው የሚያጠነጥነው። በታላቂቱ ከተማ መውደቅ እርር ኩምትር ያሉት፣ ከላይ ከንጉሡ ጀምሮ እስከ ታች እስከ መርከብ መሪዎች ድረስ ያሉት በሙሉ፣ የሚያለቅሱት የበለጸገው ንግዷ ድንገት መክሰሙን ሲያስቡት ነው። የባቢሎን መንፈስ እንደገና እንዲንሠራራ ምክንያት የሚሆነውም ሃይማኖት ወይም ፖለቲካ ሳይሆን፣ ንግድ መሆኑ ተረጋግጦአል፤ ያም በውድቀቷ ጊዜ ተለቅሶለታል። ንጹሕ ንግድ ስሕተት ነው ብለን በአጽንኦት ለመናገር አንደፍርም፣ ነገር ግን ይህኛውን በሚመለከት ጅማሬው ከሰይጣን ጋር (ሕዝ. 28)፣ ፍጻሜውም ከባቢሎን ጋር (ራእይ 18) የተያያዘ እንደ ሆነ፣ ከራሱ ከእግዚአብሔር ቃል በመነሣት እንናገራለን። ከሌሎች መስኮች ይልቅ ንግድ፣

- እግራችሁ ታጥቦአል ማለት ነው። ታዲያ ማጠብ ምን ማለት ነው? ወደ መጀመሪያው የትኩስነት ስሜት መመለስ ማለት ነው። ሁሉንም ነገሮች ልክ አሁን እግዚአብሔር ከሚገኝበት ስፍራ እንደ ወጡ፣ ልክ አሁን ከእጁ እንደ ወጡ ወደሚመስል ጥርት ያለ ነጥብ መልሶ ማምጣት ማለት ነው።

እኔ በግሌ የኀጢአት ችግር ሳይሆን፣ ይህ ዐይነቱ በዓለም አቧራ የመሸፈን ስሜት ሲያስቸግረኝና የመውረድ ስሜት ሲሰማኝ፣ ስላለሁበት ሁኔታ ምንም ሳያውቁ፣ ወደ ብርሃን የሚመልስ ተጋቦት ትተውልኝ ካለፉ ወንድም ወይም እኅት ጋር ብዙ ጊዜ ተገናኝቻለሁ። ይህ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ በቀላሉ ጨለማው ሁሉ እንደ ተወገደና ትቢያው ሁሉ እንደ ተጠረገ ይታወቃችኋል። እግዚአብሔር ይመስገን፣ ታድሳችኋል፤ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት መደሰት ወደምትችሉበት ሁኔታ ተመልሳችኋል። ይህም እግርን ማጠብ፣ በክርስቶስ ያለውን ወንድሜን ማነቃቃት፣ ልክ ከእግዚአብሔር ፊት አሁን የተነሣ ወደሚመስልበት ስፍራ ማምጣት ነው። ጌታ ይህንን የእርስ በርስ አገልግሎት በልጆቹ መካከል ለማየት ይናፍቃል።

ከእግዚአብሔር ጋር የምንጓዝ ከሆነና ለወንድሞቻችን መነቃቃት ለመሆን የምንመኝ ከሆነ፣ የማንሆንበት አንድም ቀን አይኖርም። ይህም ከትልልቅ አገልግሎቶች መካከል አንዱ ነው። ምናልባት ከእጅ መጨባበጥ አያልፍ ይሆናል። በድንገት የተነገረ የማበረታቻ ቃል ሊሆን ይችላል። በፊታችን ላይ የሚያርፍ የሰማይ ብርሃን ብቻም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚመጣበት መንገድ ካገኘና በእኛና በእርሱ መካከል የሚጋርድ ደመና ከሌለ፣ እርሱ እንደሚጠቀምብን ይገባናል። ምናልባት ለማወቅ አለመፈለጉ የተሻለ ስለ ሆነ አ፡ውቀው ይሆናል - በእርግጥም በፍጹም ባናውቀው ይሻላል። ነገር ግን አወቅነውም አላወቅነው፣ ወንድማችንን ለማነቃቃት (ለማደስ) በቋሚነት ጥቅም ላይ እየዋልን ነው። ከነበረበት ከፍታ ሲወርድና በጨለማ ውስጥ ሲሆን፣ በልቡ ሸክም ሲኖር ወይም በዐይኖቹ ፊት ጉድፍ ሲኖር፣ ሲያድፍና ሲቆሽሽ፣ ያኔ ወደ እኛ ይመጣል። ምናልባት ከጥቂት ደቂቃዎች በቀር ብዙ ላይቆይ ይችላል። ያንን አገልግሎት ፈልጉ። እርሱን ለመርዳት ጸጋን ከእግዚአብሔር አግኙ። በደንብ መስማትን የሚጠይቁ ረጃጅም ስብከቶችን ብናደርግ መልካም እንደ ሆነ ብዙ ጊዜ እናስባለን፣ ነገር ግን ይህ ስጦታ ያላቸው ጥቂቶች ናቸው፣ በእነዚህ በጥቂቶቹ ያልተደረሱ ደግሞ በርካታ ናቸው። የቅዱሳንን ልብ ማነቃቃት ማንም ሰው ሊፈጽመው የሚችለውና የትም መድረስ የሚችል የአገልግሎት ዐይነት ነው። በእግዚአብሔር ዋጋ አሰጣጥ መሠረት፣ ይህ ዋጋ አያስከፍልም።



ነገር ግን በዚህ መንገድ ሌሎችን ለማገልገል ማሟላት ያለብን ሁኔታዎች አሉ። በእርግጥ ከጌታ ጋር እየተጓዝን ከሆነ፣ እርሱን የሚገድበው ነገር ስለማይኖር እንደሚጠቀምብን አጠያያቂ አይደለም። ልባችን በእርሱ ሰላምና ደስታ ተሞልቶ፣ እኛ ራሳችን ያላደፍን ከሆንን በውስጣችን ተሞልቶ ሊፈስ ያለ ነገር ይኖራል። ስለዚህ በእግዚአብሔርና በእናንተ መካከል ያለመግባባት ነጥብ ይኖር ይሆን? ብዬ እጠይቃችኋለሁ። የምጠይቃችሁም በግልጽ ስለሚታወቅ ጉዳይ ነው። የተለየ ነገር ከሌለ፣ የሆነ ነገር ለማግኘት መፈለግ አይኖርብንም፣ ሁል ጊዜ ጌታ ራሱ ይደርስበታል። እናንተ ሳታስተውሉ ያለፋችሁትን ነገር ወደ እርሱ ብርሃን ለማምጣት ሲፈልግ፣ ሁልጊዜም ጣቱን ወደዚያ ይጠቁማል፣ እናም ታውቁታላችሁ። ስለዚህ ዐይኖቻችሁን ወደ ውስጥ በማድረግ፣ እያንዳንዱን ስሜት በማጣራትና በመተንተን ቆፍራችሁ ልታወጡት መሞከር አያስፈልጋችሁም። እርሱን አመስግኑት! በልባችሁ ውስጥ ብርሃኑን ማብራትና ከመስመር መውጣታችሁን ለራሳችሁ ማሳየት የእርሱ ጉዳይ እንጂ የእናንተ አይደለም።

አንድ ነገር ግን የተረጋገጠ ነው። ከጌታ ጋር ካልተስማማችሁ፣ ሌሎችንም ትበክላላችሁ። እግሮቻቸውን ልታጥቡ አትችሉም። ከከፍታ ወርደው ከሆነ፣ በጣም ታወርዷቸዋላችሁ። ተጫጭኖአቸው ከሆነ፣ ወደ እነርሱ መጥታችሁ የበለጠ እንዲከብዳቸው ነው የምታደርጉት። እነርሱን ከማነቃቃትና ከእግዚአብሔር ወደሚገኘው ትኩስነት መልሶ ከማምጣት ይልቅ ወደ ጥልቅ ጨለማ ማጥለቅ ብቻ ነው የምትችሉት። ከእግዚአብሔር ጋር ባላችሁ ግንኙነት ላይ የጐደለ ነገር መኖሩ፣ በእርሱ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ሸንቁር ለማበጀት የተረጋገጠ መንገድ ሲሆን፣ ትልቁ የኀይል መገለጥ ደግሞ ሌሎችን በቋሚነት ማነቃቃት መቻል እንደ ሆነ አምናለሁ። ይህ ከፍ የሚያደርገው፣ የሚያነጻው፣ የሚያድሰው ሰማያዊ መነካት ደግሞ በዋጋ አይገመትም።

“እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል”። ለደቀ መዛሙርቱ ካስተላለፋቸው ትእዛዞች ሁሉ ይህኛው ቴአትራዊ አገላለጽ የያዘ ነው። ጠቃሚነቱም ምን ያህል እንደ ሆነ ሊያሳያቸው ስለ ወደደ እርሱ ራሱ ከእነርሱ አስቀድሞ ተገበረው። ይህም “በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን” (ቍጥር 1) የወደደበት ፍቅር መግለጫ ነበር። አገልግሎት ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ለማሳየት ራሱን በምሳሌነት አቀረበ። የመድረክ ሥራ አይደለም። በመታጠቢያና በፎጣ የሚደረግ የእርስ በርስ አገልግሎት ነው። የወደቁትን ሰዎች መልሶ የማቅናትና ኀጢአት የሠሩትን ደካሞች ወደ ንስሓ የማምጣት አስፈላጊነት ሁልጊዜም ይኖራል፤ ነገር ግን ዛሬ ትልቁ የቅዱሳን አገል

ግሉት የመነቃቃት - ማለትም መጀመሪያ ወደ ነበረውና የእግዚ አብሔር ወደ ሆነው መልሶ ማምጣት ነው። ይህ ኀይል ነው። ኢየሱስ ራሱ ይህን ለመፈጸም "ከእግዚአብሔር ወጥቶ እንደ መጣ" (ቍጥር 3 - የ1980 ትርጒም) የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል። እናንተን እንዴት እንደሚያስደንቃችሁ ባላውቅም፣ ለእግዚአብሔር፣ በዓለም ፊት በእርሱ ንቁ ሆነን ከመገኘታችን የሚበልጥበት ሌላ ኀይል ያለ አይመስለ ኝም። እናንተስ ይህን የመለኮታዊው ሕይወት ኀይል ትልቅ መገለጥ ሆኖ አላገኛችሁትም? ከጥልቁ ጒድጓድ በሚወጣው ጢስ በጨለመው የዓለም-ሥርዓት መካከል በሰማያዊው ንጹሕ አየር የተነቃቁ ቅዱሳንን መገናኘት እጅግ የሚያስደስት ነው። ይህ ዐይነቱ ትኩስነት ደግሞ ለእኔና ለእናንተ መለኮታዊውን የሕይወት መንፈስ ያድስልናል።

በዚህ ዘመን ብዙም ከማይገኙ ቅዱሳን መካከል አንዲቷን በወጣትነት ቀኖቼ የማወቅ ዕድል ስለ ነበረኝ ጌታን አመሰግናለሁ። ለብዙ ዓመታት እንተዋወቃለንና ብዙ መንፈሳዊ ብቃቶች እንዳሉአት ተረድቻለሁ፤ ከሁሉ የሚያስደንቀኝ ግን ልክ አጠገቧ ስደርስ እግዚአ ብሔር በዚያ ስፍራ እንዳለ የሚሰማኝ ስሜት ነው። የእግዚአብሔር ሕልውና ሳይሰማችሁ እርሷ ባለችበት ስፍራ ረዘም ላለ ጊዜ መቀ መጥ፣ ወይም በክፍሏ ውስጥ መግባትና እጇን መጨበጥ አትችሉም። እንዴት እንደ ሆነ አታውቁም፣ ግን የእግዚአብሔር ሕልውና ይሰማ ችኋል። ይህ የሚሰማኝ ደግሞ እኔ ብቻ አልነበርኩም። ከእርሷ ጋር ግንኙነት ያለው ሁሉ ተመሳሳይ አስተያየት ይሰጣል። በእነዚያ ቀናት ብዙ ጊዜ ልቤ መዛሉ ይሰማኝ የነበረ ሲሆን፣ ነገር ሁሉ የተበላሸ ይመስለኝ ነበር። ያኔ ልክ ወደ ክፍሏ እገባለሁ፣ ወዲያውኑ ስገሠጽ ይታወቀኛል። ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት እንደ ነበርኩ ወዲያውኑ ይሰማኝና እታደሳለሁ።

ይህ ቅጽበታዊ ተሐድሶ እንዴት ይሆናል? በእርግጥ፣ ለጥቂት የታደሉ ሰዎች ብቻ የተሰጠ አገልግሎት አይደለም። እግዚአብሔር እያንዳንዳችን እንደዚህ እንድንሆን - ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሲደ በዝዙ የምናበራበት ያ ኀይል በውስጣችን እንዲኖር ይወዳል። መደብ ዘዝ በክርስቲያን ሕይወት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አንዳንዴ ከኀጢ አት ይልቅ የሚጎዳ መሆኑን ልናገር? በተለያየ ጊዜ ማንኛችንም በኀጢአት እንወድቅ ይሆናል፣ ነገር ግን ይህ የሚያመጣውን ውጤት ጠንቅቀን ስለምናውቅ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንፈልግና እናገኛ ለን። በዓለም መደብዘዝ ደግሞ ለሰዓታት ደብዝዘን እንቈይና ኀጢአት ባለ መሆኑ ሳያሳስበን ይቀራል። በዓለም ላይ የምናሳድረው የእግዚአ ብሔር ተጽዕኖ የሚደንዘው ያኔ ነው። በዚህ ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የአምልኮ ሕይወት እንዲታደስና እንድናንሰራራ ከዚህ በፊት የረ ዱንን ወንድሞችና እኅቶች በአካባቢአችን ማግኘት እንዴት ጥሩ ነው!



ታዲያ ሕጒቹ ምንድን ናቸው? ሁለት ናቸው። መጀመሪያ፣ አሁን እንዳየነው፣ በእኔና በጌታዬ መካከል ሳይስተካከል የቀረ አለ መስማማት መኖር የለበትም፤ ካለ ግን ሙሉ በሙሉ ከዚህ አገልግ ሉት ውጭ ያደርገኛል። ስለዚህ ጒዳዩ ምንም ዐይነት ቢሆን ወዲያ ውኑ መስተካከል አለበት፣ ወይም ከጥቅም ውጭ ነኝ። ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ዕቃ ከመሆን ርቄ፣ ሸክም ብቻ ነው የምሆነው። ምንም መልካም አስተዋጽኦ ማድረግ አልችልም፤ በእርሱ ልጆች ላይ ዕዳ ከመጨመር በቀር። በዚህ ጒዳይ ላይ የራሴን ድርሻ ለመወጣት፣ በእኔና በእግዚአብሔር መካከል ያለው እያንዳንዱ ጒዳይ በግልጽ ተጣርቶ መስተካከል አለበት። ከዚህ ዐይነቱ አለመስማማት ነጻ ከሆንኩ፣ ወንድሞቼን ከዓለም በተቃራኒው የኀይል ስፍራ ለመ መለስ እኔም ምክንያት እሆናለሁ።

ሁለተኛ ደግሞ (አለመግባባት እንዳይፈጠር ይህ በግልጽ መቀመጥ አለበት) ጒዳዩ የእርስ በርስ መታደስ መሆኑን አስታውሱ። ኢየሱስ "እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል" ብሉአል። ሌሎችን የሚያድሰው ሰው፣ ራሱ በሌሎች መታደስን መጠባበቅ አለበት። ጌታ ብዙ ጊዜ ይጠቀምባችሁ ይሆናል፣ ግን በዚያው መጠን እናንተኑ ለማነቃቃት ብዙ ጊዜ ሌሎች ሰዎችንም ይጠቀም ይሆናል። ማንኛችንም ብንሆን በዚህ ዓለም የምንመላለስ በመሆኑ፣ መታደስን እንፈልጋለንና ለዚህ መንፈሳዊ ሥራ ተለይተው የተቀመጡ ጥቂት "አነቃቂዎች" ሊኖሩ አይችሉም። ልክ ጴጥሮስን ይመስል፣ ከእኛ መካከል አንድም ሰው "እኔ ያንን ደረጃ አልፌአለሁ። ከእግዚአብሔርም ጋር ከመደብዘዝ በላይ የሆነ ግንኙነት ስላለኝ፣ ይህ አገልግሎት ሳያስፈልገኝ መጸለይና መስበክ እችላለሁ። ስለዚህ አንተ የእኔን እግር ፈጽሞ አታጥብም!" ለማለት መብት ያለው የለም።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መነቃቃት የማያስፈልግበት የወንድ ሞች እርከን የለም። ይህ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊደገፍ በት የሚገባ ነገር ነው። በሥርቶ ማሳያ ወይም በኩሽና ውስጥ ሙሉ ቀን ስትሠሩ የምትውሉ፣ ብሩህነት በጣም ያስፈልጋችኋል፣ ከእኛም መካከል የተወሰንነው ደግሞ ሙሉ ቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንሠራ ነው የምንውለው፣ ይሁን እንጂ እኛም ብሩህነት ያስፈልገናል! እውነታውን ሳናስተውለው ብናልፍ እንኳ አንዳንዴ የሚያስፈልገን ተሐድሶ ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል። ግልጽ በሆነ ሕዝባዊ ሥራ ወይም መንፈሳዊ ነገሮችን በመሥራት የተያዝን ብንሆንም፣ ዓለም ያለው በዙሪያችን ነው - ዘግቶ ይዞናል። ስለዚህ በየጊዜው አንዳንድ ወንድሞ ቻችንና እኅቶቻችን ወደዚያ ትኩስ የእግዚአብሔር መነካት - በመለኮ ታዊ ኀይል ወደ መታደስ እንደገና ከፍ እንዲያደርጉን ይረዱን ዘንድ ያስፈልጋል።

እናም የአካሉ መርሕ ማነቃቃትና መነቃቃት (ማደስና መታደስ) ነው። ከጌታ ጋር ብዙ በተጓዝን መጠን ይበልጥ ወንድሞችን እንፈልጋለን። ምክንያቱም በዚህ አገልግሎት ውስጥ ማንም የሚናቅ፣ ወይም በሌሎች መገልገል ወደማያስፈልገው ደረጃ የደረሰ የለም። ስለ ራሴ የምጸልየው፣ እግዚአብሔር መንፈሱ የዛለበትን ሰው ለማደስ በየጊዜው እንዲጠቀምብኝና በተመሳሳይ መልኩም የዛለውን መንፈሴን ለመንካትና እኔን ለማደስ፣ በየጊዜው ሌላ ሰው እንዲጠቀም ነው። የዓለም ማደብዘዝ፣ በዚያ ወንድም አገልግሎት ከእኔ ላይ ከተራገፈና ዝዬ የመጣሁት ታድሼና በርትቼ ከሄድኩ፣ የዚያ ወንድም አገል ግሎት ለእኔ የክርስቶስ አገልግሎት ሆኖኛል ማለት ነው።

በዚህ ስፍራ በቀላል አነጋገር ለመተንተን የፈለግሁት ዓለምን የምንጋጠምበት የተባበረ ግንባር እንዲኖረን ነው። ይህ ትንሽ ነገር አይ ደለም። በተግባር እስከ መግለጥ ያመንንበት ከሆነ፣ በውስጡ የሰይጣንን ጠንካራ ምሽጎች እንኳ የሚያንቀጠቅጥ ኃይል የያዘ እንደ ሆነ እርግጠኛ ነኝ። ልክ ጌታ እንዳለው፣ "ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ"።



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ሕጉቼን በልባቸው ውስጥ

በቀደሙት ምዕራፎች ይህ ዓለም ምን እንደሚመስል እውነተኛ ገጽታውን - ልክ እንደ ስፍራነቱ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ሕዝብ ዘርነቱ ሳይሆን፣ እንደ ማንኛውም ቁሳዊ ነገር ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጠላት ራስ እንደ ሆነበት መንፈሳዊ አሠራርነቱ ስንመለከተው ቈይተናል። "ዓለም" የሰይጣን የሥራ ውጤ ሲሆን፣ እንዲበለጽግለትና እንዲስፋፋ ለማድረግ ጠቅላላ ኃይሉንና ብልሀነቱን እየተጠቀመ መሆኑን እናስባለን። እስከ ምን ድረስ? በእርግጥም የሰዎችን ታማኝነት ለመማረክና ወደ ራሱ እስከ መሳብ ድረስ ነው። አንድ ዓላማም አለው - በመላው ዓለም በሰዎች ልብ ውስጥ የራሱን ግዛት መመሥረት። ያም ግዛት የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ማወቅ ቢኖርበትም - ያለ ምንም ጥያቄ - ያ የእርሱ ግብ ነው። እናም የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስና የእርሱ ጥረት ሲጨምር የእግዚአብሔር ልጆች ጭንቀትና ሥቃይም ይባባሳል። በዓለም ውስጥ ያላቸው ስፍራ የእንግዶችና የመጻተኞች እንጂ የዓለም ስላልሆኑ፣ አይመቻቸውም። ስለዚህ ከመንፈሳዊ ውጥረቱ ዕረፍት ለማግኘት በአካል ለመራቅ በመፈለግ ይደክማሉ። ከዚህ ዓለም ሙሉ በሙሉ ማምለጥና ለዘላለም ከጌታ ጋር መኖር እንዴት መልካም ነው!

ይህ ግን የእርሱ ፈቃድ አይደለም። የጸለየውም፣ እግዚአብሔር አብ የእርሱ የሆኑትን ከዓለም እንዲያወጣቸው ሳይሆን፣ በዚያው ከክፉ እንዲጠብቃቸው መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። ጳውሉስም ተመሳሳይ መንገድ ተከትሉአል። የቆሮንቶስ አማኞች ከአንድ ኀጢአተኛ ጋር ኅብረት ሊኖራቸው እንደማይገባ በአንድ አጋጣሚ አጥብቆ ካሳሰባቸው በኋላ፣ ይህ አባባል አለመግባባት እንዳይፈጥር ስለ ሠጋ ወዲያውኑ የማብራራት እርምጃ ወሰደ። ራሳቸውን ማግለል የለባቸውም። በዓለም ውስጥ ካሉ ምንም ዐይነት ኀጢአተኞች ጋር - እርሱ በዘረዘረው ውስጥ ከሚካተቱ ኀጢአተኞች ጋርም ቢሆን፣ ግንኙነታቸውን ማቋረጥ የለባቸውም፣ አለበለዚያ ይህን ለማድረግ ዓለምን ሙሉ በሙሉ መልቀቅ ይጠበቅባቸዋል። "ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ። በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን፥ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፤ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር" (1ቆሮ. 5፥9-10)።

እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ በእርግጥም ከዓለም ጋር መተባበር እንዳለብን፣ ከጳውሎስ ቃላት በግልጽ እናያለን፣ መተባበርም አለብን፣ እግዚአብሔር የወደደው ይህን ዓለም አይደለምን? ጥያቄው ግን እዚህ ላይ ነው - እስከ ምን ድረስ? ምን ያህል ርቀት እንጓዝ? የሆኑ ነጥቦች ላይ የዓለምን ነገሮች መንካት እንዳለብን ሁላችንም እንስማማለን። አንድ ቦታ ግን ገደብ እንዳለ እንገምታለን። ከዚህ ገደብ ውስጥ እስካልወጣን አደጋ አይኖርብንም፣ ገደቡን ከጣስን ግን በሰይጣን አሠራር ውስጥ ተሳታፊ የመደረግ ችግር እናመጣለን።

ይህ ችግር ኀይለኛና አደጋዎቹም ግልጽ ስለ ሆኑ ልናጋንነው እንችላለን ብዬ አላስብም። ለምሳሌ በጣም ታምማችሁ ሥቃያችሁ ሲበዛ ዶክተሩ ሕመማችሁን ለማስታገሥ እንዲረዳችሁ ሄሮይን ወይም ሞርፊን ሊያዝላችሁ ይችላል፣ ያኔ በሱስ የመጠመድ ችግር ያጋጥማችኋል። ሐኪሙን ትታዘዛላችሁ፣ ሕክምናውን ትወስዳላችሁ፣ ነገር ግን መድኀኒቱን የምትወስዱት በፍርሀትና በጸሎት ይሆናል፣ ምክንያቱም መድኀኒቱ እናንተን በሥሩ የሚያውል ኀይል እንዳለው ታውቃላችሁና ነው። ሕክምናው መራዘም ካለበት ደግሞ በተለይ ይህ ይሆናል።

እናንተና እኔም በዓለም ነገሮች በኩል ዓለምን በምንነካ ጊዜ ሁሉ (ይህን ደግሞ በተደጋጋሚ ማድረግ አለብን) ልክ ሕመማችንን ለማስታገሥ ሞርፊን የሚባለውን አደንዛዥ መድኀኒት ስንወስድ የሚሰማን ስሜት ሊሰማን ይገባል፣ ምክንያቱም የዓለም በሆኑ ነገሮች ሁሉ ጀርባ አጋንንቶች በመኖራቸው ነው። በጣም ከታመምኩ በሕክምና ሞርፊን እንደሚታዘዝልኝ ሁሉ፣ አሁንም በዓለም ውስጥ ነኝና ከዓለም ጋር በመሥራት - በንግድም ሆነ በሌላ የሥራ መስክ - ራሴን ማስተዳደር አለብኝ። ለኦፒየም ሱስ ሳልማረክ፣ ምን ያህል አደገኛ ድራጉችን መውሰድ እንደምችል አላውቅም፣ እንደዚሁም ሳልጠመድ ምን ያህል ነገሮችን መግዛት እንደምችል፣ ምን ያህል ገንዘብ ማትረፍ እንደምችል፣ ምን ያህል የንግድና የሙያ ቅርበት ሊኖረኝ እንደሚችልም አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ከእያንዳንዱ ዓለማዊ ነገር ጀርባ ሰይጣናዊ ኀይል መኖሩን ነው። ስለዚህ ለምን ያህል ተደጋጋሚ አደጋ የተጋለጠ መሆኑን ይረዳ ዘንድ እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ ዓለም መንፈስ ግልጽ መገለጥ ቢኖረው በጣም ወሳኝ ነው!

ምናልባት ርቄ እየሄድኩ እንደ ሆነ ታስቡ ይሆናል። ምናልባትም፣ ኦፖ ያ ጥሩ የስብከት ምሳሌ ሊሆን ይችል ይሆናል፣ ጉዳዩን እያጋነንከው መሆኑን መረዳት ግን አይከብደኝም ትሉኝም ይሆናል። ስታዩት ግን፣ ስለ ኦፒየም እንደምትናገሩት ሁሉ ከዓለም በስተ ጀርባም ሰዎችን ለማሳትና ለመማረክ የታቀደ ክፉ ኀይል መኖሩን ትናገራላችሁ። ለዚህ ዓለም እውነተኛ ባሕርይ ዐይናቸው የተከፈተላ



ቸው ሰዎች፣ በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ነገር ሲነኩ በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ፣ ያለ ማቋረጥ ወደ ጌታ እየተመለከቱ መሆን እንዳለበት ይረዳሉ። በማንኛውም ቅጽበት በሰይጣን ማደናገሪያ ሊጠመዱ እንደሚችሉም ያውቃሉ። ልክ በመጀመሪያ በሽታን ለማስታገሥ በደስታ የምንቀበለው ድራግ ራሱ በመጨረሻ የበሽታ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ሁሉ፣ በጌታ ሥልጣን ሥር በተገቢ ሁኔታ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው የዓለም ነገሮችም፣ ጥንቃቄ ከጐደለን የውድቀታችን ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን በሚመስሉ ሁኔታዎች ውስጥ ግድየለሾች መሆን የሚችሉት ሞኞች ብቻ ናቸው።

መጥምቁ ዮሐንስን በቅናት ብንመለከተው አያስደንቅም! ልክ እንደ እርሱ ሰላም ወደ ሆነ ስፍራ ገለል ለማለት ማሰብ በጣም ቀላል ነው! እኛ ግን እንደ እርሱ አይደለንም። ጌታችን ወደ ዓለም የላከን የራሱን ዱካ እንድንከተል ነው - "እየበላንና እየጠጣን"። እግዚአብሔር ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ" በማለት የእርሱን መልካም ዜና እንድናውጅ ትእዛዝ ሰጥቶናል፣ በእርግጥም "ሁሉ" የሚለው ቃል በየዕለቱ ትከሻ ለትከሻ ስንገፋፋ የምንውላቸውን ሰዎችም ያካትታል።

ስለዚህ እዚህ ጋ ከበድ ያለ ችግር ያጋጥመናል። ከዚህ በፊትም እንደተነጋገርነው፣ ገደብ መኖር አለበት። ምናልባት እግዚአብሔር የሆነ ቦታ ላይ የወሰን መስመር አስምሮ ሊሆን ይችላል። በዚያ መስመር ውስጥ ቁዩ፣ ደኅና ትሆናላችሁ፣ ከጣሳችሁት ግን ከባድ አደጋ ያጋጥማችኋል። ታዲያ መስመሩ የት ነው ያለው? መብላትና መጠጣት፣ ማግባትና ልጆችን ማሳደግ፣ መነገድና መልፋት አለብን። ታዲያ እነዚህን ሁሉ እያደረግን እንዴት ሳንመረዝ እንቀራለን? እግዚአብሔር ልጁን እስኪሰጣቸው ድረስ ከወደዳቸው ወንዶችና ሴቶች ጋር በነጻነት እየተቀላቀልን፣ የዓለም ፍንጣቂ እንዳይደርስብን ራሳችንን የምንጠብቀው እንዴት ነው?

ጌታ በአንድ ወር ውስጥ ምን ያህል መግዛትና መሸጥ እንዳለብን ገደብ አበጅቶ ቢሆን፣ እንዴት በቀለለ! ሕጉቹ ማንም እንዲከተላቸው ግልጽ ይሆኑ ነበር። በወር ውስጥ ከዚያ ከተወሰነው ፍጆታ በላይ የሚያጠፉ ክርስቲያኖች ዓለማዊ ክርስቲያን ሲሆኑ፣ ከዚያ ፍጆታ በታች የሚያጠፉ ሁሉ ዓለማዊ-ያልሆኑ በሆኑ ነበር።

ጌታ ግን ምንም ዐይነት አኀዝ እንዲኖር ስላላስቀመጠ፣ በእርሱ ላይ ያለ ማቋረጥ እንደገፋለን። ለምን? መልሱ በጣም ድንቅ እንደ ሆነ አስባለሁ። በሕግና ደንብ እንዳንታሰር፣ ሁልጊዜም በሌላ ዐይነት ድንበር ውስጥ እንድንቆይ ነው - በእርሱ ሕይወት ድንበር ውስጥ። ጌታ የምንከታተላቸውን ሕጉችና ደንቦች ሰጥቶን ቢሆን ኖሮ፣

በእነዚህ ለመኖር በጣም ጥንቃቄ በወሰድን ነበር። በእርግጥም የተሰጠን ሥራ በጣም ቀላልና የማያውክ ነው - ይህም በራሱ በጌታ ውስጥ መኖር ነው። ያኔ ሕጉን መጠበቅ እንችላለን። አሁን የሚያስፈልገን ከእርሱ ጋር በኅብረት መቆየት ብቻ ነው። የዚህም ደስታ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት የምንኖር ከሆነ በልባችን ያለው የእርሱ ቅዱስ መንፈስ ገደቡ ጋ መድረሳችንን ሁልጊዜም መንገሩ ነው!

ቀደም ብለን የክርስቶስ ተቃዋሚው መንግሥት በቅርብ እንደሚገለጥ ተነጋግረናል። ዮሐንስ በመልእክቱ "ልጆች ሆይ" ብሎ በመጀመር፣ ስለ ዓለምና በዓለም ስላሉት ነገሮች ሲጽፍ (1ዮሐ. 2÷15)፣ "የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል" (ቍጥር 18) እያለ ያስጠነቅቃቸዋል። የተጋፈጡት ከእነዚህ እና ከዚህ በተጨማሪ ውስጥ ውስጡን በድብቅ ለጥፋት ከሚሠራ "የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል÷ አሁንም እንኳ በዓለም አለ" (4÷3)፣ ታዲያ ምን ማድረግ አለባቸው? በዚህ አቅማቸው የቱ እውነት፣ የቱ ውሸት መሆኑንስ እንዴት ያውቃሉ? የትኛው መሬት ሲራመዱበት ከዳተኛ፣ የትኛው ደግሞ አስተማማኝ መሆኑንስ እንዴት መናገር ይችላሉ?

ዮሐንስ የሰጣቸው መልስ በጣም ቀላል በመሆኑ ዛሬ እኛ እንኳ ልናምነው እንፈራለን። "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል÷ ሁሉንም ታውቃላችሁ። ... እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል÷ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ÷ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ÷ እናንተንም እንዳስተማራችሁ÷ በእርሱ ኑሩ" (2÷20፣27)። ይህ ዓለምን ስለሚወቅሰውና ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ቃል ስለ ገባላቸው የእውነት መንፈስ በተዘዋዋሪ የሚናገር ነው (ዮሐ. 16÷8፣13)።

በተሰጠን በማንኛውም ምሳሌ ውስጥ፣ ጥሰናቸው መሄድ የሌለብንና ለእግዚአብሔርም የታወቁ አስተማማኝ ድንበሮች መኖር አለባቸው። እንድናያቸው በመሬቱ ላይ የተሰመሩ ባይሆኑም፣ አንድ ነገር ግን እርግጠኞች ነን፣ አጽናኙ በደንብ ያውቃቸዋል፣ ምናልባት ሰይጣንም ያውቃቸው ይሆናል። ታዲያ እርሱን ልናምነው አንችልም? የሆነ ቦታ ላይ ልንጥሳቸው ስንል፣ እርሱ በውስጣችን ይህን እውነታ እንድናስተውል እንደሚያደርገን ዐውቀን አንደገፍበትም?

በ1 ቆሮንቶስ 7 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ምሪት አቅርቦልናል። "ዳሩ ግን ÷ ወንድሞች ሆይ÷ ይህን እናገራለሁ፤ ዘመኑ አጭር ሆኖአል ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸው እንደሌላቸው ይሁኑ÷ የሚያለቅሱም እንደማያለቅሱ÷ ደስ የሚላቸውም ደስ እንደማይላቸው÷ የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው÷ በዚችም ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙባት ይሁኑ፤ የዚች ዓለም መልክ ዐላፊ ነውና። ነገር ግን ያለ አሳብ (ያለ ጭንቀት) ልትኖሩ እወዳለሁ" (ቍጥር 29-32)። እዚህ ላይ ብዙ ነገሮች ተዳስሰዋል፣ በሁሉም ውስጥ ገንኖ የሚታየው የበላይ ሁናቴ ግን "ዘመኑ አጭር ነው" የሚለው ነው። እየኖርን ያለነው ይላል ሐዋርያው፣ የተለየ ጫና ባለባቸው ቀናት ውስጥ በመሆኑ፣ በእንደዚህ ዐይነቶቹ ቀናት ልንመራበት የሚገባን መመሪያ "... ያሉአቸው እንደ ሌላቸው ይሁኑ" የሚለው ነው።

ጳውሎስ ከራሱ ጋር ይጣረሳል እንዴ? ብለን እንደነቃለን። ባሎች ሚስቶቻቸውን፣ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከወደደበት በማያንስ ፍጹም ፍቅር እንዲወዱ በኤፌሶን 5 ውስጥ ሲመክር ነበር። እዚህ ግን ጭራሹኑ ሚስቶች እንደሌሏቸው እንዲኖሩ ይነግራቸዋል! እንደ ዚህ ዐይነቶቹን ተቃርኖዎች በአንዴና በተመሳሳይ ጊዜ ማስታረቅ ይጠበቅብናል ማለት ነው? በማለት በቅሬታ እንናገራለን።

ይህ ዐይነቱ አያም ሕይወት፣ ክርስቲያን ብቻ እንጂ ሌላ ማንም ሊኖረው የሚችለው እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። "እንደ ሌላቸው" የሚለው አባባል ምናልባት ፍንጭ ይሰጠናል። ጉዳዩ ውስጣዊ ጉዳይ፣ የልብ ታማኝነት ጥያቄ መሆኑን ይገልጣል። በክርስቶስ፣ ውጫዊ የባሕርይ ለውጥ ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ውስጣዊ ነጻ መውጣትም አለ። እነዚህ ነገሮች ኖረዋቸው በኤፌሶን 5 ውስጥ እየተደሰቱ፤ ነገር ግን በያዙት ነገር ባለመታሰራቸው በ1 ቆሮንቶስ ውስጥም በእኩል ሁኔታ ይደሰታሉ። "የያዙትን" ነገር ሳይቃወሙ፣ የዓለም ከሆነው ሁሉን ነገር በእጅ የማድረግ አባዜ በመንፈስ ነጻ ስለ ወጡ "እንደሌላቸው" መኖር ይችላሉ።

ተፈጥሯዊ ሰው በአንደኛው ጽንፍ ወይም በሌላኛው ጽንፍ - እነዚህ ነገሮች ኖረውት፣ ባለው ነገር ሙሉ በሙሉ ተውጦ፣ ወይም ሃይማኖተኛ ከሆነ ደግሞ ከእንግዲህ በኋላ ምንም ነገር ሳያሳስበው እንዲኖር፣ ያለውን ነገር በሙሉ በማስወገድ ይኖራል። የክርስቲያን መንገድ ግን ከተፈጥሯዊው መንገድ በጣም የተለየ ነው። ችግሩን ለመፍታት ክርስቲያናዊው መንገድ ነገሩን በማስወገድ ሳይሆን፣ ልብን ከዚያ ነገር ይዞታ ነጻ በማውጣት ነው። ሚስትም ሆነች ለሚስት ያለን የፍቅር ስሜት አይወገድም፣ ነገር ግን ባልና ሚስት ይህ ስሜት ከሚያሳድረው ብርቱ ተጽዕኖ ነጻ ወጥተዋል። እንዲሁም የልቅሶው ሰበብ አልተወገደም፣ ሕይወቱ ግን በዚያ ችግር እየተገዛ አይደለም።

የደስታው ምክንያት አሁንም አለ፣ ነገር ግን የዚህ ደስታ መነሻ የሆነውን ነገር እንዳንተወው የሚቃወም ውስጣዊ ቍጥጥርም አለ። መጓዛትና መሸጥ እንደ በፊቱ ይቀጥላሉ፣ ነገር ግን በእነርሱ ላይ ያለንን ግላዊ ትስስር ውስጣዊው ነጻነት ፈትቶታል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ አሉን፣ ነገር ግን ያለን "እንደሌላቸው" ነው።

እንደ ዮሐንስ የኢየሱስን ምስክርነት በምድር ላይ ለማስከበር ያለንን ምኞት አንዳንዴ ስንናገር እንገኛለን። ምስክርነቱ የተመሠረተው፣ እኛ ስለዚህና ስለዚያ ልንናገር በምንችለው ላይ ሳይሆን፣ ሰይጣን *ስለ* እኛ ሊናገር በሚችለው ላይ መሆኑን እናስታውስ። እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ አስቀምጦናል - ብዙ ጊዜም በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ስፍራዎች ውስጥ እንድንኖር ስለሚያደርገን ዓለማዊነት ከክርስቲያኖች ይልቅ የተሻለ ጊዜ እንዳለው እስኪመስለን ድረስ ይፈትነናል። ይህም የሚሆነው ክርስቲያኖች በእርግጥም በተፈጥሮ የእነርሱ ባልሆነው ስፍራ የሚኖሩ እንግዶች በመሆናቸው ነው። አንድ ዋናተኛ ወደ ባሕር ጠልቆ ይገባ ይሆናል፣ ነገር ግን ለዋና የሚሆኑ የተለዩ አልባሳትን ካልተጠቀመና የራሱ ከሆነው፣ ከውጭኛው ዓለም የሚመጣ አየር ካላገኘ በዚያ መቈየት አይችልም። ጫናው ከፍተኛ በመሆኑ የግድ ከራሱ ዓለም አየር መተንፈስ አለበት። የሚሠራው ሥራ እስኪጠናቀቅና በዙሪያው ያለውን ውሃ የሚያሸንፍበት ኀይል እስከቀረበለት ድረስ፣ በዚያው ጥልቅ ባሕር ውስጥ ይቈያል፣ ነገር ግን እርሱ የዚያ አካል አይደለም፣ *ውሃውም በእርሱ ውስጥ ድርሻ የለውም*።

እንዲሁም ከዓለም ጋር ያለን ንክኪ በየትኛውም ዐይነት ውጫዊ የድርጊት ለውጥ መፍትሔ አያገኝም። አንዳንዶች እኛ ባለንበት በእንደዚህ ዐይነቱ ጊዜ፣ ለወደፊት - ለሚመጡት ቀናት የሚሆን ነገር አለማዘጋጀት የመንፈሳዊነት ምልክት እንደ ሆነ ያስባሉ። ያ ግን ጅልነት እንጂ መንፈሳዊነት አይደለም። በምናዘጋጀው ነገር ምን እንደምናደርግ በመጨረሻው ምዕራፋችን የምንመለከተው ጥያቄ ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን ዓለምን መጠቀም እንዳለብን ግልጽ አድርጎልናል። አዎ፣ መብላትና መጠጣት፣ መነገድና ሰብል ማብቀል፣ መደሰት፣ ካስፈለገም ማልቀስ አለብን፣ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እስከ አፍንጫቸው መጠቀም አይኖርብንም። ከዓለም ጋር በሚኖሩን ግንኙነቶች በሙሉ የሚያሠጋን ምን እንደ ሆነ ተምረናል። ስለዚህ አጽናፙ የሚከለክለንን በእርጋታ እያስተዋልን፣ በጥንቃቄ እንድንነግድ መማራችንም ምንም አያስደንቀንም።

ኢየሱስ "ከላይ" መጥቶአል። እናም "የዚህ ዓለም ገዥ ... በእኔ ላይም አንዳች የለውም" ብሎ ያለ ፍርሀት መናገር ይችላል። የወሰን መስመሩ የተሰመረው በምድር ላይ በእግሩ ሥር ሳይሆን፣ በገዛ ልቡ ውስጥ ነው። እንደዚሁም በዚህ ምድር ውስጥ፣ "ከላይ" የሆነ የማንኛውም ነገር ደኅንነት ልክ እንደ እርሱ የተጠበቀ ነው። ከዚህ ዓለም ውጭ የሚመጣውን አየር የምንቀበልበትን ቱቦ የሚቈጣጠረው ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ከላይ የሆነው ሕይወት፣ ለዚህ ለታች የሚሆነውን ድጋፍ የሚያገኘውና የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ የሚቀርብለትም *በእርሱ* ነው። ስለዚህ አንድ ነገር መንፈሳዊና "የእግዚአብሔር" ከሆነ፣ ልንጨነቅለትም ሆነ ለደኅንነቱ ልንከራከርለት ወደ እለ ማስፈለጉ እንመጣለን። "*መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ... ሎሌ ዎቼ ይዋጉልኝ ነበር*" (ዮሐ. 18÷36)። ነገር ግን አያስፈልጋቸውም።

እግዚአብሔር ስለ እኛ አይሠጋም፣ ምክንያቱም ስለ ቅዱስ መንፈሱ ስለማይጨነቅ ነው። መንፈሳዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ሕይወት መሆኑ እውነት የመሆኑን ያህል፣ መንፈሳዊ ሕይወት ሊሸነፍ የሚችለው እግዚአብሔር ራሱ ለመሸነፍ ሲችል ብቻ ነውና ዝቅተኛ ደረጃ ያለው መንፈሳዊ ሕይወት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። እግዚአብሔር ስለ እዚህ እውነታ አይከራከርም። ይህን ነገር በውስጣችን እንዲያረጋግጥልን ለአጽናፙ ሲተውለት ያለ ቅሬታ ነው። "ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና" (1ዮሐ. 4÷4)።

እንደገናም፣ ዓለምም በሞላው በክፉው እቅፍ የተያዘ እንደ ሆነ የሚነግረን ያው ቍጥር - እኛ "ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን" አንድ ጊዜ ደግሞ ያረጋግጥልናል (1ዮሐ. 5÷19)። *እኛ ከእግዚአብሔር ነን!* ከዚህ የሚበልጥ፣ ያንን አስቀያሚ እውነት የሚስተካከልና የሚያሸንፍ ሌላ የተባረከ እውነት ማግኘት እንችላለንን? በኢየሱስ ስም የሚያምኑ ሁሉ፣ "ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" (ዮሐ. 1÷13)። ከእግዚአብሔር በመወለዳችንም ምክንያት ክፉው ሊነካን አይችልምና (1ዮሐ. 5+18) እግዚአብሔር ይመስገን!

በቀላሉ፣ የሰይጣን ኀይል በዓለም ውስጥ በሁሉ ስፍራ መገኘቱን ተረዱ። ግና ወንዶችና ሴቶች በመንፈስ ሲመላለሱና ከእግዚአብሔር ለተቀበሉት ቅባት ትኩረታቸውን በደንብ ከሰጡ፣ ያ ክፉ ኀይል ይተንናል። የሰይጣን የማዘዣ ወረቀት ሊሠራ የማይችልበት በራሱ በእግዚአብሔር መገኘት (ሀልዎት) የተሰመረ ድንበር *አለ*። እግዚአብሔር ሁሉን ስፍራ ለራሱ ከያዘው፣ ለክፉው ምን ክፍል ይቀርለታል?

እንደዚህ በግልጽ ከእግዚአብሔር ነን? ሰይጣን፣ "ያንን ሰው ላጠምደው አልቻልኩም!" ብሎ ስለ እኔና ስለ እናንተ ይመሰክራል?

## ምዕራፍ ዐሥር

## ሊመጣ ያለው ዘመን ኀይሎች

የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ክርስቲያኖች ሲናገር “ሊመጣ ያለውን የዓለም ኀይል የቀመሱትን” (ዕብ. 6÷5) ሲል ምን ማለቱ ነው? በጉጉት የምንጠብቀው አስደናቂ የወደፊት ዘመን በመኖሩ ላይ መቼም ሁላችንም እንስማማለን። አሁን ከእግዚአብሔር መንፈስ የኀይል ሥራ አኳያ ወደ እኛ የደረሰችው መንግሥቱ (ማቴ. 12÷28)፣ ያን ጊዜ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የምትታይና የማይቋቋሙአት ትሆናለች። የዓለም መንግሥትም የአምላካችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ይሆናል (ራእይ 11÷15)። ነገር ግን እነዚህ አሁን የምንቀምሳቸው ብቻ እንጂ በደንብ በዓል የማናደርግባቸው “ኀይሎች” ምንድን ናቸው? ብለን እንደነቅ ይሆናል። መቅመስ የሚለው ቃል የሚያሳየው፣ ሊታሰብበትና ሊተነተን የሚገባውን ትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ በግል ተለማምደነው የራሳችን ስለምናደርገውም ነገር በመሆኑ፣ እነዚህ ኀይሎች የምንቀበላቸውና የምንደሰትባቸው እንደ ሆኑ ግልጽ ነው። ደግሞም፣ ብዙ ልንከተለው የሚገባ ነገር እያለው፣ ጥቂት ብቻ የበላንለት ድግስ የመጀመሪያ ደረጃ ናቸው።

ቃለ እግዚአብሔር ገና እንደሚመጡ የሚጠብቃቸውን እንደ ዚህ ዐይነት በርካታ ነገሮች መዘርዘር እንችላለን። ገና በመጨረሻው ዘመን የሚገለጥ ደኅንነት አለ (1ጴጥ. 1÷5)። በሚመጣው ዓለም አዲስ የዘላለም ሕይወት አቅጣጫ አለ (ሉቃ. 18÷30)። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የቀረ ዕረፍት አለ (ዕብ. 4÷9)። የሟች ሰውነታችን መነሣትና መታደስ ይኖራል (ሮሜ 8÷23፤ 1ቆሮ. 15÷44)። ሰዎችን የሚያስና ክል ነገር በሙሉ የሚወገድበት ቀን ይኖራል (ኤር. 31÷9፤ ኢሳ. 57÷14፤ 62÷10)። ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር በእግዚአብሔር ክብር ዕውቀት ስትሞላ (ኢሳ. 11÷9፤ ዕንባ. 2÷14)፣ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ፣ ሁሉም ጌታን የሚያውቁበት ጊዜ ይመጣል (ኤር. 31÷34፤ ዕብ. 8÷11)። እነዚህን ነገሮች በሙሉ በክርስቶስ ውስጥ አሁን ቅምሻቸውን አግኝተናል፣ ነገር ግን እስካሁን በሙላት አላየናቸውም።

የሚከተሉት አሳቦች አሁን ከምናካሂደው ጥናት ጋር ይበልጥ በቀጥታ ይያያዛሉ። የዕብራውያን መልእክት፣ በመዝሙር 8 ላይ የተጠቀሰውን፣ “ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት” የሚለውን ቃል ከጌታ ኢየሱስ ጋር ያገናኝና ቀጠል አድርጎም “አሁን ግን ሁሉ እንደ



ተገዛለት ገና አናይም” (ዕብ. 2÷8) በማለት ልንቀበለው የምንገደድበትን ልምምድ በፍጹም ግልጽነት ያሳያል። ከእነዚህ ሁለት የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ጐን ደግሞ በሉቃስ 10÷19 ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ “በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን” የሰጠበትን ዐረፍተ ነገር በተጓዳኝ ማስቀመጥ አለብን። በእርግጥ ይህም እስከ አሁን ያላየነውን የወደፊቱን ቀን፣ አሁን *በቅምሻ* እንድናገኘው ተስፋ ይሰጠናል።

እንደገናም በዚያው የወንጌል ንባብ ውስጥ ኢየሱስ፣ “ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ” ብሎ መናገሩ ተዘግቦአል (10÷18)። ይህን ድርጊት ዮሐንስ በራእይ 12÷9 ውስጥ ገና ወደ ፊት የሚፈጸም መሆኑን በርቀት ያስቀመጠው ይመስላል። ኢየሱስ ግን ከመስካሪዋ ቤተ ክርስቲያን ማዕዘን ሲያየው፣ ይህ በተወሰነ ደረጃ ነባራዊ ተጨባጭ እውነታ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። በተጨማሪም፣ ሰይጣን ለአንድ ሺህ ዓመት እንደሚታሰር ዮሐንስ በራእይ የመጨረሻ ምዕራፎች በአንዱ ውስጥ አይቶአል (20÷1-4)። ኢየሱስ ደግሞ “ኀይለኛው ሰው” ስለ ታሰረ፣ አሁን ወደ ቤቱ ጥሰን በመግባት ልንበዘብዝ ስለ መቻላችን (ማቴ. 12÷29) ይናገራል።

እነዚህ ትልቅ ቁምነገር ያዘሉ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው። አሁን ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት ካለን (ይህ ደግሞ የተረጋገጠ ነው)፣ ቀሪ ምቹን እነዚህን የወደፊት “ኀይሎች” ቅምሻ እናውቃለን። እስካሁን በአጽናፍ አቀፋዊነት ባይገለጡም፣ የክርስቶስ ትንሣኤ ፍሬ በመሆናቸው፣ በመርሕ ደረጃም ቢሆን፣ የቤተ ክርስቲያን የአሁን ጊዜ ንብረት ናቸው።

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ከሰው ጋር የተሳሰረ ነው። “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር” አለና “ ... ይግዙ” አለ። ሰው ኀይልን እንዲጠቀም፣ ሌሎች የተፈጠሩ ነገሮችን እንዲገዛ፣ እንዲያስተዳድርና እንዲቈጣጠር እግዚአብሔር አሰበ። መዋጀት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው - ወይም የዕቅዱ ክፍል ነው ማለት አንችልም - ምክንያቱም ሰው እንኳን መጥፋቱ፣ መውደቁ እንኳ ፈጽሞ አልታሰበም ነበር። ዘፍጥረት 3ም የሰውን ታሪክ እንጂ እግዚአብሔር ስለ ሰው የነበረውን ዕቅድ አይወክልም። አንድ ሠራተኛ በግንባታ ላይ ካለ አምስተኛ ፎቅ ሕንፃ ላይ ሊወድቅ ይችላል፤ ያ ግን ፈጽሞ በሕንፃው መሀንዲስ ዕቅድ ውስጥ የነበረ ሊሆን አይችልም!

አይደለም፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ የሚያያዘው ከሰው ገዥነት ጋር ሲሆን፣ በተለይም ይህ የሚያካትተው ክልል “ምድርን ሁሉ” (ዘፍ. 1÷26) ተብሎ እንደ ተጠቀሰ ልብ ማለት ያሻል። ሰማይ ችግር

የላትም፣ ችግሩ እዚህ መሬት ላይ ነው። ሰዎች "ግዙአት" ተብሉ ተነግሮአቸዋል (ቍጥር 28)፣ ስለዚህ፣ እኛም ለምን? ብለን እንጠይቃለን። መገዛት ያለበት ኀይል ከሌለ ይህ ለምን አስፈለገ? ከዚህም በላይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሰውን ወስዶ፣ ያበጃትና "ይጠብቃትም" ዘንድ በዔድን ገነት እንዳኖረው ተነግሮናል (2÷15)። እዚህ ጋ የተጠመበት ቃል፣ "ለመጠበቅ" ከሚውለው የተለመደው የዕብራይስጥ ቃል የላቀ ነው። አዳም የእግዚአብሔርን ገነት መጠበቅ አለበት፣ እንደገናም ይህ በውጭ ሊጠበቅ የሚገባውን የጠላትን ቅርበት ያሳያል።

የዘፍጥረት 1÷26 ን አገላለጽ ልብ ማለቱ በብዙ ይጠቅማል። ሰው "ምድርን ሁሉ" ለመግዛት ሥልጣን ተሰጥቶታል፣ ይህም ሐረግ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ "በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ" የሚያካትትና ሰፋ ያለ ነው። ነገር ግን ከታሪኩ ውስጥ እንደምናነበው፣ ሰው ሊቈጣጠረው ያልቻለው የመጀመሪያው ነገር በምድር ላይ የሚንቀሳቀስ ነገር - ትል ነበር። በሰው ውድቀትም ሰይጣን፣ በአዲስ መንገድ በሰው በራሱ ውስጥ፣ በምድር ላይ ሕጋዊ መብት አገኘ። የምድር ዐፈር የእርሱ ግዛት የበታች ክልል መሆኑ እውነት ነው። "በሆድህም ትሄዳለህ፥ ዐፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ" (3÷14)። ግና ዐፈር ምንድን ነው? ዐፈር፣ አዳም የተሠራበት ንጥረ ነገር ነው! ስለዚህ አሁን ሰው በሥጋ ኀሊ በሞራል የሰይጣን ተገዥ ነው። የእግዚአብሔር ጠላት፣ በተፈጥሯዊ ልደት የሰው የሆነውን ነገር እና ሰውንም ጭምር ለራሱ የሚያደርግበትን ግልጽ ማዕረግ አረጋግጦአል። ተፈጥሯዊው የሰው ሕይወት እዚህ ምድር ላይ የሰይጣን እንቅስቃሴ መረጋገጫ ነው። የሰይጣን ዓለም የሚመነጨውና ጥንካሬውን የሚያገኘው በሰው ውስጥ ካለው መብቱ ሲሆን፣ እነዚህን መብቶቹን እግዚአብሔር እንኳ አልከለከለውም። የአሮጌው ፍጥረት በሆኑት ነገሮች ሁሉ ላይ፣ በአዳም ውድቀት ምክንያት ሙሉ ሥልጣን አግኝቶአል።

ሰይጣን በእኛ ውስጥ መሥራቱን ማቆም ካለበት፣ በውስጣችን ያለው መንደርደሪያው (መሬቱ) ከእርሱ መወሰድ አለበት። ስለዚህ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመዋጀት አስተካከለ - ከሰይጣን ጋር በቀጥታ በመገናኘት ሳይሆን፣ አስቀድመን እንዳየነው፣ የአሮጌው ፍጥረት የሆነውን ነገር በሙሉ - ራሱን ሰውን፣ ዓለሙንና እያንዳንዱን ነገር - ከመንገድ በመጥረግ፣ የሰይጣንን ሕጋዊ መቆሚያ አስወገደው። የሰይጣን ግልበጣ የተከናወነው በእርሱ ላይ በተነጣጠረ ቀጥተኛ ምት ሳይሆን፣ የመቈጣጠር ሕጋዊ መብት የሚሰጠውን ነገር በሙሉ በክርስቶስ ሞት በተዘዋዋሪ በማስወገድ ነው። "ከእንግዲህስ ወዲያ ለኀጢአት እንዳንገዛ የኀጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን " (ሮሜ 6÷6)።



ስለዚህ እግዚአብሔር ይመስገን፣ ሰይጣን ከእንግዲህ በእኛ ላይ ምንም መብት የለውም። ይህ ግን አሉታዊ እውነት ብቻ ነው። አዎንታዊም ደግሞ አለ። አሮጌውን ፍጥረት በማስወገድ፣ እግዚአብሔር በዘላለም ዕቅዱ መንገድ ላይ የተገተሩትን በሙሉ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን፣ አዲስ ፍጥረት - አዲሱን ሰው በማምጣት ያንን ዕቅድ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነውን ነገር በሙሉ አመቻችቶአል። "ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአልና፣ ዳግመኛ እንደማይሞት እናውቃለንና፤ ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጉልበት አይኖረውም" (ቍጥር 9 - አ.መ.ት)። በዘፍጥረት 1 የተገለጠውና በዘፍጥረት 3 የጠፋው ዕቅድ፣ የጠፋው ለመልካም አይደለም። እግዚአብሔር በመጀመሪያው ሰው ውስጥ ሲያረጋግጠው ያልቻለውን በሁለተኛው ውስጥ አግኝቶአል፣ ያም ሁለተኛ ሰው በዘፋን ላይ ነው። ስለዚህ የአዲስ ኪዳኑ ጸሐፊ፣ "ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ወይስ ትጐበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?" በማለት፣ የመዝሙረኛውን ቃል በድጋሚ ለመጠቀም መድፈሩ አያስደንቀንም። በዚህ ሁኔታ ከመዝሙረ ዳዊት ሲጠቅስ ይቈይና "ኢየሱስን ... ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን!" - እያለ በደስታ ይናገራል (መዝ. 8÷4-6፣ ዕብ. 2÷6-9)። የሰው ልጅ መፈጠር የእግዚአብሔርን ፍላጐት እንዲያሟላ ታስቦ ከሆነ፣ ያ ፍላጐት አሁን ተሳክቶአል። እግዚአብሔር የራሱን ሰው አግኝቶአል።

ስለዚህ ዘፍጥረት 1፣ መዝሙረ ዳዊት 8 እና ዕብራውያን 2 በልዩ ሁኔታ የተጋመዱ ናቸው። በእርግጥ መዝመር 8 እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ስላለው ዕቅድ በግጥም የቀረበ ዝማሬ ሲሆን፣ የሚገርመው ግን መዝሙረኛው ውድቀትን ለማመልከት ከመስመር አለመውጣቱ ነው። "በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው" እያለ የዘፍጥረት 1ን የመጀመሪያ ዕቅድ ብቻ ያስረግጥ ነበር። ዕቅዱ አልተለወጠም። ማኅሌቱን የጀመረው ብቻ ሳይሆን፣ የጨረሰውም በአድናቆት ምስጋና ነው - "ስምህ በመላው ዓለም ምንኛ የገነነ ነው!" (ሕያው ቃል)።

ጠላት፣ የሚችለውን በጣም የከፋ ነገር አድርጎአል፤ ሰው እግዚአብሔርን ለመሳደብ እስኪደፍር ድረስ ተጠምዶአል፣ እናም ይህን መዝሙር የጻፍነው እናንተና እኔ ብንሆን ኖሮ፣ "ነገር ግን ወይኔ! ሰው ወድቆአል፤ ሁሉ ጠፍቶአል!" የሚል የሐዘን ጩኸት ከስምንተኛው ቍጥር በኋላ ማስከተላችን አይቀሬ ነበር። መዝሙረኛው ግን እንዲህ አላደረገም። ውድቀትን ሙሉ በሙሉ የረሳው ይመስላል፣ በተዘዋዋሪ እንኳ አላወሳውም። በአሳቡ፣ የመዋጀትን ጠቅላላ ታሪክ ይዘልና "ምንኛ የገነነ ነው!" ብሎ እንደገና ይጮኻል። አዳምና ሔዋን ሊወድቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሰው በመጨረሻ የሰይጣንን ኀይል መገል

በጥ እንዳለበት የእግዚአብሔርን ዕቅድ መለወጥ አልቻሉም። ዕቅዱ ሳይ ለወጥ ጸንቶአልና ይህ ገናናነት የታወቀ ይሆናል - የት? በምድር ሁሉ።

ይህም ዕቅድ የተፈጸመው በሰው ልጅ (በኢየሱስ) ውስጥ ብቻ አይደለም፣ በሰዎች ልጆችም - እግዚአብሔር ወደ ክብር በሚያመ ጣቸው "ብዙ ልጆች" ውስጥም እንጂ። መዝሙረኛው ይህንን እውነት ሲያሰምርበት በጭንቅ ነው። ጠላት እጅግ የከፋ ነገር ቢያደርግም፣ በውድቀት ምክንያት ያገኛቸው መብቶች የማይነጠቁ መሆናቸው አል ተረጋገጠም። ከሰዎች መካከል እንኳ ሊነካቸው ያልቻላቸው አሉ። "ከልጆችና ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣ (ብርታትን) አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፤ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ" (ቍጥር 2 - አ.መ.ት)። እግዚአብሔር በትልልቅ ወታደራዊ መሪዎች አልተደገፈም። ሕፃናት ልጆች፣ አዎን በጣም ሕፃናት የሆኑ፣ የጠላቶቹን ሰራዊት ጸጥ ለማሰኘት በቂ ናቸው።

እስካሁን እንዳየነው፣ ዕብራውያን 2 መነሻ አሳቡን ያገኘው ከመዝሙረ ዳዊት ነው። ተጨማሪ እርምጃ ግን ሄዶአል። በፍጥረት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ዕቅድና ዕቅዱ የሚጠቁመውን ግብ ዳግም እያረጋገጠ፣ ከዚህም የበለጠ አድርጎአል። የወደቀውን ሰው የጨለመ የታሪክ ሂደት ዞር ብሉ በማስተዋል እየተመለከተ፣ ያ በመዋጀትና በማደስ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ዕቅድ፣ ወደዚያው መጀመሪያም ወደ ነበረው ፍጻሜ የሚያመራ መሆኑን ያረጋግጣል። ያ መዋጀት የፈጠራቸው አዳዲስ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ ዕቅዱ አልተለ ወጠም። እግዚአብሔር ግቡን አልተወም። ከዚህም በላይ፣ ከመስቀሉ ድል መንሣት ባሻገር፣ የመዝሙረኛውን የእምነት ማረጋገጫ እርሱም በልበ ሙሉነት በድጋሚ ማጽናት ይችላል። ስለዚህ ሁሉ መጥፋቱን ከመናገር ይልቅ፣ ፍጻሜው በክርስቶስ ውስጥ አስተማማኝ መደረጉን መናገር እውነት ይሆናል።

አዎን፣ ዕቅዱ ያው ራሱ ነው፣ "ያልተገዛለት ምንም አልተወ ምና" (ቍጥር 8)። የሚታየው ግን ይህን የሚክድ ይመስላል፣ ስለዚህ "ሁሉ እንደ ተገዛለት ገና አናይም"። ይህ እውነት ቢሆንም፣ ጸሐፊው ቸል ይለውና "ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፥ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን" (ቍጥር 9) እያለ በአንድ ጊዜ በድል አድራጊነት ስሜት ይቀጥላል። ይኸውም "ዲያቢሉስን ... እንዲደመስስ ነው" (ቍጥር 14 - አ.መ.ት) ብሉ ይጨምርበታል።

ሰው በምድር ላይ ለእግዚአብሔር ማድረግ የነበረበትንና ያቃተ ውን ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አከናውኖለታል። እርሱ "ስለ ነገር



ሁሉ ሞትን ቀምሶአል" (የመጀመሪያው ግሪክኛው የሚያሳየው - "ስለ ሰው ሁሉ"ን አይደለም)። ማለትም፣ ሰውን ለመዋጀት ብቻ ሳይሆን የሞተው፣ የፍጥረት ለሆነው ነገር ሁሉ ነው። በተጨማሪም ሰይጣናዊ ውን የዓለም ሥርዐት ጠቅልሉ ለመገልበጥ፣ የአብን ዕቅድ ወደ ኋላ ተጉዞ እንደገና ለማግኘት ነው።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በዲያብሉስ ግዛት ውስጥ የክርስ ቶስን ድል መንሣት የማሳወቅ ግልጽ ኀላፊነት አለባት። እናም ይህ ለኀይላትና ለሥልጣናት ምስክር የሚሆን ከሆነና የክርስቶስ ሉዐላዊነት በመስቀሉ በኩል በመንፈሳዊው ክልል ውስጥ መዘገብ ካለበት፣ "እስመሳዩ" በልባችን ውስጥ ያለው ሕጋዊ መረጋገጫ በዚያው መስቀል ከትውልዱ ውስጥ ሲወገድና ሲካድ ብቻ ነው ይህ ሊሆን የሚችለው። ምክንያቱም አሁንም የእግዚአብሔር ዓላማ ሰው "ገዥ" እንዲሆን ነው። ለእርሱ የምናደርገው ሥራም የዘፍጥረት 3ን ውጤት ለማፍረስ የታቀደውን ወንጌል በማወጅ አያበቃም። እግዚአ ብሔር ወደ ዘፍጥረት 1 እንደገና ሊወስደን ይፈልጋል። በዚያም በሚታየው ጠላቱ ላይ በክርስቶስ ሆነን ሞራላዊ የበላይነትን እንድ ንይዝ፣ በዚህም ምድርን በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ራሱ ለመመለስ ይፈልጋል። ሐዋርያው ጳውሉስም እንደሚነግረን "የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ" መጠበቅ (ሮሜ 8፥19) የሆነው በእርግጥም ለዚህ ነው።

የሰውን ጉድለት ለመሙላት የደኅንነት ወንጌል አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይነታችን ለሌሎች የምንደክም ብቻ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥ ያለውን ቀዳሚ ዐላማ እንስታለን፣ ይኸውም የሰውን ጉድለት ሳይሆን የራሱን ፍላጐት ማሟላት ነው። አስቀድመን እንዳልነው፣ የሰው መፈጠር የእግዚአብሔርን ፍላጐት ለማሟላት ነው። ስለዚህ ዛሬ የእግዚአ ብሔርን ፍላጐት ለመገናኘት ከፈለግን፣ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ተራምደን ከራሱ ከሰይጣን ጋር ያለውን ጉዳይ መወጣት አለብን። የሰረቀውን ኀይል ማስመለስ፣ ከግዛቱ መንቀል፣ ንብረቱን መበዝበዝና ምርኮኞቹን ነጻ ማውጣት አለብን - ለእግዚአብሔር። ስለዚህ ጥያቄው፣ ነፍሳትን በመማረክ ውስጥ የገባነው በምን ምክንያት ነው? የሚል ብቻ ሳይሆን፣ ይልቅ በሥልጣናትና በኀይላት ግዛት ውስጥ ያለነው በምን ምክንያት ነው? የሚል ነው። ለዚያ ደግሞ የምንከፍለው ዋጋ አለ።

ብዙ ጊዜ፣ ሰይጣንን ከስፍራው ማንቀሳቀስ የማይቻል ሲሆን፣ ሰዎችን ማንቀሳቀስ የሚቻል ሆኖ ይገኛል። ግልጹ እውነት፣ ከሰይጣን ጋር ያለውን ጉዳይ መወጣት፣ ነፍሳትን ከመማረክ ይልቅ ዋጋ የሚያ

ስወጣ መሆኑ ነው። ይህም መንፈስን ወደ እግዚአብሔር ማቅናትን ይጠይቃል፣ ከዚህም ሰይጣን ራሱ በእኛ ውስጥ እንዲኖረው ሊሚገት የሚችልበትን ማንኛውንም ሞራላዊ መንደርደሪያ በብቃት ያሳጣዋል። ይህም ዋጋ የሚያስከፍል ነው። በአገልጋዮቹ ውስጥ የሚታየውን፣ ሌላው እንደ አስጸያፊ ድካምና እንደ ውድቀት የሚቈጥረውን ነገር፣ እግዚአብሔር ለጠፉት ባለው ምሕረት የተሞላ ፍቅር ምክንያት፣ ብዙ ጊዜ በይቅርታ ሊያልፋቸው ይችላል። ነገር ግን ጌታ ነፍሳትን ወደ ጌታ ለሚማርክ ሰው ይህንን ቢያደርግም፣ ከሰይጣን ጋር ያለንን ጉዳይ ወደ መወጣት ሲደረስ ግን ጉዳዩ ሌላ ነው።

እርኩሳን መናፍስት በሰው ምስክርነት በኩል አጮልቀው ማየት ይችላሉ። በግማሽ ልብ፣ ወይም ከዐንገት በላይ በመሆን ሲመ ቻመች ለይተው ያውቃሉ። ልንከፍለው የሚገባንን ዋጋ ስናስቀርም ያውቃሉ። እኛን በመመልከት ብቻ፣ ማንን ያለ ምንም ጉዳት መቋቋምና ችላ ማለት እንደሚችሉ በምንም መልኩ አይምታታ ባቸውም፣ በተቃራኒውም ከማን ጋር ደግሞ ለመጋጠም ኀይል አልባ እንደሚሆኑ በደንብ ያውቃሉ። "ኢየሱስንስ ዐውቀዋለሁ፣ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤እናንተሳ እነማን ናችሁ?" (የሐሥ. 19÷15)። ስለሚያምኑ መቼ መንቀጥቀጥ እንዳለባቸው ያውቃሉ። አንድ ለማለት የምፈልገው ነገር አለ - በጣም ጠቃሚው ተግባራችን የእነርሱ መገልበጥ ከሆነ፣ ከሰዎች ምስጋና ይልቅ የክፉ ኀይላትን ምስክርነትን ብናገኝ ይሻላል።

ነገር ግን የዚህ የሥልጣናትና የኀይላት ምስክርነት ዋጋው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ማበርን ከመግለጽ አኳያ ዋጋ ቢስ ነው። የራሳችንን አሳብና ምኞት ማስተናገድ፣ ወይም የተለያዩና የሚጋጩ ምርጫዎቻችንን ማስቀደም ለጠላት ጥቅምን ማቅረብ ነው። በአጭሩ፣ ፍልሚያውን አሸቀንጥሮ መጣል ነው። በሌላ በማንኛውም ጉዳይ ላይ፣ ምናልባት ያለ ከባድ ኪሳራ ለራሳችን ጥቅም በተጓዳኝ የምናካሂደው፣ የራሳችን ጉዳይ ሊኖር ይችላል። በዚህ ጉዳይ ግን - ፈጽሞ! ከእንደ ዚህ ዐይነቱ ለእግዚአብሔር ፍጹም መስጠት ውጭ ምንም ማከናወን አይቻልም፣ ምክንያቱም ያለዚህ እግዚአብሔርን እንኳ ጠላቱን በሚ መለከት ኀይል አልባ እናደርገዋለን።

ስለዚህ አንድ ጊዜ ደግሜ እናገረዋለሁ - ተፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው። እናንተና እኔ እዚህ በምድር ላይ፣ በግልጽ ወስነን ለእግዚአ ብሔር ሙሉ በሙሉ ተሰጥተናል? በዚህም ምክንያት፣ ሊመጣ ያለውን የከበረ ዘመን ኀይሎች አሁን እየቀመስን ነውን? ከዚህ በፊት የሰረቀውን፣ በዚህ ዓለም አምላክ እጅ ያለውን ግዛት፣ ለብቸኛው ባለ መብት እንደገና ለመመለስ እየተሚገትን ነውን?



## ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## ያለ አግባብ ዘሩፉትን የያዘውን መዝረፍ

"ኀጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ" (1ጢሞ. 1÷15)። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ መሠረት ኀኘርነቱን መያዝ ያለበት ሰው በመሆኑ፣ ርኅራኄአችን ወደ እነዚያ ኀጢአተኞች መሆኑ የሚጠበቅም፣ ትክክልም ነው። እስከ አሁን የተባሉት ሌሎች ነገሮች ቢኖሩም እንኳ፣ በዚህ አጭር የጸጋ ቀን ነፍሳትን ወደ ዓለም መድኀኒት ማምጣት፣ ከሰይጣን ምርኮዎቹን የምንዘርፍበት የላቀው መንገድ መሆኑ፣ ምናልባት በደንብ ይሰማን ይሆናል። "ሰው" የእስካ ሁን ትልቁ ርዕሳችን ስለ ነበር፣ በዚህ ነጥብ ላይ ነፍሳትን ስለ መማ ረክ ትልቅ ስፍራ መስጠት አለብን።

ነገር ግን ስለ ወንጌል ሥርጭት ከዚህ በፊት በሌላ ስፍራ[1] ተነጋግረናል። ስለዚህ በዚህ ምትክ፣ ይህንን ስለ "ዓለም" የምናካ ሂደውን ጥናት ስናጠቃልል "ኀይለኛውን ሰው በመበዝበዝ"፣ ተግባራዊ ምሳሌ በመጠቀም፣ የሰይጣን የበላይነት የሚታይበትን ሌላ ቁሳዊ አካ ባቢ እንድንመለከት አሳብ አቀርባለሁ። ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ማለቴ ነው።

ገንዘብ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ ሲናገር "የዓመፃ ገንዘብ" ይለዋል (ሉቃ 16÷9)። ኢየሱስ "በእርሱ (በዐመፃ ገንዘብ) ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ" ሲል፣ ይህን በዐመፃ ድርድር እንዳገኛችሁት ገንዘብ መተንተኑ አይደለም። ገንዘቡ ራሱ ዐመፃ ነው እያለ ነው። በዚህ ስፍራ የቀረበልን፣ ገንዘብ የተገኘ በት የዐመፃ መንገድ ወይም በገንዘብ የሚፈጸመው ዐመፃ ሳይሆን፣ *የገንዘብ የዐመፃ ባሕርይ ነው።* ገንዘብ በመሠረታዊ ባሕርይው ክፉ ነው። እኛ ስለ "ንጹሕ ገንዘብ" እና "ቆሻሻ ገንዘብ" እናወራለን፣ በእግዚአብሔር ዕይታ ግን ቆሻሻ ገንዘብ ብቻ ነው ያለው። እግዚአብ ሔርን የሚያውቅ ሰው የገንዘብን ባሕርይ ያውቃል። ገንዘብ በራሱ ክፉ እንደ ሆነ ያውቃል።

የማንኛውንም ነገር ባሕርይ መፈተን ከወደዳችሁ፣ ያ ነገር ወደ እግዚአብሔር የሚመራችሁ፣ ወይም ከእግዚአብሔር የሚያርቃ ችሁ መሆኑን ብቻ ነው፣ መጠየቅ የሚያስፈልጋችሁ። ገንዘብ ደግሞ

---

[1] - What Shall This Man Do? ምዕራፍ 3

ከእግዚአብሔር ያርቃል። ኢየሱስም እግዚአብሔርንና ገንዘብን ማገልገል እንደማይቻል መርሑን በቍጥር 13 ላይ አስቀምጦአል፤ ለነገሩ እርሱ ባይናገረውም እንኳ፣ አብዛኞቻችን በዚህ ጉዳይ እንተማመናለን ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔርና ገንዘብ ፈጽሞ በአንድ አቅጣጫ እንዳልሆኑ ልምምድም ይነግረናል፤ ገንዘብ ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ላይ የሚነሣ ነው።

የኢየሱስን ቃላት ሰፋ አድርጎ መተርጐምና "ገንዘብ" እግዚአብሔርን የሚቃወመውን ነገር ሁሉ አጠቃልሎ እንደሚወክል ማየት ይቻላል። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ገንዘብ፣ እኛን ከእግዚአብሔር ለማራቅ ዓለም በተሳካ ሁኔታ የሚጠቀምበት መንገድ መሆኑን እንድናውቅ ይረዳናል። "ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ" አለ ጳውሎስ ሲጽፍ፣ "በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና÷ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ" (1ጢሞ. 6÷9-10)። በሌላ አነጋገር፣ ከእግዚአብሔር አስኮብልሎ የሚያርቀን ምንም ነገር ካለ፣ እርሱ ገንዘብ ነው።

የዓለም ፍሬነገር ገንዘብ ነው። ገንዘብን በምትነኩ ጊዜ ሁሉ፣ ዓለምንም ትነካላችሁ። ስለዚህ በዓለም አሠራር ውስጥ ተሳታፊ ሳንሆን፣ የዓለም መሆኑን አስረግጠን የምናውቀውን ነገር እንዴት መውሰድ እንችላለን? ከዓለም ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ዓለማዊ የሆነውን ነገር - ገንዘብን - በሰይጣን የጥፋት ተግባር ተካፋይ ሳንደረግ፣ እንዴት መቈጣጠርና ጥቅም ላይ ማዋል እንችላለን? የሚል ጥያቄ ይነሣል። ወደ ዋናው ነገር ስንመጣ ደግሞ - ዛሬ ሳይከፈልበት የሚሠራ ምንም ነገር የለምና የክርስቶስ ተቃዋሚውን መንግሥት በመገንባት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለውን ነገር - ገንዘብን በመውሰድ የክርስቶስን መንግሥት ለመገንባት እንዴት ልንጠቀምበት ይቻለናል?

የነበራትን በጣም ጥቂቱን ነገር በመቅደሱ የገንዘብ መቀበያ ሳጥን ውስጥ የጣለችዋ መበለት፣ ድርጊቷ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ስላገኘ፣ በእርሱ ተሞገሰች። ያደረገችው እንዲህ ነው - ከሰይጣን መንግሥት ውስጥ የሆነ ነገር ወሰደችና ለእግዚአብሔር መንግሥት አበረከተችው። ኢየሱስም ድርጊቷን አጸደቀ። ስለዚህ፣ እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፣ ይህ ዐይነቱ ዝውውር የሚደረገው እንዴት ነው? ባሕርይው በመሠረቱ ዐመፃ የሆነውን፣ ገንዘብን ወስደን እንዴት ነው የእግዚአብሔርን መንግሥት ልንገነባበት የምንችለው? በዓለምና በኪሳችሁ ውስጥ ባለው ገንዘብ መካከል ያሉት ግንኙነቶች በሙሉ መቋረጣቸውን እንዴት ማረጋገጥ ትችላላችሁ? በእጃችሁ የሚገኘው የትኛውም



ገንዘብ በሰይጣን የሂሳብ መዝገብ ላይ ያልሰፈረ መሆኑንስ ደፍራችሁ ትናገራላችሁ?

በእያንዳንዱ የሮማ ዲናር ላይ የቄሳር ምስል ነበር። እንደዚህ ዐይነት ሳንቲሞች በሙሉ፣ በኢየሱስ አነጋገር "የቄሳር ናቸው"። ታዲያ በቄሳርና በዚያ ሳንቲም መካከል ያለው ትስስር፣ እንዴት ነው ሊበጠስ የሚችለው? ገንዘብ የዓለም ነገር ነው። የዓለም አሠራርም መሠረታዊ ክፍል ነው። ታዲያ በገንዘብ ላይ የባለቤትነት ጥያቄ ከሚያነሣው ዓለም ተወስዶ፣ ገንዘብ ለእግዚአብሔር ሥራ እንዴት ሊውል ይችላል?

በብሉይ ኪዳን ዘመን የወጣ አንድ ጥብቅ መመሪያ ነበር። "ለእግዚአብሔር ተለይቶ የተሰጠ ማንኛውም ነገር፡- ሰውም ሆነ እንስሳ ወይም በውርስ የተገኘ መሬት አይሸጥም፤ አይዋጅምም። ለእግዚአብሔር የተሰጠ ማንኛውም ነገር እጅግ የተቀደሰ ነውና" (ዘሌ. 27÷28 - አ.መ.ት)። በሌላ አነጋገር፣ ያለ መፍረስ እውነተኛ መስጠት አይኖርም። በእነዚያ ቀናት አንድ በግ ለእግዚአብሔር ከተሰጠ፣ በእግዚአብሔር ፊት ሕያው ሆኖ እንዲቈይና እንዲረባ ሳይሆን የሚደረገው፣ መሥዋዕት እንዲሆን በእርሱ ፊት ይቀርባል። "ፈጽሞ ይገደላል" (ቍጥር 29)። መፈራረሱ (መሞቱ) ተቀባይነት የማግኘቱ ምልክት ነው።

በእውነት ለእግዚአብሔር የተሰጠ ገንዘብ በሙሉ፣ በዚህ የመፈራረስ (የመጥፋት) መርሕ ሥር አልፎ መምጣት አለበት፤ ማለትም፣ ዓለምን በተመለከተ ሕልውናው ማብቃት አለበት፣ እኔን በሚመለከትም ሕልውናው ማብቃት አለበት። ጌታችን ሁለቱን ሳንቲሞች በመዝገቡ ውስጥ ስላስቀመጠች መበለቲቱን ሲያመሰግናት፣ ትዳሯን - ጠቅላላውን ሕይወቷን እንዳስቀመጠች ተገንዝቦአል። "ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን *(bios - ሕይወቷን)* ሁሉ ጣለች" (ማር. 12÷44)። ብዙ ሰዎች በጌታ መዝገብ ውስጥ ገንዘባቸውን ብቻ ያስቀምጣሉ፤ እርሷ ግን ሕይወቷን ከገንዘቧ ጋር አስቀመጠች። በሌላ አነጋገር፣ ያ ገንዘብ ከእርሷ ይዞታ ሲወጣ ሕይወቷም አብሮት ወጥቶአል። ሁለቱን ሳንቲሞቿን በመስጠት ሁለንተናዋን ሰጥታለች።

ገንዘባችሁ ከዓለም መውጣት ካለበት፣ ሕይወታችሁም ከዓለም መውጣት ሊኖርበት ነው። ራሳችሁን ወደ ኋላ አስቀርታችሁ፣ ትርጕም ያለው ነገር ለእግዚአብሔር ማበርከት አትችሉም፤ ገንዘባችሁን ከዓለም ውጭ መላክ በፍጹም አትችሉም፤ ከዓለም ይዛችሁት መምጣት ብቻ እንጂ!

ስለዚህ ገንዘብን ከሰይጣን ክልል ወደ እግዚአብሔር ክልል ማሻገር ቀላል ጉዳይ አይደለም - ምጥ ይጠይቃል። ነፍሳትን ከሰይጣን

የእግዚአብሔር ወደ መሆን መለወጥ፣ ገንዘብን ከሰይጣን የእግዚአብሔር እንዲሆን ከመለወጥ በእርግጥም የቀለለ ነው። እኛ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት ባይኖረንም፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ወደ ጌታ ይመጡ ይሆናል፤ ከገንዘብ ጋር ግን እንዲህ አይደለም። ሰቅሎቻችንን - በባሕርያቸው ክፉ የሆኑትን፣ ወደ መቅደሱ ሰቅል ለመለወጥ ትልቅ መንፈሳዊ ኀይል ይጠይቃል። ሰዎች ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ያህል፣ ገንዘብም ለውጥ ያስፈልገዋል፣ እንደዚሁም ነፍሳት አዲስ የሚሆኑትን ያህል ገንዘብም (በሌላ መልኩ ቢሆንም) አዲስ መሆን እንደሚችል አምናለሁ። ነገር ግን ወደ መቅደሱ ስጦታ ማምጣታችሁ በራሱ፣ የሰጣችሁትን ገንዘብ ባሕርይ አይለውጠውም። ሕይወታችሁ ከገንዘባችሁ ጋር ካልወጣ፣ ከሰይጣን መንግሥት ተላቅቆ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መሻገር አይችልም። ለእግዚአብሔር የምትሠሩት ሥራ መንፈሳዊ ዋጋም፣ በእጃችሁ ያለው ገንዘብ ከዓለም አሠራር በመውጣቱና ባለመውጣቱ ላይ በጣም ይወሰናል። እናም እጠይቃችኋለሁ፣ ይህ ሆኗልን? በእጃችሁ የዓለም የሆነ ምንም ገንዘብ አለመኖሩን መናገር ትችላላችሁ? ገንዘባችሁ ሙሉ በሙሉ ተለውጦአልና ከእንግዲህ የኮስምስ ክፍል እንዳልሆነ ለመናገር ትችላላችሁ? ለእግዚአብሔርስ፣ “በላቤ ያገኘሁትንም ሆነ በስጦታ ያገኘሁትን ገንዘብ በሙሉ የአንተ ይሆን ዘንድ እለውጠዋለሁ” ብላችሁ ልትነግሩት ፈቃደኛ ናችሁ?

ይህ መርሕ ለጳውሎስ በጣም ግልጽ ነበር - የምንፈልገው የእናንተን ሳይሆን እናንተን ነው። ከጥልቅ ድኽነታቸው ከፍ ያለ ልግስና ስላደረጉት፣ የመቄዶንያ ቅዱሳን ሲናገር፣ “በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ” ከዚያም ገንዘባቸውን ሰጡ (2ቆሮ. 8÷5 - አ.መ.ት - ሕያው ቃል) ብሎአል። ጳውሎስ ልምምዱን ያገኘው፣ ቁሳዊ ስጦታዎችን መቀደስ፣ ስጦታዎቹን ያመጡትን ሰዎች ከመቀደስ ጋር ሁል ጊዜም የተያያዘ ከሆነበት፣ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ነው። ለዚህ አባባሉ መነሻ ያገኘው ከዚያ ይሆናል።

አስደንጋጭ ሊሆን ይችላል፣ ግን እውነት ነው፤ እግዚአብሔር ያለው የተወሰነ የገንዘብ አቅርቦት ሲሆን፣ የሰይጣን የገንዘብ አቅርቦት ግን ያልተወሰነ ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ከሌላኛው ጋር - ብሩም ሆነ ወርቁ የእርሱ እንደ ሆነ ከሚናገረው ጋር እንዴት ሊታረቅ ይችል ይሆን ብላችሁ ምናልባት ትደነቁ ይሆናል። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ራሱ ለእግዚአብሔር የተገባ እና ለቄሳር የተገባ እንዳለ ተናግሮአል። በፈጣሪነቱ ሁሉም ቁሳዊ ነገሮች ለእግዚአብሔር የተገቡ እንደ ሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ነገር ግን ዛሬ በእግዚአብሔር መዝገብ ውስጥ ያለው የገንዘብ መጠን፣ ራሳቸውን ለእርሱ በሰጡት ሰዎች ብዛት የተወሰነ ነው።



በብሉይ ኪዳን ዘመን ብኖር ኖሮ በመቅደሱ ውስጥ ያለውን የገንዘብ መጠን ወዲያውኑ ማስላት እችል ነበር። የእስራኤል ልጆችን ጠቅላላ ብዛት እጠይቅና እያንዳንዳቸው ለሕይወታቸው ቤዛ የሚሰጡትን ግማሽ ሰቅል እቈጥር ነበር (ዘፀ. 30÷11-16)። በዚህም ላይ ከሌዋውያን ብዛት በላይ ከሚሆኑት የበኵር ልጆች መካከል፣ ለእያንዳንዱ የበኵር ልጅ ቤዛ የሚሆን በነፍስ ወከፍ 5 ሰቅል እጨምርበታለሁ (ዘኁ. 3÷39-51)። በእነዚህ በሁለቱ ድምር ላይ ደግሞ፣ ራሱን በፈቃዱ ለእግዚአብሔር ለሰጠ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ መቅደሱ ሚዛን የተገመተውን ዋጋ እደምርበታለሁ (ዘሌ. 27÷1-8)። አዎን፣ የእግዚአብሔርን የገንዘብ መጠን የሚወስነው የእግዚአብሔር ሕዝብ ብዛት ነው። በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ያለው ሀብት፣ ራሳቸውን ለእርሱ በሰጡ ሰዎች ብዛት ላይ የተመሠረተ ነው።

ስለዚህ፣ እዚህ ጋ ሁላችንም የምንመልሰው አንድ ወሳኝ ጥያቄ አለ - ዛሬ እየነካሁት ያለው ገንዘብ፣ መቅደሱን ነው የሚወክለው ወይስ የዐመፃን ገንዘብ? አንድ ብር ስቀበል ወይም አንድ ብር ሳተርፍ፣ ያ ብር ከዓለም ምንዛሪነት ወደ መቅደሱ ምንዛሪነት መለወጡን አረጋግጣለሁ። ገንዘብ መጥፊያችን ሊሆን ይችላል፤ ገንዘብ ከለላችን ሊሆንም ይችላል። ገንዘብን አትናቁ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነው። ለጌታ ለሚሆን ትልቅ ሥራ ሊውል ይችላል። እናንተ ራሳችሁ ከነልባችሁና ከነነፍሳችሁ ከዓለም ከወጣችሁ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ከእናንተ ጋር ብዙ የከበሩ ነገሮችን ከዓለም ማምጣት ትችላላችሁ። እስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ ብዙ ንብረት ይዘው ነው የወጡት። ግብፃውያንን በዝብዘዋል፣ ተሸክመው የመጡትም ብዘበዛ የማደሪያውን ድንኳን ለመገንባት ውሎአል። የተወሰነው ደግሞ የወርቁን ጥጃ ለመሥራት ውሎ ለእግዚአብሔር ምንም ያልጠቀመ እንደ ሆነ እናስታውሳለን። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ግብፅን ሲለቁ፣ የማደሪያውም ድንኳን ቢያንስ በቁሳቁሶቹ (በጥሬ ዕቃዎቹ) ውስጥ አብሮአቸው ግብፅን ለቆአል። የግብፃውያን ወርቅ፣ ብር፣ ግምጃ - በሙሉ ተለውጦ ለእግዚአብሔር መቅደስ ውሎአል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያንን እውነታ ማግኘት ከቻላችሁ፣ በአዲስ ኪዳን የተቀመጠው ደረጃ ደግሞ ምንኛ ይልቅ ይሆን! ገንዘብን በሚመለከት የአዲስ ኪዳን ቁልፉ፣ ለራሳችን ምንም አለመያዛችን ነው። የጌታ ቃል፣ “ስጡ ይሰጣችሁማል” የሚል ነው (ሉቃ. 6÷38) እንጂ፣ “ቆጥቡ እና ወደ ሀብታምነት ታድጋላችሁ” የሚል አይደለም! ይህም መለኮታዊው የብዜት መርሕ፣ መስጠት እንጂ ማከማቸት አለመሆኑን ለመናገር ነው። እግዚአብሔር እያንዳንዳችን ዋጋችንን የምንተምን እንጂ እንዲሁ እንዳመጣልን የምንሰጥ እንዳንሆን ይጠብቅ

ብናል። መስጠታችን በዚያ ቅጽበት ድንገት በሚመጣብን፣ "በል በል" የሚል ስሜት የሚመራ ሳይሆን፣ በጉዳዩ ላይ ከእርሱ ጋር የደረስን በትና አጥብቀን የምንይዘው የኪዳኑ ፍሬ እንዲሆንልን ይመኛል።

የዚህም ምክንያት፣ ሰይጣንን የመበዝበዣው እውነተኛ ምስጢር - እስካሁን እንዳየነው - ግላዊ መስጠት በመሆኑ ነው። ለእኛ፣ ከዓለም ተዋጅተን ሳለ በውጤቱ ራሳችንን ለእግዚአብሔር አለማቅረብ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው። "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም" (1ቆሮ. 6፥19-20)። ከዓለም ትርፍ እንዲያመጣልን የተከተልነው ንግድን ወይም ሌላ ሙያዊ የሥራ መስክ ቢሆን፣ ወይም ደግሞ ወንጌልን በመስበክ ላይ ብቻ ተወስነን ከእግዚአብሔር ሕዝብ በምናገኘው ስጦታ የምንተዳደር መሆናችን፣ የሚያመጣው ልዩነት የለም፣ ከፊታችንም ያለው መንገድ ሁለት ሳይሆን አንድ ነው። ሁላችንም በእኩልነት ለእግዚአብሔር የተሰጠንና ሁላችንም የእርሱ ምስክሮች ነን። ወንጌልን መስበክ በራሱ ንጹሕ፣ የንግድ ሥራ ደግሞ ንጹሕ ስላልሆነ፣ በኋለኛው ሥራ ውስጥ ያሉት ሰዎች በመደነዛቸው እግዚአብሔርን ከመጥቀም አኳያ ዋጋ የሌላቸው የሚሆኑበት ፈሊጥ፣ እውነት አይደለም።

"ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አትውደዱ" (1ዮሐ. 2፥15 አ.መ.ት)። ከቅዱሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅባት አግኝታችኋል - ኑሩበት! ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ፣ ለእርሱም በሙላትና በግልጽ ኑሩ! እናንተን በግል በሚመለከት የዚህ ዓለም ነገሮች ከሰይጣን መዝገብ ላይ ተፍቀው ወደ እግዚአብሔር ሂሳብ የተሻገሩ መሆናቸውን አስተውሉ። "ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል" (2፥17)።



## ምስጋና

ለዚህ ሥራ የከበረ ጊዜአቸውን ሠውተው ለረዱኝ፡-

- ☞ ለፈቃደ ተሰማ (መጋቢ)
- ☞ ለመሐሪ ታደሰ
- ☞ ለደረጀ በላይነህ
- ☞ ለልዑል ገብርኤል
- ☞ ለሐሊማ መሐመድ

እንዲሁም ለመተርጉም ስዘጋጅ እንግሊዘኛውን መጽሐፍ ላዘጋጁልኝ ለጋሽ ታደሰ ተስፋይ እና ለሌሎችም በስም ላልጠቀስኳቸው፣ በተለያየ መንገድ ላበረቱኝ ሁሉ "ሰላም" ይሁንላቸው።